# ኢትዮጵያዊው

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢት
ዮጵያ ፡ ፴፪ኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፤ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ብርሃንና ፡
ሰላም ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

መብቱ ፡ የደራሲው ፡ ነው ።



ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።





የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡
አስፋ ፡ ወሰን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

## ማ ው ጫ ።


ገጽ ፤

፩. መቅድም ............................................ ፱
፪. ሕይወት ............................................ ፲፩
፫. የልጅ ፡ ሽማግሌ ፡ ............................................ ፲፫
፬. ታሪኩ ፡ ታዬ ፡ ............................................ ፳፩
፭. አቻ ፡ ጋብቻ ፡ ............................................ ፴፩
፮. የልጅና የሀብት ፡ ጸጋ ፡ ............................................ ፶፮
፯. ምርቅና ፡ ፍትፍት ፡ ............................................ ፷፩
፰. የአቶ ፡ ግሩምና ፡ የወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ፍች ፡ ............ ፸፫
፱. የወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ የገዳም ፡ ኑሮ ፡ ............................ ፺፭
፲. የቤተሰብ ፡ ውይይት ፡ ............................................ ፻፳፩
፲፩. መርዶ ፡ ............................................ ፻፴፫
፲፪. የቡርከትና ፡ የዕምላዕሉ ፡ ጋብቻ ፡ ............................ ፻፶፫
፲፫. ታሪካዊ ፡ ሥፍራዎችን ፡ መጐብኘት ፡ ........................ ፻፷፱
፲፬. ወደልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ጉዞና ፡ ጉብኝት ፡ ............ ፪፻፲፮
፲፭. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጅቶችን ፡ ማቋቋም ፡ ........................ ፪፻፴፮

# መ ቅ ድ ም ፡

ኻያኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የቴክኖሎጂ፡ ዘመን ፡ በመሆኑ ፤ የሰው ልጅ ፡ ዕውቀቱን ፡ እያስፋፋ ፡ እንደመሄዱ ፡ መጠን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍትም ፡ በየዓመቱ ፡ በብዛት ፡ በመጻፋቸው ፤ ሰው ፡ ከሥራ ፡ የሚተርፍ ፡ ጊዜውን ፡ በሌላ ፡ ማሳለፉን ፡ እየቀነሰ ፡ ውሎውን ፡ ከመጻሕፍት፡ ጋር ፡ ያደርጋል ።

ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ መጻሕፍትን ፡ ለማንበብ ፡ ወይም ፡ ለመጻፍ ፤ ከልብ ፡ የገነፈለ ፤ ፍላጐትና ፡ ፈቃድ ፡ መኖር፡ አለበት ። በታዳጊ ሀገሮች ፡ በየዓመቱ ፡ የሚታተሙት ፡ መጻሕፍት፡ ቊጥር ፡ እጅግ ፡ ከፍ ብሎ ፡ የሚታየው ፤ የሕዝቡ ፡ መጻሕፍት ፡ ማንበብ ፡ ፍላጐት ፡ የጋለ ፡ በመሆኑ ፡ የቆዩ ፡ ደራስያንም ፡ የሕዝቡን ፡ የማንበብ ፡ ፍላጐት ፡ ለማርካት ፡ በበኩላቸው ፡ በርትተው ፡ ስለሚጽፉና ፤ አዳዲስ ፡ ደራስያንም፡ በየጊዜው ፡ በመፈጠራቸው ፡ ነው ።

የማንበብ ፡ ፍላጐት ፡ ያላቸው ፡ እንኳን ፡ በሌላው ፡ ጊዜ ፤ ለዕረፍት ፡ ወይም ፡ ለመዝናናት ፡ ወደልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራ ፡ ሲሄዱ ፤ የሚያነቡዋቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ይዘው፡ ይሄዳሉ ። ለምሳሌ ፤ ዋና ፡ የሚዋኙ ከባሕሩ ፡ ወጣ ፡ ብለው ፡ ሲያርፉ ፡ አጭርዋን ፡ ጊዜ ፡ መጻሕፍትን ፡ በማንበብ ፡ ያሳልፋሉ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ የማንበብ ፡ ፍቅርና ፡ ፍላጐት ፡ ስላለ ፡ ነው ። በመጻሕፍት ፡ የሚተላለፍ ፡ መልእክት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ለሥጋዊም ፡ ሆነ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ሕይወቱ ፡ ምግብ ፡ ነው ።

ከመጻሕፍት ፡ የሚገኝ ፡ ትምህርት ፤ ያዘነን ፡ ልቡና ፡ ያጽናናል ። የተሸበረን ፡ መንፈስ ፡ ያረጋጋል ። የዓለምን ፡ አቅዋም ፡ መስተዋት ፡ ሆኖ ፡ ያሳያል ። ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሲኖር ፡ ለመኖሩ ፡ ምልክት ፡ የሚሆን ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ ይመራዋል ። ከሰው ፡ ይልቅ ፡ የመጻሕፍት ፡ ጓደኛነት ፡ ዋስትና ፡ ላለው ፡ ኑሮና ፡ ወደዘለዓለማዊ ፡ ድኅንነት ፡ ይመራል ።

መጽሐፍ ፡ ታትሞ ፤ ጥራዙንና ፡ አርእስቱን ፡ አሳምሮ ፡ ሲቀርብ ፤ በአፋዊ፡ አቀራረቡ፡ ዓይንን፡ የማረከው፤ በውስጡ፡ የያዘውን፡ ለማወቅ፤ በጅምር፡ ንባብ፡ ብቻ፡ አይረባም ፡ ይረባል ፡ ከማለት ፤ ወይም ፡ አለፍ ፡

አለፍ ፡ ብሎ ፡ ከማንበብ ፤ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ በጽሞና ፡ ያነበበ ፡ አንባቢ ፡ ትክክለኛውን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።

ይህ ፡ « ኢትዮጵያዊው » የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ታሪኩን ፡ አተኩሮ ፡ ለተከታተለው ፡ ከልብ ፡ ወለድ ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ ያዘነበለ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይመዝነው ፡ ይሆናል ።

በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ስሞች ፡ አሉ ። በመጻሕፍትም ፡ በማ ናቸውም ፡ በኩል ፡ አንዱ፡በሚጠራበት ፡ ስም ፡ ሌላው ፡ እንዳይጠራ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ስለስም ፡ አጠራር ፡ የሚከለክል ፡ ሕግ ፡ አለመ ኖሩ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ስሞች ፡ ለጽሑፉ ፡ ባለታሪኮች ፡ መጠሪያ ፡ የወጡ ፡ ከመሆናቸው ፡ በቀር ፡ ታሪኩ ፡ በነዚህ ፡ ስሞች ፡ የሚጠሩ ፡ ሰዎችን ፡ ታሪክ ፡ የማይ መለከት ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ው ፤



# ሕ ይ ወ ት ፡

እኖራለሁ ፡ እንጂ ፡ በአካሌ ፡ ሠርቼ ፤
አልሻም ፡ ለመኖር ፡ በሰው ፡ ተመክቼ ።

በሰው ፡ መታመኑ ፡ ዳርቻም ፡ የለው ፤
ከዓይናችን ፡ ሲጠፉ ፡ መሄጃው ፡ የት ፡ ነው ?

እናስብ ፡ ይልቁን ፡ የሚያዋጣንን ፤
ከሁሉ ፡ እንደሚበልጥ ፡ በራስ ፡ መታመን ።

በራሱ ፡ ያልቆመ ፡ የተጠራጠረ ፤
ሳይይዘው ፡ አንዱንም ፡ በቅዠት ፡ ላይ ፡ ቀረ ።

አጣዳፊው ፡ ዓለም ፤ አጋፋሪው ፡ ብዙ ፤
ራስን ፡ ካልቻሉ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ መዘዙ ።

ጠንካራ ፡ አካል ፡ ራስ ፡ ሁሉን ፡ ተሸካሚ ፤
አንዳች ፡ ከተሜነው ፡ ይሆናል ፡ ታማሚ ።

ይፈለግ ፡ አጥብቆ ፡ የራስ ፡ መድኃኒት ፤
ያስፈልጋልና ፡ ጤናማ ፡ ሕይወት ።

ተጠብቆ ፡ ጤና ፡ አካላት ፡ ከጸና ፤
ይገኛል ፡ ፀጥታ ፡ ይተኛል ፡ ሕሊና ።

ከረጋ ፡ ሕሊና ፡ ከተደላደለ ፤
ሐሳብ ፡ ለማመንጨት ፡ የሚያግደው ፡ የለ ።

የሐሳብ ፡ በሽታ ፡ የሕሊና ፡ ጻዕር ፤
ዕንቅፋት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ተስፋን ፡ የሚሰብር ።

ውሳጣዊ ፡ ልቤን ፡ ማየት ፡ ቢቻልማ ፤
ትሞት ፡ ነበር ፡ አዝና ፡ ርኅሩኋ ፡ እማማ ።

ውስጠ ፡ ልቦናዬ ፡ በእሳት ፡ ተቃጠለ ፤
ለሚያየኝ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ደኅና ፡ እየመሰለ ።

እስቤ ፡ ነበረ ፡ ለቤታችን ፡ ዋልታ ፤
አልቻልኩም ፡ ላቆመው ፡ ይሻላል ፡ ዝምታ ።

እስቤ ፡ ነበረ ፡ በንጹሕ ፡ ሕሊና ፤
ባልጠበቅሁት ፡ መንገድ ፡ አደረጉት ፡ መና ።

ያንዱን ፡ ሐሳብ ፡ አንዱ ፡ መቸ ፡ ያውቀውና !!!

ሆድ ፡ ነገር ፡ አማቂ ፤ አፍ ፡ ግን ፡ እሳት ፡ ጫሪ ፤
አልተገኘም ፡ እኮ ፡ የልብ ፡ መካሪ ።

ካልተመከረበት ፡ የጋራ ፡ ቤታችን ፤
መሠረቱ ፡ አይጸናም ፡ የአንድነታችን ።

መሠረት ፡ ሳይኖረው ፡ የተሠራ ፡ ቤት ፤
የሚመጣበትን ፡ አይችል ፡ አይመክት ።

አይጠቅመንምና ፡ እናጥፋ ፡ ጥላቻ ፤
ዘመኑም ፡ አይፈቅድም ፡ ያፍ ፡ ሽንገላን ፡ ብቻ ፤
በእጃችን ፡ ውስጥ ፡ ይኑር ፡ ያንድነት ፡ መክፈቻ ።

ያንድነታችንን ፡ ከያዝነው ፡ ቁልፉን ፤
ማንም ፡ አይከፍተውም ፡ የወል ፡ ቤታችን ።

ኃላፊ ፡ ነው ፡ ገንዘብ ፡ ይመጣል ፡ ይሄዳል ፤
እያታለለ ፡ ግን ፡ ስንቱን ፡ ይለውጣል ።

የፍላጐት ፡ አዝማች ፡ ክዳኑ ፡ ገንዘብ ፤
ሰውሮ ፡ ሕሊናን ፡ ያራውጣል ፡ ሕዝብ ።

ቤተ ፡ ሠሪ ፡ ሁሉ ፡ እታያለሁ ፡ ባይ ፤
ለዘላለም ፡ ሕያው ፡ ነዋሪ ፡ መሳይ ።

የሠራም ፡ ያልሠራም ፡ ልቡ ፡ እየነደደ ፤
አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ሳይዝ ፡ እየጣለ ፡ ሄደ ።

መጣሁ ፡ እዚህ ፡ ዓለም ፤ ሄድኩኝ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፤
ሥራ ፡ ላልሠራ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ሥፍራ ፡ የለም ።

ደክሜ ፡ ደክሜ ፡ ሥፍራ ፡ ካጣሁኝ ፤
ምነው ፡ በቀረብኝ ፡ ባልተፈጠርኩኝ ።

ይህ ፡ ጣጣ ፡ እንዳለብኝ ፡ ባውቅ ፡ ስፈጠር ፤
እሞክር ፡ ነበረ ፡ ለመኖር ፡ በአጭር ።

እጠጣለሁና ፡ በተፈጥሮ ፡ ዋንጫ ፤
እቋቋመዋለሁ ፡ ምንም ፡ የለኝ ፡ ምርጫ ።



## ክ ፍ ል ፩ ፡

# የልጅ ፡ ሽማግሌ ፡

ከሕይወትና ፡ ከዓለምነሽ ፡ በ፲፱፻፲፰ ዓ፡ም ፡ በልደተ ሥጋ ፡ ወደ ዚህ ፡ ዓለም ፡ መጣሁ ። አራት ፡ ዓመት ፡ እስኪሞላኝ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሳለፍኳቸው ፡ ጊዜያት ፡ እንደምን ፡ እንደነበሩ ፡ ትዝ ፡ አይሉኝም ።

አራተኛ ፡ ዓመቴን ፡ አክብሬ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተላክሁ ፤ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ በአንድ ፡ ቀበሌ ፡ የሚገኝ ፡ የመንደር ፡ ትምህርት፡ ቤት ፡ ነበር ።

በዕድሜና ፡ በትምህርት ፡ ጓደኞች ፡ ከሆኑኝ ፡ ጋር ፡ የማደርገው፡ የልጅነት ፡ ዘመን ፡ ጨዋታ ፡ ትዝታው ፡ አሁንም ፡ በፊቴ ፡ ውል ፡ ይለኛል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሌቱ ፡ በቀን ፡ ተለውጦ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የምሄድበት ፡ ሰዓት ፡ እስኪደርስ ፡ እቸኩል ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካየሁት ፡ ደስታ ፡ ከፊቴ ፡ የማይጠፋው ፤ ያው፡ በመንደር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በዕድሜ ፡ እቻ ፡ ከሆኑኝ ፡ ባልንጀሮቼ፡ ጋር፡ ያሳለፍኩት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቀኑ ፡ በቀን ፤ ወራቱ ፡ በወራት ፤ ዓመቱ ፡ በዓመት ፡ በተለወጠ ፡ መጠን ፤ በዕድሜ ፡ እያደግሁ ፡ በአዕምሮ ፡ እየጐለመስኩ ፡ ሄድኩ ።

የቤተሰቦቼ ፡ የኑሮ ፡ አኳኋን ፡ ድካማቸውና፡ ልፋታቸው፡ ተሰማኝ፡ በትእዛዝም ፡ በፈቃዴም ፤ የምችለውን፡ ሥራ፡ እየሠራሁ፡ ድካማቸውን፡ ተካፈልኩ ።

አልፎ ፡ አልፎ ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ ሲጣሉ ፡ አያለሁ ። እናቴም ፡ ምርር ፡ እያለች ፡ ታለቅሳለች ። ጠጋ ፡ እያልኩ ፡ እጠይቃታለሁ ፤ ዕንባዋን ፡ እያፈሰሰች ፡ አትነግረኝም ።

አባትና ፡ እናቴ ፡ በዕድሜ ፡ የተራራቁ ፡ ናቸው ። እናቴ ፡ በአባቴ፡ ላይ ፡ ያላት ፡ ብሶት ፡ ከጊዜ ፡ ወደ—ጊዜ ፡ እየጨመረ ፡ ሔደ ።

በዕድሜ ፡ እየገፋሁ ፤ በአዕምሮ ፡ እየጐለመስኩ ፡ በሄድኩ ፡ መጠን ፤ የእናቴ ፡ ብሶት፡ በበለጠ፡ ተሰማኝ ፤ እናትና፡ አባቴ ፡ ለኔ ፡ ትክ

ክል ፡ ናቸው ፣ ሆኖም ፡ የእናቴን ፡ መሠረታዊ ፡ ብሶት ፡ ለማወቅ ፡ መንፈሴ ፡ በየዕለቱ ፡ ይጐተጐተኝ ፡ ጀመር ።

ችግሯን ፡ ለማወቅ ፡ ከመጓጓቴ ፡ የተነሣ ፡ በየጊዜው ፡ በመጠየቅ፡ አሰለቸኋት ፣ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ «አባትህ ፡ በዕድሜ ፡ ከሃምሳ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ናቸው ። ምክንያቱን ፡ አላውቅም ፣ የሚያስደስታቸው ነገር ፡ የለም ። በትንሹ ፡ በትልቁ ፡ በነገር ፡ ጦር ፡ ይወጉኛል ። ለባብሼና ፡ አጋጊጬ ፡ ወጣ ፡ ያልኩ ፡ እንደሆነ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ያኰርፋሉ። ውበትሽን ፡ ጠብቂ ፡ ማለት ፡ ቢቀርስ ፡ እንዴት ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ እንኳረፍ ? የማለቅሰው ፡ በአባትህ ፡ ሳይሆን ፡ በዕድሌ ፡ ነው ፡ ልጄ ፡ » አለችኝ ።

በመካከላቸው ፡ የተፈጠረው ፡ አለመግባባት ፡ እየተባባሰ ፡ ሄዶ ፣ እናቴም ፡ ብስጭትና ፡ ለቅሶዋን ፡ ቀጠለች ። በሌላ ፡ ልረዳት ፡ ባልችልም ፣ ከአጠገብዋ ፡ ባለመለየት ፣ ላረሳሳት ፡ ሞከርኩ ።

ለእናቴ ፡ ያለኝን ፡ የመቆርቆር ፡ ስሜት ፡ በማጤን ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፣ አባቴ ፡ በኔም ፡ ላይ ፡ ጥላቻ ፡ አደረበት ። በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ ይቆጣኛል ። ለኔ ፡ በማሰብ ፡ እናቴ ፡ በምታደርገው ፡ ተቃውሞ ፡ ከአባቴ ፡ ጋር ፡ ያላቸው ፡ ጠብ ፡ በበለጠ ፡ እየተባባሰ ፡ ሄደ ።

ጠባቸው ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፣ በሚያውቃቸው ፡ ሰው፣ ሁሉ፣ ተሰማ። አስታራቂዎች ፡ በመካከላቸው ፡ ገቡ ። በማስታረቅ ፡ ፋንታ ፡ ተናግረው ፡ በማናገር ፡ ጥላቻውን ፡ የሚያባብሱ ፡ ቊጥራቸው ፡ በዛ ።

የማያውቁትንና ፡ የማይጠረጠሩትን ፡ በየበኩላቸው ፡ ሰሙ ። እንዲያውም ፡ የባሰ ፡ ጉድ ፡ መጣ ። የኔን ፡ ልጅነት፣ የሚያጠራጥር ፡ ወሬ አባቴ ፡ ሰማ ፡ በምንና ፡ ምን ፡ እንደምመስለው ፡ አካሉን ፡ ከአካሌ ፡ ጋር ፡ ያስተያይ ፡ ገባ ።

አንቺን ፡ የመሰለ፡ ቆንጆ ፡ ከሽማግሌ፡ ጋር ፡ ሆነሽ ፡ እያሉ ፡ ንብረትዋን ፡ እንድታፈርስ ፡ እናቴን ፡ የሚያደፋፍርዋት፣ በዙ። በጠቅላላው፣ ያባትና ፡ የእናቴ ፡ ኑሮ ፡ ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ ተበላሸ ። የሚያባብስ፣ እንጂ፣ ተቆጥቶ ፡ የሚያስታርቅ ፡ ጠፋ ።

የዘመኑ ፡ ወዳጆች ፡ ነገሩን ፡ እያባበሱ ፡ ጠቡን ፡ በበለጠ ፡ ካጠነከሩ ፡ በኋላ ፣ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ የሁለቱ ፡ በአንድ ፡ ቤት ፡ መኖር ፡ በደም፣ ፍላት ፡ የከፋ ፡ ነገር ፡ ሊደርስ ፡ ስለሚችል ፡ እናቴ ፡ ቤትዋን ፡ ለቃ ፡



ወደዘመድ ፡ ቤት ፡ እንድትሄድ ፡ በቀረበው ፡ ምክር ፡ ሁሉም ፡ ተስማምተው ፣ እናቴ ፡ ከደረጃ ፡ ቤትዋ ፡ ወጥታ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ በደባልነት ፡ ተቀመጠች ፡ እኔም ፡ ከእናቴ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ ተሰደድኩ ።

ጉድ ፡ ቀጠለ ፣ አንተም ፡ ተው ፣ አንቺም ፡ ተይ ፣ በማለት ፡ ማስታረቅ ፡ ቀረና ፡ ንብረታቸውን ፡ እንዲካፈሉ ፡ ሐሳብ፣ ቀረበ። አባትና፣ እናቴ ፡ ነገሩን ፡ ቻል ፡ ብለው ፣ ይቅር ፡ ለቤታችን ፡ የማለት ፡ ሐሳብ ፡ እያላቸው ፡ የሁለቱ ፡ ጉዳይ ፡ በሌሎች ፡ ስለተያዘ ፣ እነርሱም ፡ በይሉኝታ ፡ ስለተያዙ ፡ በዝምታ ፡ መመራት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ።

ከእናቴ ፡ ጋር ፡ በሰው ፡ ቤት ፡ በስደት ፡ ባለሁበት ፡ ወቅት ፡ ትምህርቴን ፡ አቋርጫለሁ ። የትምህርት ፡ ጣዕም ፡ ጠልቆ ፡ ባይገባኝም ፣ ከጓደኞቼ ፡ ጋር ፡ የማደርገው ፡ ለዛ ፡ ያለው ፡ ጭውውት ፡ ትውስ ፡ እያለኝ፡ ጠዋት ፡ ማታ ፣ እማማ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ወደቤታችን ፡ የምንሄደው እላታለሁ ።

ለጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ ትተክዝና ፡ «ለኛ፣ እናስባለን ፡ ብለው ፡ በመካከላችን ፡ የገቡ ፡ ገላጋይዎች ፡ ንብረታችንን ፡ አከፋፍለው፣ ሊለያዩን፣ ነው ፡ ልጄ » ትለኛለች ።

አባቴ ፡ ፊት ፡ ቢነሣኝና ፡ ከናቴ ፡ ጋር ፡ አብሬም፣ ብሰደድ ፡ ናፍቆቱ ፡ ግን ፡ አላስቀምጥ ፡ ስላለኝ ፣ ሳልነግራት፣ ሄድኩ። አባቴ ፡ ባየኝ፣ ጊዜ ፡ አቅፎ ፡ ሳመኝ ። እንዲያውም ፡ ዕንባው ፡ እርግፍ ፡ አለ ። የእናቴን ፡ ደኅንነት ፡ ጠየቀኝ ፣ ነገርኩት ።

ለምን ፡ እናቴ ፡ አትመጣም ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ፣ ለአንድ ፡ ደቂቃ ተከዘ ። «የሁለታችን ፡ ጠብ ፡ እስከዚህ ፡ አይደርስም ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ነገር ፡ በእናትህ ፡ ላይ ፡ በመስማቴ ፡ ተበሳጨሁ ። በደም ፡ ፍላት ቁጣ ፡ ተናገርኳት ። ጠባችን ፡ ከሁለታችን ፡ አለፈ ። ሰላም ፡ እናወርዳለን ፡ ብለው ፡ ገብተው ፡ እንዲያው ፡ ሰላማችንን ፡ አሳጡን ። በአንድ ቤት ፡ መቀመጣችሁ ፡ ይቅር ፡ ብለው ፡ ለያዩን ። በመተፋፈር ፡ እንደ ቃላቸው ፡ ሆነ ። በዕለት ፡ ጠብ ፡ ሳንግባባ ፡ ቀርተን ፣ ብንማረርም ፡ ውሎ ፡ ሲያድር ፡ ማናቸውም ፡ ይረሳል ። ለምሳሌ ፡ አሁን ፡ ተፀፅቻለሁ፡ እናትህንም ፡ በድያለሁ ፣ የበደልኩዋትም ፡ የሰው ፡ ነገር ፡ ሰምቼ ፡ በወሬ ፡ ነው ። ርግጥ ፡ ነው ፡ በዕድሜ ፡ እበልጣታለሁ ። ከሽማግሌ ፡ ጋር ፡ ሆኜ ፡ ያለጊዜዬ ፡ ልወድቅ ፡ ነው ፣ እያለች ፡ ትማረራለች ፡ ማለ

ትን ፡ ሰማሁ ። የጥላቻ ፡ ሁኔታ ፡ አሳየችኝ ። የሰማሁትን ፡ ከሁኔታዋ ፡ ጋር ፡ ሳመዛዝን ፣ እውነት ፡ መሰለኝ ። እየተበሳጨሁ ፡ ክፉ ፡ ክፉ ፡ ቃላት ፡ ተናገርኳት ። አሁን ፡ በማስተዋል ፡ ስመለከተው ፡ ተሳስቻለሁ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሰውን ፡ የሚያጣላ ፡ እንጂ ፡ የሚያፋቅር፡ ወዳጅ ፡ የለም፣ እናትህን ፡ ለምነህ ፡ አስታርቀኝ» ፡ እያለ ፡ ለኔ ፡ ገና ፡ በዕድሜ ፡ ልጅ ፡ ለሆንኩት ፡ ልጁ ፡ እንደ ፡ ዐዋቂ ፡ አዋየኝ ።

በአደረገው ፡ ሁሉ ፡ እንደተፀፀተ ፡ ስረዳ ፡ ስሜው ፡ ወደ ፡ እናቴ በሩጫ ፡ ሄድኩ ። ጠፋ ፡ ብላ ፡ ስትጨነቅ ፡ ደረስኩ ።«ወዴት ፡ ሄደህ፡ ነው ፡ ያስጨነከኝ ፡» ብላ ፡ ጠየቀችኝ ። አባቴ ፡ ያለውን ፡ በሙሉ ፡ ነገ ርኩዋት ። «አዬ ፡ የልጅ ፡ ነገር ፡ መቼ ፡ እንደዚህ፡ ይሆናል» ፡ ብላ ፡ የነገርኳትን ፡ ባለማመን ፡ በል ፡ ተወዉ ፡ አለች ።

«እማምዬ» ፡ እያልኩ ፡ ከጫማዋ ፡ ጀምሮ፡ እየሳምኩ ፡ ከልቅሶ ፡ ጋር ፡ ለመንኳት ። «ምን ፡ አድርጊ ፡ ነው ፡ የምትለኝ ፡ ልጄ» ፡ አለችኝ ። ወደ ፡ ቤታችን ፡ እንሂድ ፡ «አልኳት» ። «አዬ ፡ የልጅ ፡ ነገር ፡ ብላ» የፌዝ ፡ ሳቅ ፡ አሁንም ፡ ሳቀች ። ማስቸገሬን ፡ ቀጠልኩ ። ስንጨቃጨቅ ፡ የሚ ወደዱና ፡ የሚታፈሩ ፣ ኑሮዋቸውን ፡ በቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር፡ ግቢ ፡ ያደረጉ ፡ መነኰሲት ፡ ሊጠይቋት ፡ መጡ ።

ሰላምታ ፡ ተለዋወጡ ፡ እኔም ፡ ልመናዬን ፡ ቀጠልኩ ። « ከእን ግዳ ፡ ጋር ፡ አላነጋግረኝ ፡ አልክ»ብላ፡ ተቆጣች ። ቁጣዋን ፡ ቻል ፡ ብዬ ፡ ቀጠልኩ ። መነኰሴዋ ፡ «ልጄ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ይልሻል» ብለው፡ ጠየቁ ዋት ።

የምላትን ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝራ ፡ ነገረቻቸው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ መነኰ ሲቷ ፡ «በልጆች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጸጋ፡ ሰው፡ ሊያውቀው ፡ አይችልም ። መድኃኒታችን ፡ ሕፃናትን ፡ አትከልክሏቸው ፣ ወደኔ ፡ ይምጡ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮላቸዋል ። እግዚአብሔር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ የሚሠ ራው ፡ አይታወቅምና ፣ የሚልሽን ፡ ፈጽሚለት» አልዋት ።

አንገትዋን ፡ ሰበር ፡ አድርጋ ፡ አሰበች ፣ ተክዛች ። « ልጄ ፡ ከዚህ ፡ የቀለለ ፡ ነገር ፡ የለም ። የሚያስተክዝ ፡ አይደለም ። የመጣሁት ፡ አን ችን ፡ ልጠይቅ ፡ ነው ። ሰውና ፡ ሰው ፡ ሲጣላ ፡ በማስታረቅ ፡ ፋንታ ፡ ዛሬ ፡ ማባባስ ፡ ሆንዋል ። እግዚአብሔር ፡ በልጃችሁ ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ በቤታችሁ ፡ ሰላም ፡ ያወርድ ፡ ይሆናል ። ከዕትብትሽ ፡ የተቈረጠ ፡ ለእ ርሱም ፡ ከአብራኩ ፡ የተከፈለ ፡ ከልጅ፡ የቀረበስ፡ ማን፡ አለ!የልጅሽን፡



ፈቃድ ፡ ለመፈጸም ፡ ተነሽ ፡ ወደቤትሽ ፡ ሂጂ ። እኔም ፡ ሳልለይሽ ፡ አብሬ ፡ እሄዳለሁ» አልዋት ፡ መነኰሲቷ ።

የልጅ ፡ ነገር ፡ ታምኖ ፡ እንዴት ፡ ይኬዳል ፡ ብዬ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ስንጨቃጨቅ ፡ መጡ ። ልጄ ፡ ሐሳቡን ፡ ለመፈጸም ፡ ከርስዎ ፡ ጋር ፡ አላነጋግር ፡ በማለቱ ፡ ነገሩን ፡ ሰሙት። የልጄን ፡ ሐሳብ ፡ ደግፈው ፡ ሂጂ ፡ ካሉኝና ፣ ርስዎም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ከሄዱ ፡ መልካም ፡ ነው ፣ « እን ሂድ » አለቻቸውና ፡ ጕዝዋችንን ፡ ቀጠልን ።

የጕዞው ፡ መሪ ፡ ሆኜ ፡ ከቤታችን ፡ ደረስን ። ከዚህ ፡ ዓለም፡ ደስታ ፡ ርቀው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ የሚኖሩ ፡ መሆናቸውን ፡ አባቴ፡ በበለጠ ፡ ያውቅ ፡ ስለነበር ፣ መነኰሲቷን ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ሲያያቸው ፡ ደነ ገጠ ፣ ደስም ፡ አለው ።

ጕልበታቸውን ፡ በመሳም ፡ ሰላምታ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፣ «ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ለፈጠረ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብለሽ ፡ ማሪኝ» ብሎ ፡ ከናቴ ፡ ጫማ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። እናቴም ፡ ደነገጠች ። ከተቀመጠችበት ፡ እመር ፡ ብላ ፡ ቆመች ። መነኰሲቷ «ተይ ፡ ልጄ ፡ የእግዚአብሔርን፡ ስም፡ ጠርቶ፡ ይቅርታ ፡ ለመነሽ። አንቺ ፡ ይቅር ፡ ካላልሽ ፡ አንቺን ፡ ይቅር ፡ የሚልሽ፡ የለም ። ይቅርታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ። መወቃቀስም ፡ አያስፈል ግም፣ ትርፉ፡ እንደዚህ፡ ተባባሉ ፡ ነው ። በሥሩት ፡ መፀፀት ፡ ይገባል ። ንስሐ ፡ እንደመግባት ፡ ይቈጠራል ። ከጫማሽ ፡ ላይ ፡ ወድቆ፡ ይቅርታ ፡ የለመነሽ ፡ በመፀፀቱ ፡ ነው ፣ ይቅር ፡ ባይ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልጃችሁ ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ ይቅር ፡ ስላላችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። እኔም ፡ በመካከላ ችሁ ፡ የተገኘሁት ፡ ለምስክርነት ፡ ነው» ፣ አሉ ።

« የልጄን ፡ ምልጃ ፡ ሳልንቅ ፣ ወደቤቴ ፡ ስመጣ ፡ ይቅር ፡ ብያለሁ ። ባለቤቴ ፡ ከጫማየ ፡ ላይ ፡ ሲወድቁ ፣ አድራጐታቸው ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ሆኖብኝ ፡ ደንግጬ ፡ ተነሣሁ ፡ እንጂ ፣ ይቅርታውን፡ ላለመቀበል ፡ አይ ደለም » ብላ ፡ መለሰች ።

መነኰሲቷ ፡ ቆመው ፣ « በሉ፡ ስለይቅርታ ፡ ተሳሳሙ፡ አልዋቸው» ተሳስመው ፡ ከልብ ፡ ታረቁ ። ከምረቃ ፡ ጋር ፡ ሁሉም ፡ እኔን ፡ ሳሙኝ ።

በቤታችን ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ወረደ ። መነኰሲቷም ፡ ወደ ፡ በዓ ታቸው ፡ ሄዱ ። ሁላችንም ፡ ለመሸኘት ፡ ስንነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ነው ፣ ፍቅር፡ እግዚአብሔር፡ ነው። በፍቅር፡ ተሳሰቡ። እመኝው፡ እመናት ፣ በራሳችሁ ፡ ላይ ፡ ሊያደርጉባችሁ ፡ የማትወዱትን ፡ በሌላው ፡



2*

ሰው ፡ ላይ ፡ አታድርጉ ። ምንም ፡ በቊጥር ፡ ሁለት ፡ ብትሆኑ ፡ በባልና ፡ ሚስትነት ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አድርጓችኋል ። እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ያደረገውን ፡ ሰው ፡ አይለየውም ፡ ተብለዋልና ፣ በመካከላችሁ ፡ ሰው ፡ እንዳይገባ ፡ ተከላከሉ ። በሩ ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ። ዘመናት ፡ ሲያልፉ ፡ ዘመናት ፡ ይተካሉ ። እንደ ፡ ዘመናቱ ፡ መለዋወጥ ፡ የሰው ፡ ጠባይ ፣ ፍላጐትና ፡ ምኞት ፡ ተለዋዋጭ፡ ይሆናል።ለሰው ፡ ደግ ፡ ከማሰብ ፡ ክፉ ፣ ሰውና ፡ ሰው ፡ በፍቅር ፡ ከሚቀራረብ ፡ ቢራራቅ ፣ ሲያምኑት ፡ የሚከዳ ፣ ያላየውን ፡ እንዳየ ፣ ያልሰማውን ፡ እንደሰማ ፣ ከሰው ፡ ይልቅ ፡ ገንዘብ ፡ መውደድ ፣ አባቶችን ፡ ከማክበር ፡ ይልቅ ፡ ማዋረድ ፣ ራስን ፡ ከመውደድ ፡ የተነሣ ፡ የተፈጥሮ ፡ ወንድምን ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ከምግባርና ፡ ከሃይማኖት ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ በዘመናችን ፡ ጐልቶና ፡ ሰፍቶ ፡ ስለሚታይ ፣ በሃይማኖት ፡ ስላምን ፡ ግዝዋት » ብለው ፡ ተሰናበቱንና ፡ ሄዱ ።

ያባቴና ፡ የናቴ ፡ ፍቅር ፡ እንደገና ፡ ታደሰ ። በመካከላቸው ፡ ተፈጥሮ ፡ የነበረው ፡ ሁከት ፡ እንደዚህ ፡ ሊቀር ፣ ወደሰው ፡ ጆሮ ፡ ተላልፎ ፡ መተረቻ ፡ በመሆናቸው ፡ አዘኑ ። ከጠነከረ ፡ ጠብ፡ ላይ፡ የተዳረሱበትን ፡ ምክንያት ፡ ሲጠያየቁ ፣ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ከራሳቸው ፡ የመነጨ ፡ ሳይሆን ፡ ከቤታቸው ፡ ግቢ ፡ ውጭ ፡ ከሆኑ ፡ ከወዳጆቻቸው ፡ የመነጨ፡ ሆኖ፡ ሲያገኙት ፣ ዋጋቸውን ፡ ይከፈላቸው ፡ ብለው፡ ቂም፡ መያዙን ፡ ተዉት።

ስላማዊ ፡ ኑሮዋቸው ፡ እንደገና ፡ ከተመሠረተ ፡ በኋላ ፣ አቋርጬ ፡ የነበረውን ፡ ትምህርት ፡ ቀጠልኩ ። አባትና ፡ እናቴ ፡ እንደ ፡ ዓይን ፡ ብሌናቸው ፡ አድርገው ፡ ጠበቁኝ ። በመካከላቸው ፡ የወረደው ፡ ሰላም ፡ ለኔም፡ የመንፈስ፡ ደኅንነትን ፡ ሰጠኝ ። ሐሳቤን ፡ ሁሉ ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ አጠቃለልኩ ። አባትና ፡ እናቴ ፡ በኔ ፡ ምክንያት ፡ በመታረቃቸውና ፡ እንደገና ፡ በመፋቀራቸው ፡ የልጅ ፡ ሽማግሌው ፡ እየተባልኩ ፡ በመንደራችን ፡ ሰዎች ፡ አፍ ፡ እጠራ ፡ ጀመር ።

# መ ም ህ ር ፡

የዛሬን ፡ ሰባኪ ፡ መምህር ፡ ልሁናችሁ ፣
አፍቅሩ ፡ መሥራትን ፡ በንጹሕ ፡ ልባችሁ ።
ልንገራችሁ ፡ ሰዎች ፡ ስሙኝ ፡ እባካችሁ ፣
ቀርቶ ፡ መለያየት ፡ በኅብረት ፡ ቆማችሁ ።



ኃላፊ ፡ ናት ፡ ዓለም ፡ መልኳም ፡ ረጋፊ ፣
ያለፈ ፡ ነው ፡ ሠርቶ ፣ ጀግናና ፡ አሸናፊ ።
ጠቢባን ፡ ኃያላን ፡ የታወቁ ፡ ሁሉ ፣
በዚች ፡ ዓለም ፡ ትናንት ፡ ነበሩ ፡ በሙሉ ።
የነበረው ፡ ሲሄድ ፣ ያልነበር ፡ ሲመጣ ፣
ተቀባይ ፡ ናት ፡ ዓለም ፡ ሁሉንም ፡ አድፍጣ ።
የቸገረኝ ፡ እኔን ፡ የዓለም ፡ ጠባይ ፡ ነው ፣
ጅማሬው ፡ ማር ፡ ሲሆን ፡ ሬት ፡ ነው ፡ ፍጻሜው ።
ለሚቀረው ፡ እንዲህ ፡ በድንገት ፡ በቅጽበት ፣
ለዚህ ፡ ነወይ ፡ ለካስ ፡ ከዚያም ፡ ከዚያም ፡ ያልኩት ።
እኔ ፡ መቼ ፡ ዐውቄ ፡ የመንገዱን ፡ ማጠር ፣
እያልኩ ፡ ያዝኩት ፣ ያዝኩት ፣ መራመድ ፡ ስጀምር ፣
ሆኖ ፡ ቀረ ፡ ከንቱ ፡ ድካሜ ፡ በጅምር ።
ተረዳሁት ፡ አሁን ፡ ሁሉንም ፡ መርምሬ ፣
መጣሁ ፡ ላገለግል ፡ በሰው ፡ ተፈጥሬ ።
አልሆነም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሳትኩኝ ፡ ዓላማየን ፣
ተቸነፍኩ ፣ ወደቅሁኝ ፣ ላስደሰት ፡ ሥጋዬን ።
የሥጋ ፡ ፍላጎት ፡ የሥጋ ፡ ስሜት ፣
የሚበን ፡ እንደጢስ ፡ የሌለው ፡ ውጤት ።
የተሠራው ፡ ሥጋ ፡ ከአፈር ፡ ላይ ፡ ሆኖና ፣
አድሮ ፡ ሟሙቶ ፡ ያልቃል ፡ የለውም ፡ ትድግና ።
በሕግ ፡ ተፈጥሮ ፡ ባንድዬ ፡ ጥበብ ፣
ልልማ ፡ እንጂ ፡ ሠርቼ ፡ በግንባሬ ፡ ላብ ፣
አልሻም ፡ ከማንም ፡ የዓመፅ ፡ ገንዘብ ።
እያልኩ ፡ ብመኝም ፡ በኔ ፡ ፍልስፍና ፣
አስቈጠረኝ ፡ ከሞኝ ፡ እየነሣኝ ፡ ጤና ።
የማኅበር ፡ ጽዋ ፡ አብሬ ፡ ተሳተፍኩ ፣
ፈጣሪዬ ፡ ማረኝ ፡ መቼም ፡ ማምለጥ ፡ አልቻልኩ ።
ያታለለኝ ፡ እኔን  ልቤን ፡ የማረከው ፣
የማውቀው ፡ ሰው ፡ ትናንት ፡ አንዳችም ፡ የሌለው ፣
ባላወቅሁት ፡ መንገድ ፡ በልጦኝ ፡ ስላየሁ ፡ ነው ።
አብሬ ፡ ልከተል ፡ ልካፈል ፡ ሐሳብ ፣
ግዴታ ፡ አለኝ ፡ እኔም ፡ ለአገርና ፡ ሕዝብ ።
ብዬ ፡ ባስረዳቸው ፡ ሁሉንም ፡ ገልጬ ፣
አጣሁኝ ፡ ተቀባይ ፡ ቀረሁኝ ፡ ተውጬ ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ፡

# ታሪኩ ፡ ታዬ ፡

በመንደር ፡ የሚሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ ፈጸምኩ ። ወደተሻለ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተዛውሬ ፡ ትምህርቴን ፡ ቀጠልኩ ። ከትምህርት ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ በተለይ ፡ ማታና ፡ በዕረፍት ፡ ቀን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ ለአባትና ፡ ለእናቴ ፡ አነብላቸዋለሁ ። ጊዜው ፡ አጭርም ፡ ቢሆን ተፈጥሮ ፡ የነበረውን ፡ ጠብ ፡ ሲያስታውሱት ፡ እየዘገኑናቸው ፡ «ዋ ፡ ሰው ! ለሰው ፡ ሞት ፡ አነሰው» ፡ እያሉ ፡ የቆየ ፡ ተረት ፡ ያነሣሉ ።

«ያለፈው ፡ ትምህርት ፡ ይሁን ፤ በመካከላችን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዳይገባ ፡ እንከላከል ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ልጄን ፡ ልጅነቱን፡ እስከመ ጠራጠር ፡ ደረስኩ ። በዕድሜ ፡ ወጣት ፡ ብትሆኝም ፤ እህል ፡ ውሃ፡ አገ ናኝቶን ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ መውለድ ፡ ደርሰናል። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በበ ኩሌ ፡ አላሳዝንሽም ፤ ቃል ፡ ገብቻለሁ » አለ ። አባቴ ፡ ባለፈው ፡ አድራጐቱ ፡ በመፀፀት ።

የኔን ፡ ወጣትነት ፡ ያንቱን ፡ መካከለኝነት ፡ ዐወቅን ፡ ያሉ ፡ ያለ ፡ ጉዳያቸው ፡ ገብተው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አወሩ ። ይህ ፡ አልበቃቸው ፡ ቢል ፡ ልጅዎን ፡ የሌላ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ አደረጉት ። ከአንቱ ፡ ጋር ፡ የእኔ፡ መኖር ፡ የሚያስከትልብኝን ፡ ጉዳት ፡ አመለከቱኝ ። ምክራቸውን ፡ ትቀብዬ ፡ በአንቱ ፡ ላይ ፡ ያሳየሁት ፡ ለውጥ ፡ ግን ፡ የለም ። በወሬ ፡ ተፈቱ ። ያበሳጩኝ ፡ እርስዎ ፡ ነዎት ። በነገሩ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አን ደነቅበት ። ይህ ፡ የኑሮ ፡ ታሪክ ፡ ነው ። ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ከሌለ ፡ ታሪክም ፡ ሊኖር ፡ አይችልም » ብላ ፡ መለሰችለት ፡ እናቴ ፡ አባቴን ፡ ለማጽናናት ።

በዕድሜና ፡ በአዕምሮ ፡ እያደግሁ ፡ ሄድኩ ። ማናቸውንም ፡ መጽ ሐፍና ፡ ጽሑፍ ፡ የማንበብ ፡ ፍቅር ፡ አደረብኝ ። በጽሕፈትም ፡ ራሴን ቻልኩ ።

አባትና፡ እናቴ ፡ ከሚገባኝ ፡ በላይ ፡ አክብሮት ፡ ሰጡኝ ። አንድ፡ ልጅ ፡ ከመሆኔም ፡ ይልቅ ፡ ፍቅር ፡ ርቆ ፡ ጠብ ፡ ሠልጥና ፡ በነበረበት ፡ ወቅት ፡ ጠብ ፡ ጠፍቶ ፡ ፍቅር ፡ ሊተካ ፡ የቻለው ፡ በኔ ፡ ምክንያት ፡

በመሆኑ ፡ ዘወትር ፡ እያስታወሱ ፡ የሚያሳዩኝ ፡ አክብሮትና ፡ ፍቅር፡ በጣም ፡ የጋለ ፡ ሆነ ። «አባትህንና ፡ እናትህን ፡ አክብር » ፡ የተባለውን ፡ በመከተል ፡ ራሴን ፡ ዝቅ ፡ አድርጌ ፡ እየታዘዝኩ ፡ አገለግላቸዋለሁ ።

በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ በሰላምና ፡ በደስታ ፡ ስንኖር ፡ አባቴን ፡ አልፎ፡ አልፎ ፡ ሕመም ፡ ተሰማው ። ለርሱ ፡ የሚሰማውን ፡ ያህል ፡ ለቤተሰቡ ፡ የሕመሙ ፡ አሥጊነት ፡ እጅግም ፡ አልታወቀም። ይሁን ፡ እንጂ፡ ሕመሙ ፡ ሥር ፡ ሰዶ ፡ ኖሮ ፡ ባላሰብንበት፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ በድንገት ፡ በጠና ፡ ታመመ ። «ከምወድሽ ፡ ባለቤቴና ፡ ከምወድህ ፡ ልጄ፡ በሞት ፡ ስለያችሁ ፡ የሚሰማኝና ፡ የሚሰማችሁ ፡ ኀዘን ፡ የመረረ ፡ ነው ።

በዓዕር ፡ ተይዣለሁ ፤ አንደበቴ ፡ በሞት ፡ ከመዘጋቱ ፡ በፊት ፡ እንደኔ ፡ እስክትሆኑ ፡ ልጄ ፡ እናትህን ፡ ደግፋት፡ ርዳት ። አንቺም ፡ በሚቻልሽ ፡ ሁሉ ፡ አስቢለት ።

የምንተዳደረው ፡ መሬት ፡ ከምትሰጠን፡ ረድኤት ፡ ነው። መሬት፡ ጥቅም ፡ የምትሰጠው ፡ በመኖር ፡ ሳይሆን ፡ በመሥራት ፡ ስለሆነ ፡ የኔን በሞት ፡ መለየት ፡ እያሰላሰላችሁ ፡ የግብርናው ፡ ሥራ ፡ እንዳይዳከም፡ ከሞትኩ ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሥራው ፡ ይቀጥል ፡ እንጂ ፡ የኔን ፡ መለየት ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ከኀዘን ፡ የተነሣ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ እንዳይሞት ።

ያለንን ፡ ሀብት ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞትዋ ፡ እናትህ ፡ የምትተዳደርበት ፡ ነው ። ከርስዋ ፡ በኋላ ፡ ያንተው ፡ ነው ። ትዳር ፡ ብትይዝም ፡ ሀብቱ ፡ በርስዋ ፡ እጅ ፡ እንደሆነ ፡ አንተም ፡ ተረዳበት ፡ እንጂ ፡ ትዳር ፡ ይዛለች ፡ በማለት ፡ ደክማ ፡ የመሠረተችውን ፡ ሀብት ፡ በሕይወት ፡ እያለች ፡ ከእጅዋ ፡ እንዳይወጣ ።

ለአንተ ፡ እናትህ ፤ ለአንቺ ፡ ልጅሽ ፡ ከሁለታችሁ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ለናንተ ፡ የሚያስብ ፡ በኔም ፡ በአንቺም ፡ በኩል ፡ የለም ። እናትና፡ ልጅ ፡ ብትሆኑም ፤ ነገ ፡ ስታገባ ፡ ሚስትህ ፡ አሸንፋህ ፤ ወይም፡ ለውጣህ ፡ እናትህን፡ እንዳትክዳት ፤ እንዳታሳዝናት፡ አደራህን ፡ ልጄ።

አንቺም ፡ እንደኔ ፡ እስክትሆኚ ፡ ትዳር ፡ መያዝ ፡ ግድ ፡ ሆኖብሽ ባለትዳርም ፡ ብትሆኚ ፤ ለልጅሽ ፡ ያለሽ ፡ አስተሳሰብና ፡ ፍቅር ፡ እንዳይለወጥ ፡ አደራ » ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እማኝና ፡ ዳኛ ፡ በማድረግ ፡ የኑዛዜ ፡ ንግግሩን ፡ ለመቀጠል ፡ ሲሞክር ፡ በድንገት፡ ከትራሱ ፡ ዝልስ ፡ አለና ፡ በሞት ፡ ተለየን ።



አንድ ፡ ቃል ፡ ሳንመልስለት ፡ በሞት ፡ ሲለየን ፡ የተሰማንን ፡ ድንጋጤና ፡ መራራ ፡ ኀዘን ፡ አንባቢ ፡ ሊመዝነው ፡ ይችላል ። ፊታችንን ፡ ብንነጭ ፤ ብንወድቅ ፡ ብንነሣ ፤ የማንመልሰውና ፡ የማንቋቋመው ፡ ሆነ ። ወዳጅ ፤ ጐረቤት ፡ የቅርብ ፡ የሩቅ ፡ ዘመድ ፡ ተሰብስቦ ፡ የመቃብሩ ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጸመ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ በኀዘን ፡ ላይ ፡ ከሦስት፡ ቀን ፡ የበለጠ ፡ እንዳንቀመጥ ፡ ሟቹ ፡ ቢያማጥነንም ፤ ሰባት ፡ ቀን፡ በኀዘን ፡ ላይ ፡ ተቀመጥን ። ከሰባት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሥራችንን ፡ ቀጠልን ። የቤቱን ፡ ጣጣ ፤ የወንዱንም ፡ የሴቱንም ፡ እናቴ ፡ ግዴታ ፡ ተሸከመች ። እኔ ፡ ግን ፡ ትምህርቴን ፡ ቀጠልኩ ። ከትምህርት ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ የተሟላ ፡ ርዳታ ፡ ለእናቴ ፡ ማድረጌን ፡ በበለጠ ፡ ቀጠልኩ ።

እናቴ ፡ ሆደ ፡ ባሻ ፡ ሆነች ። ደስታ ፡ ራቃታ ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አልቅሳ ፡ ታስለቅሰኛለች ። ቢሆንም ፡ አጽናናታለሁ ። በርሻ፡ ቦታ ፡ ከገበሬዎቹ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ በመሥራትና ፡ በማሠራት ፡ የሚቈጣጠር ፡ ካለመኖሩ ፡ የተነሣ ፤ የግብርናው ፡ ውጤት ፡ አባቴ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ይገኝ ፡ ከነበረው ፡ ሩቡን ፡ ያህል ፡ ቀነሰ ። እናቴ ፡ የባሰ ፡ አዘነች ። «በአንድ ፡ ዓመት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ያጐደለ ፡ በሚቀጥለው ፡ ጊዜ ፡ የባሰ ፡ ይሆናል» ፡ አለች ። እኔም ፡ ነገሩን፡ ባመዛዝነው፡ የወደፊቱ ፡ ተስፋ ፡ የመነመነ ፡ ሆኖ ፡ ታየኝ ። ትምህርቴን ፡ ትቼ ፤ በአባቴ ፡ እግር ፡ ተተክቼ ፡ እያሳረስኩ ፤ የእናቴን ፡ ቅሬታ ፡ ከፊቷ ፡ ማጥፋት ፡ አለብኝ ፡ ብዬ ፡ ቆረጥሁ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሐሳቤን ፡ በሙሉ ፡ ለናቴ ፡ ነገርኳት፤ እናቴ ፡ እያለቀሰች ፡ በመቃወም ፤ ምን ፡ በወጣህ ፡ የጀመርከውን ፡ ትምህርት ፡ ጨርስ ፤ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ሥራውን ፡ እኔ ፡ እከታተለዋለሁ ፡ አለችኝ ። የእናትነት ፡ አንጀቷ ፡ በርኅራኄ ፡ መላወሱን ፡ የፊቷ ፡ ሁኔታ ፡ ይናገር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሐሳቤ ፡ ወደግብርና ፡ ሥራ ፡ ስለአዘነበለ ፤ ትምህርቴን ፡ ልከታተል ፡ አልችልም ፤ ብዬ ፡ እጭር ፡ መልስ ፡ ሰጠኋት ። ርስዋም ፡ ቆርጬ ፡ እንደተነሣሁ ፡ ስታውቅ ፤ «መልካም ፡ ነው ፡ እንዳልከው ፡ ይሁን» ፡ አለችኝ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ አቅሜ ፡ እርፍ ፡ ለመለወጥ ፡ ባይችል ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የግብርናን ፡ ሥራ ፡ እከታተል ፡ ስለነበር ፤ ሥራዬን ፡ ቀጠልኩ ። ይልቁንም ፡ ስለግብርና ፡ የተጻፉ ፡ መጻሕፍት ፡ እየፈለግሁ ፡ በማንበቤ ፡ ከነበረኝ ፡ ልማድ ፡ ጋር ፡ በመጻሕፍት ፡ ያገኘሁትን ፡ በማጣመር ፡ የግብርና ፡ ሥራዬን ፡ አሟልቼ ፡ በየዓመቱ ፡ አባቴ ፡ ያገኝ ፡ ከነበረው ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ አስገኘሁ ። እናቴ ፡ ደስ አላት ። ሞቷን ፡ ከኔ ፡ ሞት ፡ በፊት ፡ እንዲያደርግላት ፡ የዘወትር ፡ ጸሎቷ ፡ ሆነ ።

አባቴ ፡ በሞት ፡ ከመካከላችን ፡ ከመለየቱ ፡ በቀር ፤ በግብርናና ፡ በሌላውም ፡ መጠነኛ ፡ ንግድ ፡ ደኅና ፡ ገቢ ፡ በማግኘታችን ፡ ቤታችን ፡ የተሟላ ፡ ሆነ ። ቢሆንም ፡ እኔም ፡ አባቴን ፤ እናቴም ፡ ባሏን ፡ በማጣታችን ፡ ያገኘነውና ፡ የምናገኘው ፡ ደስታ ፡ ጐደሎነቱ ፡ እጅግ ፡ አድርጐ ፡ ሲሰማን ፡ ቆየ ።

በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ሳለን ፤ አባቴ ፡ ከሞተ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሆነው ። በአዕምሮም ፡ በአካልም ፡ ጐለመስኩ ፤ እናቴ ፡ እኔን ፡ ትዳር ፡ ለማስያዝ ፡ ውሳኔ ፡ አድርጋ ፤ ሐሳብዋን ፡ አካፈለችኝ ። « ያለ ፡ ትዳር ፡ መኖር ፡ ርግጥ ፡ አልችልም ። መያዝ ፡ ይኖርብኝ ፡ ይሆናል ። ዳሩ ፡ ግን ፤ ሚስት ፡ ሳገባ ፡ በአንቺ ፡ በእናቴ ፡ ላይ ፡ ያለኝ ፡ አስተሳሰብና ፡ አስተያየት ፡ ይለወጥ ፡ ይሆናል ፤ ወይም ፡ ሚስቴ ፡ ትጠላሽና ፡ «ሴት ፡ የላከው ፡ ሞት ፡ አይፈራም » ፡ እንደተባለው ፡ በሚስቴ ፡ ተመርቼ ፡ አሳዝንሽ ፡ ይሆናል ። ጊዜ ፡ የሚያመጣውን ፡ ጊዜ ፡ ይወቅ ፡ እንጂ ፤ እኔ ፡ እንደዚህ ፡ ነኝ ፤ አላደርግም ፡ ማለት ፡ ከንቱ ፡ ስለሆነ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ መቆየት ፡ አለብኝ » ፡ አልኩዋት ።

«ያንተ ፡ ትዳር ፡ አንተን ፡ የሚያስደስት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ ከቶ ልጄ ፡ ለኔ ፡ አታስብ ። እኔ ፡ አንድ ፡ ራሴን ፡ ነኝ ። አንተ ፡ ደኅና ፡ ትዳር ፡ ይዘህ ፡ ከተቋቋምክ ፤ የኔ ፡ «ዕዳው ፡ ገብስ ፡ ነው» ፡ እንደተባለው ፡ እንደ ፡ አባትህ ፡ እስከ ፡ ጠራኝ ፡ ድረስ ፤ ወደ ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ሄጄ ፤ በአንድ ፡ ልብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ እኖራለሁ ፡ ብላ ፡ መለሰችልኝ ።

በዚህ ፡ መልስዋ ፡ ልቤ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ስለተነካ ፤ አዘንኩና ፡ በሕይወት ፡ እያለሁ ፡ አንቺ ፡ ከኔ ፡ ተለይተሽ ፡ ባልሆነ ፡ ሥፍራ ፡ አትወድቂም ። ባይሆን ፡ እኔ ፡ ያለትዳር ፡ ሕይወቴን ፡ አሳልፋለሁ ፡



እንጂ ፡ ትዳር ፡ ከያዝኩ ፡ እኔም ፡ ባላስቀይምሽ ፤ ሚስቴ ፡ እንደምታስቀይምሽ ፡ እመኝ ። ርስዋ ፡ ከአስቀየመችሽ ፡ እኔ ፡ እንዳስቀየምኩሽ ፡ ይቈጠራል ። እኔም ፡ በሰላምና ፡ በፍቅር ፡ ልኖር ፡ አልችልም ። አባቴን ፡ በማጣታችን ፡ ደስታችን ፡ ጐድሎ ፡ እንደሰቀ ፡ እንጂ ፤ ቤታችን ፡ የበለጠ ፡ በረከት ፡ አግኝቷል ። ባባቴ ፡ መለየት ፡ እንዘን ፡ እንጂ ፡ በሰላምና ፡ በፍቅር ፡ እነሆ ፡ እንኖራለን ፡ ብዬ ፡ መለስኩላት ።

እኔ ፡ ለናቴ ፤ ርስዋ ፡ ለኔ ፡ በመተሳሰብ ፡ ባደረግነው ፡ የሐሳብ ፡ ልውውጥ ፤ ሳንግባባ ፡ ብዙ ፡ ከተነጋገርን ፡ በኋላ ፤ በአንድ ፡ ቀን ፡ የምንወስነውና ፤ ወደስምምነት ፡ የምንደርስበት ፡ ባለመሆኑ ፤ አንተም ፡ አስብበት ፤ እኔም ፡ ላስብበት ፤ ተባብለን ፡ ንግግራችንን ፡ አቆምን ።

ይህን ፡ በተነጋገርን ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፤ ያልተጠበቀና ፡ ያልታሰበ ፡ እናቴን ፡ በሚስትነት ፡ የፈለጋት ፡ ሰው ፡ ኖሮ ፡ መልእክተኞች ፡ ወደቤታችን ፡ መጡ ። አባቴ ፡ ከሞተ ፡ ጀምሮ ፡ የቅርብ ፡ ጐረቤትና ፡ ወዳጆችን ፡ የሆኑ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፤ እልፎ ፡ አልፎ ፡ እየመጡ ፡ ከመጠየቃቸው ፡ በቀር ፤ ከዓመት ፡ በኋላ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ ጠይቆን ፡ አያውቅም ። እንዲያውም ፡ እነዚህ ፡ መጥተው ፡ አያውቁም ። ዛሬ ፡ ለምን ፡ መጡ ፡ ብዬ ፡ አሰብኩ ።

ከቤት ፡ ገብተው ፡ ጥቂት ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፤ ከናቴ ፡ ጋር ፡ የሚነጋገሩበት ፡ ልዩ ፡ ጉዳይ ፡ እንዳላቸው ፡ ገልጠው ፤ ወጣ ፡ እንድልላቸው ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ተናገረ ።

ሐሳባቸውንም ፡ ከመናገራቸው ፡ በፊት ፡ የመጡበት ፡ ጉዳይ ፡ እንዴት ፡ እንደገባት ፡ አይታወቅም ፤ «ከልጄ ፡ የተሰወረ ፡ ጉዳይ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ስለሌላችሁ ፤ ልጄ ፡ የምትሉትን ፡ መስማት ፡ አለበት ፡ » ብላ ፡ ጠንከር ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ ሰጠቻቸው ።

በንግግር ፡ አለመግባባት ፡ «ርሱ ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ልጅ ፡ የሚሰማው ፡ አይደለም ፤ ቢያስፈልግም ፡ በኋላ ፡ ይሰማል» ብለው ፡ መለሱላት ።

«ርግጥ ፡ በዕድሜ ፡ ልጅ ፡ ነው ። በአዕምሮ ፡ ግን ፡ ከኛ ፡ የበለጠ ፡ የሚያስብና ፡ የሚያስተውል ፡ ስለሆነ ፤ የመጣችሁበትን ፡ ጉዳይ ፡ ከኔ ጋር ፡ ሆኖ ፡ መስማት ፡ አለበት ።

ርሱ ፡ እንዲሰማ ፡ ካልፈለጋችሁ ፡ ጊዜያችሁንና ፡ ጊዜያችንን ፡ ሳታባክኑ ፡ ብትሔዱ ፡ ይሻላል» ብላ ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቆርጥ ፡ መልስ ፡ ሰጠቻቸው ።

ያልጠበቁት ፡ ነገር ፡ ስላጋጠማቸው ፡ ይታያዩ ፡ ጀመር ። እኔ ፡ ወደ ፡ ጓዳ ፡ ገባ ፡ ብዬ ፡ መጠጥ፡ አዘዝኩና ፡ ቀረበላቸው ። «ምኑን ፡ ጠጣነው ፡ የመጣንበትን ፡ ጉዳይ፡ ሳንነጋገር »አሉ ። « መጠጡ፡ ንግግር ፡ አይከለክል ፤ መነጋገር ፡ ትችላላችሁ ፡ ጠጡ» ብዬ ፡ ስጋብዛቸው ፡ እናቴ ፡ የተቆጣች ፡ አንበሳ ፡መስላ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ታዳምጣለች ።

ከተመካከሩ ፡ በኋላ ፤ «ጋብቻ ፡ የሚፈርሰው ፤ ወንዱ ፡ ወይም ፡ ሴትዋ ፡ በሞት ፡ ሲለዩ ፡ እንጂ ፤በሕይወት ፡ ካሉ ፡ ጋብቻ ፡ ማፍረስ ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። በሞት ፡ ብትለይ፤ ወይም ፡ ቢለይ ፤ መዋዕለ ፡ ኀዘኑና ፤ ኀዘንዋ ፡ ካለቀ፡ ሴትዋ፡ ወይም፡ ወንዱ ፡ እንዲያገቡ ፡ የተፈቀደ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ሥርዓትና ፡ ሕግ ፡ ነው።

በቅርብ ፡ የሚያውቁትና፡ የሚያውቅዎት ፡ አቶ ፡ ታሪኩ ፡ ታዬ ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛነትዎን ፡ ፈልጐ፡ ስለላከን ፤ ልመናችን ፡ ሞገስ ፡ አግኝቶ ፡ ፈቃድዎን ፡ ቢገልጹልን ፡ እናመሰግናለን ፡ » ብሎ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ተናገረ ።

እናቴም ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳትሰጥ፡ በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ አለቀሰች ። መልእክተኞቹ ፡ ደነገጡ ። እማማዬ፡ እያልኩ ፡ ባጽናናትም ፤ እንዲያውም ፡ ባሰባት ፤ እየተንጐራደደች፡ አለቀሰች። መልእክተኞቹ፡ ብርቱ ፡ ድንጋጤ ፡ ይታይባቸው ፡ ጀመር ።

ብስጭትዋን ፡ በልቅሶ ፡ ካሳለፈች ፡ በኋላ ፤ ረጋ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፤ «ወንድሞቼ ፡ ይቅርታ ፡ አድርጉልኝ ፤ ለጠየቃችሁኝ ፡ መልስ ፡ ሳልሰጣችሁ ፡ ልቅሶዬን ፡ ያስቀደምኩት ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ከንቱ ፡ መሆኑ ፡ አሳዝኖኝ ፤ ሰው ፡ መሆኔን ፡ ጠልቼ ፡ ነው ።

እናንተን ፡ የላካችሁ ፡ ሰው ፤ ሰው ፡ ያላደረገውን ፡ ሥራ፡ አልሠራም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ልቤ ፡ በኀዘን ፡ ተነክቶ ፡ ያለቀስኩት ፡ አቶ ፡ ታሪኩ ፡ ታዬ ፡ በቤታችን ፡ ገቢ ፡ ወጪ ፤ የሚቼ ፡ባለቤቴ ፡ ልዩ ፡ የቅርብ ፡ ወዳጅና ፡ ጓደኛ ፤ የሐሳብና ፡ የምሥጢር ፡ ቴካፋዩ ፡ ነበር ።

ባላሰብነው ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ በሞት ፡ ስንለያይ ፡ ሁሉም ፡ ሊቀር ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት ፡ በኔና ፡ በሚቼ ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ ጠፍቶ ፡ ነበር ። አቶ ፡ ታሪኩ ፡ ታዬ ፡ ገላጋይና ፡ አስታራቂ ፡ መስሎ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ለርሱም ፡ ሆነ ፡ ለሌሎች ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደየልቦ



ናቸው ፡ ዋጋቸውን ፡ ይክፈላቸው ፡ ብለን ፤ ነገሩን ፡ ተውነው ። በእኔ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሐሳብ ፡ ካለው ፡ ሚቼ፡ በሕይወት ፡ በነበረበት ፡ ወቅት ፡ ቤተሰብ ፡ ሆኖ ፡ የምንለያይበትን ፡ ዘዴ ፡ እየሠራ፤ ይልቁንም፡ በአንድ ፡ ቤት ፡ አብራችሁ ፡ ከተቀመጣችሁ ፡ በደም፡ ፍላት፡ ከመጥፎ፡ ሁኔታ ፡ ላይ፡ ትደርሳላችሁ፤ ብሎ፡ ከቤቴ፡ ወደ፡ ሌላ ፡ ለጥቂት ፡ ቀናት፡ ከልጄ ፡ ጋር ፡ እንድሰደድ ፡ ያደረገው ፡ ለካስ ፡ ይህን ፡ አስቦ ፡ ነው ! «ሴት፡ ልብ ፡ የላትም»፡ እንደተባለው፤ ሴት፡ አዳሪ ፡ ስሆንለት፡ አሁን፡ ለላካችሁ ፡ ዓላማው ፡ ማዘጋጀቱ ፡ ኑሯል ፡ ለካ ። አሁን፡ ገባኝ ፤ ሐሳቡንና ፡ ሥራውን ፡ ጊዜ ፡ ገለጠው ።

ወንድሞቼ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ፡ ከባሌ ፡ ጋር፡ በኖርኩ ፤ ከርሱ ፡ ከቀረ ፡ የሚያውቁትን ፡ መልሶና፡ መላልሶ ፡ ቢያደርጉት ፡ ውጤቱ ፡ ያው ፡ ነው ። አቶ ፡ ታሪኩ፡ ታዬ ፡ ከሚቼ ፡ ጋር ፡ የነበረውን ፡ ወዳጅነት ፡ ረስቶት ፡ እኔን ፡ በሚስትነት ፡ በመመኘቱ፡ይቅር፡ ይበለው ። መስሎት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ርሱም ፡ ሚች ፡ ነው። የኔ ፡ ትዳር፡ አብሮ ፡ ከባሌ ፡ ጋር ፡ ስለተቀበረ ፤ ከጐኑ ፡ ሔጄ ፡ እስካርፍ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ባል ፡ የለኝም ፤ ደግሞስ፡ ለሚወዱት፡ ሰው ፡ የኀዘን ፡ ጊዜ፡ ለመወሰን ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ? ብላ ፡ መለሰችላቸው ።

በአነጋገርዋና ፡ በጠቅላላ ፡ ሁኔታዋ ፤ ይልቁንም፡ አቶ ፡ ታሪኩ ፡ ታዬ ፡ ሲልካቸው ፡ ከሚቼ ፡ ጋር ፡ የነበረውን ፡ የቅርብ ፡ ወዳጅነትና ፡ ፍቅር ፡ ሸሽጐ ፤ በመካከላቸው ፡ ጣልቃ ፡ ገብቶ ፡ የሠራውንም ፡ አስቀድሞ ፡ የማያውቁ ፡ ስለሆነ ፤ ስሜታቸው ፡ ተነክቶ ፤ «እኅታችን፡ ሆይ፡ በንግግርዎ ፡ ልባችን ፡ ተነክትዋል ። ካቶ ፡ ታሪኩ ፡ ታዬ፡ጋር፡ እስከ፡ ዚህ ፡ ቅርብ ፡ ወዳጅ ፡ መሆናችሁንና ፡ በትዳራችሁ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የሠራውን ፡ አናውቅም ። የሚጠቅምዎንና ፡ የሚያዋጣዎን፡ ከራስዎ ፡ የበለጠ ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ። የሁላችንም ፡ ጉዞ ፡ በሞት ጐዳና ፡ ላይ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። በቤታችሁ ፡ ገቢ ፡ ወጪ ፡ ሆኖ ፡ በወዳጅነት ፡ በአንድ ፡ ገበታ ፡ በልቶ ፤ ርስዎን ፡ በሚስትነት ፡ መመኘቱ ፤ ሲያሳዝነን ፡ የማናውቀውንም ፡ ሰማን ። ስለዚህ ፡ የልቦናዎን ፡ ሐሳብና ፡ ምኞት ፡ ይፈጽምልዎ» ብለው ፡ ተሰናብተው ፡ ሔዱ ።

በአክብሮት ፡ ሰዎቹን ፡ ከሸኘች ፡ በኋላ ፡ በትካዜ ፤ «አዬ፡ ሰው ፤ ለሰው ፡ ሞት ፡ አነሰው» የተባለው ፡ ለካ ፡ እውነተኛ ፡ አባባል፡ ነው ። ትናንት፡ ያንተ ፡ አባት ፡ ሞተው ፡ ቅርብ ፡ ወዳጅ ፡ ጠባያቸውን፡ ሁሉ፡

ለውጦ ፡ ያበጣበጠን ፤ ያንተን ፡ ልጅነት ፡ ያጠራጠረ ፡ ታሪኩ ፡ ታዬ ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ እንድሆነው ፡ ይጠይቀኝ ። ከወንድ ፡ እርሱ ፤ ከሴት፡እኔ፡ ብቻ ፡ ብንቀር ፤ ርሱን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የማገባው ? ምን ፡ ያድርግ ፤ ሞት ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ ያስጠቃል ። የሰው ፡ ገመና ፡ ይገልጣል ። እናት ፡ ስም ፡ ማውጣት ፡ ታውቃለች ። እውነትም ፡ ታሪክ፡ የሌለው ፡ ምግባረ ፡ ቢስ፡ ነው» አለች ፤ የውስጥ ፡ ስሜቷ ፡ በፊቷ ፡ እስኪነበብ ፡ እየተትከነከነች።

«እማማ ፡ አባቴ ፡ ከሞተ ፡ ሦስተኛ ፡ ዓመት ፡ ሆነ ፤ ዘወትር ፡ ርሱን በማስታወስ ፡ እያዘንሽ ፡ ራስሽን ፡ ጐዳሽ ። ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖረው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ይቅርታ ፡ አድርገሽልኝ ፡ ባል ፡ ብታገቢ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር። ይህን ፡ ስል ፡ አቶ ፡ ታሪኩ ፡ ታዬን፡ አግቢ ፡ ማለቴ፡ አይደለም ። ርሱ ፡ ያልሆነ ፡ የሆነውን ፡ አውርቶ ፡ እናንተን ፡ አለያይቶ፤ እንቺን ፡ የማግባት ፡ እቅድ ፡ እንዳለው ፡ አሁን ፡ ራሱ ፡ መሰከረ ። ሌላ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ብታገቢ ፡ ደግ ፡ ይመስለኛል» ፡ አልኩዋት ።

«አባትህ ፡ የሞት ፡ ጽዋቸውን ፡ ተቀብለው ፡ በሞት ፡ ቢቀድሙ ፤ ነገ ፡ በተራችን ፡ እንከተላቸዋለን ። እንሄዳለን ፡ እንጂ ፤ እሳቸው ፡ እንደ ማይመጡ ፡ ዐውቃለሁ ። ባል ፡ አላገባም ፡ ስል ፡ አባትህን ፡ በዚህ ፡ እጠቅማቸዋለሁ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ። አግብቼ ፡ ምን ፡ ላገኝ ፤ ባላገባስ ፡ ምን ፡ ይቀርብኛል ። እንዲያውም ፡ ከማግባት ፡ አለማግባት ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ተናግሯል ። እያሉ ፡ በድንግልናዬ ፡ የንስሐ አባቴ ፡ የነገሩኝ ፡ አይረሳኝም ። ሰው ፡ ወደማያውቀው ፡ ዓለም ፡ ይሄ ዳል ፡ እንጂ ፤ ወደሚያውቀው ፡ አይመለስም ። ባል ፡ አግብቼ ፡ ከባል ፡ ጋር ፡ ኖሬ ፡ ሁሉንም ፡ አይቼዋለሁ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ያለባል ፡ በንጽ ሕና ፡ መኖርን ፡ መርጫለሁ ።

በመንደር ፡ መኖር ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያሳያል ። ወደፊትም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያስከትላል ። ወደቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ ብቀመጥ ፡ እታፈራለሁ ። ሆኖም ፡ አንተ ፡ አንድ ፡ ልጄ፡ ትዳር ፡ ሳትይዝ ፡ ጥዬህ ፡ መሔድ ፡ ባለመቻሌ ፡ ከዚህ ፡ እኖራለሁ ።

ከተነጋገርን ፤ ልጄ ፡ እባክህን ፡ ትዳር ፡ ያዝ ። ትዳር ፡ መያዝ ፡ የሚያምረው ፡ ባንተ ፡ ነው ። ገና ፡ ወጣት ፡ ነህ ፤ ፈቃድህ ፡ ሆኖ ፡ አንተ ትዳር ፡ ብትይዝልኝ ፤ እኔ ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠጋ ፡ ብዬ ፡ እቀ



መጣለሁ ።የሚያስፈልገኝን ፡ ሁሉ ፡ትረዳኛለህ፤ ሚስቴ ፡ ታስቀይምሽ ፡ ይሆናል ፤ ወይም ፡ እኔ ፡ እለወጥና ፡ አሳዝንሽ ፡ ይሆናል ፡ ያልከውን ፡ ርሳው ።

ልጄ ፡ እኔ ፡ የምጠብቅ ፡ ያንተን ፡ ትዳር ፡ መያዝ ፡ እንጂ ፡ ትዳር፡ ከያዝክ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ አብሬም ፡ ሆነ ፤ ወይም ፡ በተለይ ፡ ከመኖር ፡ ከቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ለመኖር ፡ ምርጫ ፡ እንዳለኝ ፡ ቀደም ፡ አድርጌ ፡ ገልጬልሃለሁ ።

ልጄ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የምፈልገው ፡ ደስታ ፡ እንደሌለ ፡ ዕወቅ ልኝ ። የምጠብቀው ፡ ደስታ ፡ አንተ፡ ትዳር ፡ ይዘህ ፤ ከአብራክ ፡ ሥጋህ፡ የተከፈሉ ፡ ልጆች ፡ ባይ፡ ታላቅ ፡ ደስታዬ ፡ ነው ። ይህም ፡ የሚሆነው፡ ሐሳቤን ፡ ተቀብለህ ፡ ትዳር ፡ የያዝክ ፡ እንደሆነ ፡ ነው።ፈቃድህ ፡ ሆኖ፡ መልካም ፡ ቤተሰብ ፡ ያሳደጋት ፡ እንፈልግ ፤ እንፈላለግ ፡ ብላ ፡ አለ ችኝ ። »

እናቴ ፡ ለተነሣችበት ፡ አሳብ ፡ ፍጹም ፡ ቆራጥ ፡ መሆንዋን ፡ ስለ ማውቅ ፤ ሌላ ፡ መልስ ፡ ልሰጣት ፡ አልወደድሁም ። «ላስብበት ፤ አስቢ በት ፡ ብላት ፡» በበኩሌ ፡ ካሰብኩበት ፡ ቆይቻለሁ ። አንተ ፡ አስብበት፡ ብላኝ ፡ ንግግራችንን ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ አሳደርነው ።

# መ ን ገ ደ ኛ ፡

አንዱ ፡ መንገደኛ ፡ ሌላው ፡ ሽኝ ፡ ነው ፤
በማግስቱ ፡ ደግሞ ፡ ተከታይ ፡ ሌላው ።

ግብዙ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በመከዳት ፡ ወንድሙን ፤
ይረሳና ፡ ይህን ፡ ይመኛል ፡ ንብረቱን ፤
ተሳክቶ ፡ ሐሳቡ ፡ ይወርሳታል ፡ ሚስቱን ።

ይኖራሉ ፡ አብረው ፡ ያለፈው ፡ ተረስቶ ፤
ያረካል ፡ ሥጋውን ፡ በዚህ ፡ ተደስቶ ።

ወቃሽ ፡ ነው ፡ ሕሊና ፡ እውነተኛ ፡ ዳኛ ፤
ይነሳል ፡ ፀጥታ ፡ እንቅልፍ ፡ አያስተኛ ።

ይባንናል ፡ ዘወትር ፡ ይነቃል ፡ ሌሊት ፤
ያየዋል ፡ በሐሳብ ፡ በግሩም ፡ ትንግርት ፤
ይሰማዋል ፡ ሐፍረት ፡ በሥራው ፡ ድርጊት ።

በቀረብኝ ፡ ምነው ፡ ባልገባሁ ፡ አበሳ ፤
እንቅልፍ ፡ የሚያሳጣ ፡ ሰላም ፡ የሚነሳ ፤
ወቀሰኝ ፤ ከሰሰኝ ፤ ያበላኝ ፡ ሳይሳሳ ።

በፃዕር ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲያደርግ ፡ ኑዛዜ ፤
ቃል ፡ ተቀባይ ፡ ነበርኩ ፤ በኀዘን ፡ ትካዜ ።

በሰጠው ፡ ኑዛዜ ፡ በንብረት ፡ ቈጠራ ፤
የንብረት ፡ ጠባቂ ፡ ነበርኩ ፡ ባላደራ ፤
አደራዬን ፡ ጥዬ ፡ በሠራሁት ፡ ሥራ ፤
መንፈስ ፡ የሚያሸብር ፤ ልብን ፡ የሚያስጨንቅ ፡ አገኘኝ ፡ መከራ ።

ወንድ ፡ ጠያቂ ፡ ነው ፡ የለውም ፡ ይሉኝታ ፤
ተው ፡ ብላኝ ፡ ነበረ ፡ አጥብቃ ፡ ወትውታ ፤
አሸነፍኳት ፡ እንጂ ፡ በብዙ ፡ ሐተታ ።

በዚህ ፡ ነገር ፡ አሁን ፤ በዚህ ፡ የተነሣ ፤
በማን ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የሚያርፍ ፡ ወቀሳ ፡ ከሰሳ ።

እፈርዳለሁ ፡ እኔው ፤ እኔው ፡ ዳኛ ፡ ሆኜ ፤
ፍርዴን ፡ ልቀበለው ፤ ጥፋቴን ፡ አምኜ ።

ያመነ ፡ ጥፋቱን ፡ ፀፀት ፡ የገባው ፤
ያገኛል ፡ ሥርየትን ፡ እስከ ፡ ወዲያኛው ።

ሰዎች ፡ ወስፌ ፡ አቅራቢ ፤ ዓለም ፡ ቁና ፡ ሰፊ ፤
የደም ፡ ዘመን ፡ ሆንዋል ፡ ሰላም ፡ ተሸናፊ ።

ያለም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ተማሩ ፡ ትምህርት ፡
ሰላምን ፡ የሚያወርድ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረት ።



## ክ ፍ ል ፡ ፫ ፡

# አቻ ፡ ጋብቻ ፡

የናቴ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፤ የተፈጥሮ ፡ አቅዋሟና ፡ ውበትዋ ፤ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ያላት ፡ ባልትና ፡ በብዙዎች ፡ ዘንድ ፡ ይታወቃል ። ሐሳብዋን ፡ ያላወቁ ፡ ሊጋብቻ ፡ ፈልገዋት ፤ መልክተኞች ፡ ወደቤታችን ፡ ይመጣሉ ። እናቴ ፡ ተበሳጨች ። «የሚመጣውን ፡ ማናቸውንም ፡ እንዳመጣጡ ፡ እየተቀበልሽ ፡ መልስ ፡ ስጪ ፤ በብስጭትና ፡ በማልቀስ ፡ ከግምት ፡ ላይ ፡ አትውደቂ ፡ » ብዬ ፡ በቅድሚያ ፡ ምክር ፡ አካፈልኩዋት ።

ከአክብሮት ፡ ጋር ፡ ቃሌን ፡ ስለምትሰማ ፤ «እውነትህን ፡ ነው ፡ ልጄ» ፡ ብላ ፡ ምክሬን ፡ ተቀበለች ። ለመጡት ፡ መልእክተኞች ፡ ጥያቄ ውን ፡ እንደማትቀበለው ፡ አስረድታ ፡ አሰናበተቻቸው ። በመጨረሻም ፡ የመጡት ፡ መልእክተኞች ፡ በተለይ ፤ እናትህን ፡ በኑሮ ፡ ጓደኛነት ፡ ብዙዎች ፡ ሲፈልግዋት ፤ የሚቀርብላትን ፡ ጥያቄ ፡ ሳትቀበል ፤ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ እንደመለሰች ፡ ሰምተናል ። አንተን ፡ በመፍራት ፡ ይሆናል ፡ ለምን ፡ አታደፋፍራትም ፡ ብለው ፡ አሉኝ ።

ያደረግሁትን ፡ ጥረት ፡ አስረዳኋቸው ። በሀገሩ ፡ ውስጥ ፡ በባላባ ትነት ፡ የታወቀ ፤ በአቋምና ፡ በውበት ፡ ሰውን ፡ የሚማርክ ፤ ሀብቱ ፡ እስከዚህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ምጣኔ ፡ የሌለው ፡ እንደላካቸው ፡ ገለጡልኝ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ተልካችሁ ፡ የመጣችሁ ፡ ስለሆነ ፡ እነጋግርዋት ፡ አል ኳቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደቤት ፡ ገብቼ ፡ እማማ ፡ እንግዶች ፡ ይፈልጉሻል ፡ አልኩዋት ፤ ያው ፡ የባል ፡ ጉዳይ ፡ መሆኑ ፡ ገባችና ፡ ከዚህ ፡ ችግር ፡ ላይ የጣልከኝ ፡ ልጄ ፡ አንተ ፡ ነህ ። በውነት ፡ ብታዝንልኝ ፤ ሐሳቤን ፡ ፈጽ መህ ፡ ትዳር ፡ ብትይዝ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ሊያገኘኝ ፡ ስለማይችል ከችግር ፡ እድን ፡ ነበር ፡ ብላ ፡ እንግዶቹን ፡ ተቀበለች ።

መልክተኞቹ ፡ የላካቸውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በመጥራት ፡ እጅግ ፡ አጋ ንነው ፤ በኑሮ ፡ ጓደኛነት ፡ እንደፈለጋት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ታሪክ ፡ ጠቀስ ምሳሌ ፡ ጋር ፡ ነገርዋት ።

በመሠረቱ ፡ የጋብቻ ፡ ሐሳብ ፡ ስለሌለኝ ፤ ጥያቄያችሁን ፡ አልቀበልም ። በሰፊው ፡ ዘርዝራችሁ ፡ ያስረዳችሁኝን ፡ በአጭር ፡ በመመለሴ ፡ ይቅርታ፡ አድርጉልኝ ፡ ሁለተኛ ፡ ስለዚህ፡ ጉዳይ ፡ ባታነሡብኝ ፡ እወዳለሁ ፤ ብላ ፡ አሰናበተቻቸው ።

እንግዶቹ ፡ ከቅጥር ፡ ግቢው ፡ እስኪወጡ ፡ ተከትዬ ፡ ሸኘኋቸው። ኃይለኛ ፡ እናት ፡ አለችህ ። ከፊትዋ ፡ ቆሞ ፡ መናገር ፡ ያስፈራል ። የላከን ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ ርሱ ፡ ለምኖ ፡ ተለምኖ ፡ ዘመድ ፡ የሚያደርጉት ነው ። በል ፡ መቼም ፡ አላደላችሁም ፡ ብለው ፡ ሄዱ ።

ወደቤት ፡ ስገባ ፡ ተከዛ ፡ አገኘኋት ፤ እማማ ፡ ምነው ፡ ተከዝሽ ፡ አልኳት ። እኔ ፡ ያልተከዝኩ ፤ ማን፡ ይተክዝ ፤ ቀርጮ፡ የተነሣሁበትን፡ ዓላማ ፡ ከግቡ ፡ እንዳላደርስ ፤ አንተ ፡ ሐሳቤን፡ አልቀበለኝ ፡ አልክ ። በየጊዜው ፡ ሰው ፡ እየመጣ ፡ አስቸገረኝ ። ብዙ ፡ ሰው ፡ አስቀየምኩ ። ከብዙ ፡ ሰው ፡ አንደበት ፡ ገባሁ ።

የላኩቸውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ቀደም ፡ አድርጌ ፡ እሰማለሁ ። ሀብታም መሆኑም ፡ ይነገራል ። በሀብቱና ፡ በባላባትነቱ ፡ የማገባው ፡ መስልዋቸው ፤ ሀብቱን ፡ ባላባትነቱን ፤ ውበቱን ፡ በቅድሚያ ፡ ተንትነው ፡ ነገሩኝ ።

ዋ ፤ ሰው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ሀብት ፤ የሰው ፡ ውበት ፤ ምን ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መስልዋቸው ፡ ይሆን ? ሀብት ፡ ጤዛ ፡ ነው ። ይጠፋል ። ውበትም ፡ ረጋፊ ፡ ነው ። የርሱ ፡ ሀብት ፡ ለኔ ፡ ምንድር ፡ ነው ። አንድ ፡ እንጀራ ፡ ለሆድ ፤ አንድ ፡ ልብስ ፡ ለሥጋዬ ፡ መሸፈኛ ፡ ይበቃል። ለዓይን፡ ተስፋ ፡ ሆኖ ፡ ራሴን ፡ በራሴ ፡ ማታለል ፡ ካልሆነ ፤ ሌላው ፡ ምንም ፡ ፋይዳ ፡ የለውም ።

ልጄ ፡ አባክህን፡ ስማኝ ። በሐሳብ፡ አልወዛወዝ። ቀርጮ ፡ ወደተነሣሁበት ፡ ግብ፡ ልድረስ ። ለሐሳቤና፡ ለምኞቴ፡ ዕንቅፋት፡ አትሁነኝ ፡ ለኔ ፡ ይጠቅማታል ፡ ብለህ ፡ ያሰብከው፡ ይልቁንም፡ እኔን ፡ እንደሚጐዳኝና ፡ እንደጐዳኝ፤ፈተናም ፡ እንደሚያስከትልብኝ ፡ ብትገነዘብልኝ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አለችኝ ።

እናቴ ፡ በእውነት ፡ አቸነፈችኝ ። በንግግርዋ ፡ ልቤ ፡ ተነካ ። ከፈተና ፡ ላይ ፡ ትጥለኛለህ ፡ ያለቺኝ ፡ የበለጠ ፡ ተሰማኝ። ከዛሬ ፡ ነገ ሐሳብዋን ፡ ለውጣ ፡ ትዳር ፡ እንድትይዝ፡ ወይም ፡ በቤትዋ፡ እንድት



ቀመጥ ፡ ሞከርኩ ። አልሆነም ። እንግዲህ፡ ፈቃድዋ ፡ ይሁን ፤ ሐሳብዋን ፡ ልቀበል ፡ ብዬ ፡ ወሰንኩ ።

በቁርስ ፡ ላይ ፡ ስንነጋገር፤ በመጨረሻ፡ ጊዜ ፡ ስለመጡት፡ ሰዎች፡ አነሣን ። አሁንስ ፡ በቃሽ ፡ ባለኝ ፤ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ጥያቄ፡ ልሰማ ፡ አልፈልግም ፡ አለች ። የእኔም ፡ ምኞት፡ ነው፡ እማማ፤ ስለእኔ ፡ ትዳር፡ መያዝ ፡ ሐሳብሽን ፡ መፈጸም ፡ ፈቃዴ ፡ ሆንዋል ፡ አልኩዋት ።

እቅፍ ፡ አድርጋ ፡ ሳመችኝ ። ቀጥላም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ፈቃድህ ፡ ከሆነ ፤ ስለምታገባት ፡ ልጅ ፡ እንነጋገር። በአባትህም፡ ሆነ፤ በኔ ፡ የበቃ፡ ዩነቃ ፡ ዘመድና ፡ ወገን ፡ የለም። አባትህና፡ እኔ ፡ በመረዳዳት፡ ስንኖር፡ በመካከላችን ፡ አንተን ፡ የመሰለ ፡ የተባረከ ፡ ልጅ፡ ወለድን። ከሁለት፡ ወደ ፡ ሦስት ፡ ቤተሰብ ፡ ደረስን ።

አባትህ ፡ በሞት ፡ ሲለዩን ፤ እኔና ፡ አንተ ፡ ቀረን። የሚጠበቀው ፡ ከአንተ ፡ የሚገኝ ፡ ዘር ፡ ነው ። በጠባይህና፡ በልጅነትህ ፡ በሥራህም ፡ የቀወደድክ ፡ ነህ ። ደኅና ፡ ወገን ፡ ያላትን ፡ ፈልግንና ፡ ተፈላልገን ፡ ብታገባ ፡ እወዳለሁ ፡ አለችኝ ።

እማማ ፡ በመሠረቱ ፡ ጋብቻ ፡ ለመፈጸም ፡ ፈቃዴን፡ ገልጨልሻለሁ ። ባለወገን ፡ የሆነች ፡ እግብቼ ፡ በርስዋ ፡ ወገኖች፡ ባለወገን ፡ ልሆን ፡ ከቶ ፡ ፍላጐት ፡ የለኝም ። ከርስዋ ፡ የምፈልገው፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ከቤት ፡ ባልትና ፡ ሞያ ፡ ጋር ፡ ነው። ከኔ ፡ ጋር ፡ ተባብራ፡ የድካሜና ፡ የሐሳቤ ፡ ተካፋይ ፡ ሆና ፡ የጋራ ፡ ቤታችንን፡ በጥሩ፡ መሠረት ላይ ፡ ለመመሥረት ፡ ፍላጐት ፡ ያላት ፡ እንጂ ፤ ከሞቀ፡ ከተደላደለ ፡ ቤት ፡ ገብታ ፡ እመቤት ፡ ለመሆን ፡ ምኞት ፡ ያላትን ፡ ማግባት ፡ አልፈልግም ።

እኔ ፡ ከምውልበት፡ እማማ ፡ አትውይም ። የዛሬዎቹ፡ ልጃገረዶች፡ አስተሳሰብ፡ ሌላ ፡ ሆንዋል ። በጠባዩና፡ በዕውቀቱ ፡ ተወዳጅ ፡ የሆነ፡ ባል ፡ አይፈልጉም ። ጠባዩና ፡ ዕውቀቱ፡ የራሱ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፤ ብቻ ፡ የደረጀ ፡ ሀብት ፡ ያለው ፡ እንዲሆን፡ ምኞታቸው ፡ የጋለ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የቀነሣ፡ የዕድሜ ፡ እቻ፡ ሳይጠብቁ ፤ ሰውየውን ፡ ሳይሆን ፡ ሀብቱን ፡ እያገቡ ፡ ያለፍቅር ፡ የሚኖሩ ፡ እየበዙ ፡ ሄደዋል ።

የሀብታሞቹ ፡ ልጆች ፡ ወላጆቻቸው፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ እያሉ ፡ ሀብታቸውን ፡ ደልድለው ፡ በውርስ ፡ የሚደርሳቸውን ፡ ያውቃሉ ።

ይህን ፣ በመተማመን፣በዕውቀትና፣በትምህርት፣ሳያድጉ ፣ በመሞላቀቅ፣ እያደጉ ፣ ትዳር ፣ ሲይዙ ፣ ትዳራቸውን ፣ ጠብቀውና ፣ አክብረው ፣ አይኖሩም ።

ትውልድዋ ፣ ከደኃ፣ ቤተሰብ ፣ የሆነ፤ አስተዳደግዋ፣ በዕውቀትና፣ በትምህርት ፣ ሆኖ ፣ መልክ፣ከደም፣ግባት ፣ ጋር ፣ ያላት ፤ በፍቅር ፣ የምታቸንፍ ፣ ሚስት ፣ ካላገኘሁ ፣ አለማግባቴን ፣ እመርጣለሁ ፣ ብዬ ፣ መልስ ፣ ሰጠኋት ።

ከዚህ ፣ ዓለም ፣ ደስታና፣ ስጦታ ፣ ሁሉ ፣ ደግና ፣ ባለሞያ ፤ መልክ ከደም፣ግባት፣ ጋር ፣ አስተባብራ፣ የያዘች ፣ ሚስት ፣ ማግኘት ፣ ታላቅ ፣ ዕድል ፣ ነው ። ይህ ፣ ስጦታ፣ ከድኖች፣ ቤተሰቦች ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ ከሀብታም ፣ ቤተሰቦችም ፣ መካከል ፣ ይገኛል። ፈላጊና ፣ ተፈላጊ ፣ ሳይገናኙ ፣ በመቅረታቸው ፣ ሁሉም ፣ በምኞት ፣ ይቀራል ።

ከደኀና ፣ ቤተሰብ ፣ በጋብቻ፣ ተቀላቅሎ ፣ ወገን ፣ ማብዛት ፣ ልጄ ክፉ ፣ አይመስልህ ። ዘወትር ፣ አይሞላም። በሰው ፣ ላይ ፣ ልዩ ፣ ልዩ፣ ችግር ፣ የሚደርስበት ፣ ጊዜ ፣ አለ። በዚያን ፣ ጊዜ ፣ በወገን ፣ የከበረ ፣ ሰው ፤ የመጣበትን ፣ በሰው ፣ ኃይል፣ ለመከላከል ፣ ይችላል ። ወገን ፣ ከሌለ ፣ ችግሩን ፣ ሁሉ ፣ መቋቋም ፣ ያዳግታል። በወላጆችዋ ፣ ሀብት ፣ የማትመካ ፣ በዕውቀትና ፣ በትምህርት፣ ተጠብቃ፣ ያደገች ፣ ወይዘሪት፣ ተፈላልገን ፣ ብታገባ ፣ ደስ ፣ ይለኛል።በመልክዋ ፤ በደም፣ግባትዋ ፤ በፍቅር ፣ ተማርኮ ፣ በዚህ ፣ ቢጐድል ፣ በዚህ ፣ ታሟላለች ፣ የማትባል ፣አግብቶ ፣ በችግር ፣ ላይ ፣ ችግርን ፣ ከማስከተል ፤ ግዴለህም ፣ ልጄ ፣ በዚህ ፣ ዓለም ፣ ከአንተ ፣ በፊት ፣ ቀድሜ፣ ተገኝቼ ፣ እስካሁን ፣ ባለሁበት ፣ ሕይወቴ ፣ ያጠናሁ ፣ ስለሆነ ፤ ምክሬን ፣ ስማ፣ ብላ ፣ ለመልሴ ፣ መልስ ፣ ሰጠችኝ ።

የናቴና ፣ የኔ ፣ አሰተሳሰብ፣ የሰማይና፣ የምድር ፣ ያህል ፣ ተራራቀ፣ ቢሆንም ፣ ማስተሐቀር ፣ ስላልፈለግሁ ፤ በተቻለ፣ መጠን ፣ በጊዜው ፣ ላይ ፣ የሚታየውንና ፣ የደረሰውን ፣ ሁሉ፣ በመዘርዘር ፣ አስረድቼ ፣ ሐሳብዋን ፣ ወደሐሳቤ ፣ ለመመለስ ፣ ስል፣ ባንደበቴም ፣ በአኳኋኔም ፣ ለሰለስኩ ። እማማ ፣ እንኳን ፣ ምክርሽን፣ ትእዛዝሽን ፣ በደስታ ፣ እንደምቀበል ፣ እመኚ ። ለኔ ፣ ደኅንነት ፣ ያለው ፣ ኑሮ፣ ለመመሥረት ፣ ያለሽ በጐ ፣ ፈቃድ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ መሆኑን ፣ ዐውቃለሁ ።



ካሁን ፣ ቀደም ፣ እንደገለጽኩልሽ ፤ እኔ ፣ ከምውልበት ፣ አትውይም ። እኔ ፣ የምሰማውን ፣ አትሰሚም ። ያንቺ ፣ አስተሳሰብ ፣ ከብዙ ዓመታት ፣ በፊት ፣ የነበረውን ፤ የተከተለ፣ ነው ። እኔ ፣ የማየው ፣ ባለንበት ፣ ዘመን ፣ ያለውንና ፣ ከዓመት፣ ወደ ፣ ዓመት ፣ ጠባዩን ፣ እየለወጠ ፤ ባህላችን ፣ በሌላ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ የሀገር፣ ባህል ፣ እየተበከለ ፣ መልኩን ፣ ለውጧል ።

ሰው ፣ የሚመራውና፣ ዕድሉ፣ የሚመሠረተው ፣ በእግዚአብሔር፣ ቸርነት ፣ እንጂ ፣ በሰው ፣ ፈቃድና ፣ ስጦታ፣ አይደለም ። መገኛ ፣ የሆነው ፣ አዳም ፣ አንድ ፣ ነው ። ከርሱ ፣ የተገኘው ፣ ሰው ፣ ተባዝቶ ፣ በመልክ ፤ በቋንቋ፣የተለያየ ፣ ሆኖ ፣ ዓለምን፣ አልብሶ ፣ ይኖራል ። ከትውልድ ፣ ሲያያዝ ፣ በመጣ ፣ ታላቅነት ፤ ታላቅነትን ፣ እንደንብረት ፣ ወርሶ ፣ ታላቅ ፣ የሚሆን፣ አለ ። ከትውልድ ፣ ያገኘውን ፣ ታላቅነት ፣ ወደ ፣ ታናሽነት ፣ አውርዶ፣ ታናሽ ፣ የታናሽ ፣ ታናሽ ፣ የሚሆን ፣ አለ ።

ከታናሽ፣ ቤተሰብ ፣ ተገኝቶ ፣ ራሱን፣ ወደታላቅነት ፣ ደረጃ ፣ ከፍ፣ የሚያደርግና ፣ የብዙዎች ፣ ወገንና ፣ መሪ ፣ የሚሆን ፣ አለ ።

ችግርና ፣ መከራ ፣ በዚህ ፣ ዓለም ፣ ላይ ፣ ለሰው ፣ የቅርብ ፣ ጓደኛ ፤ መታሰቢያውና ፣ መፈተኛው ፣ የሕይወት ፣ ታሪኩ ፣ ናቸው ። መከራና ፣ ችግር ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ ያልጠበቁት፣ ውለታ ፣ የሌለው ፣ የመከራውና ፣ የችግሩ ፣ ተካፋይ ፣ እንዲሆን ፣ ጊዜው፣ ራሱ ፣ ይፈጥረዋል ።

ለሰው፣ ጠላቱ፣ ራሱ፣ ነው ። ካቅሙ ፣ በላይ ፣ የሚፈልግ፣ ከሚጠቅመው ፣ ይልቅ ፣ ይጐዳዋል ፣ ሰው፣ ወደተመኘው ፣ ግብ ፣ የሚደርሰው ፣ በፈቃደ፣እግዚአብሔር፣ ነው። ያሰቡት ፣ ወይም ፣ የተመኙት ፣ የሚፈጸመው ፣ በእምነት ፣ ስለሆነ ፣ እምነታችን ፣ ሁሉ ፣ በፈጠረን፣ በአንድ ፣ እግዚአብሔር ፣ ይሁን ።

ከደኃ ፣ ቤተሰቦች ፣ ደኃ ፣ አደግ ፣ የሆንች ፣ በዕውቀትና ፣ በትምህርት ፣ አድጋ ፣ አስተዋይ ፣ ካልሆንች ፣ ንብረት ፣ ብትይዝም ፣ በልዩ፣ ልዩ ፣ ጠባይ ፣ ንብረትዋን ፣ ታፈርሰዋለች ፣ ከሀብታም ፣ ቤተሰብ ፣ የምትገኘው ፣ በተፈጥሮ ፣ ከተሰጣት ፣ አስተዋይነት ፣ ጋር ፣ በዕውቀትና ፣ በትምህርት፣ ካደገች ፣ የወላጆችዋን፣ ታላቅነት ፣ ወይም ፣ ሀብት ፣ ዋጋ፣ ሳትሰጠው ፣ ራስዋን ፣ በራስዋ ፣ ታላቅ ፣ ለማድረግ ፣ ትጥራለች ።

ይሁን ፣ እንጂ ፣ የነእገሌ ፣ ወገን ፣ ናት ፣ ወገን ፣ ይሆኑኛል። የእገሌ፣ ልጅ ፣ ናት ፣ ወገንነትዋ ፣ አይጠቅመንም፣ በሚል ፣ አስተያየት ፣ ሳንመራ

የምፈልግ ፡ ልጅቱን ፡ ስለሆን ፡ በጠባይዋ፡ በሞያዋና ፡ በዕውቀትዋ ፡ የታወቀች ፡ በውበትና ፡ በደምግባትዋ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ በፍቅር ፡ የምትማርክ ፡ ይህች ፡ ዓይነትዋ ፡ ብትገኝ ፡ ሚስቴ ፡ ትሆናለች ፡ የሚለት ፡ እምነት፡ አለኝ ። ምርጫዬ ፡ ይህ ፡ መሆኑን፡ ውድ፡ እናቴ ፡ ብታውቂው፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ብዬ ፡ አስረዳኋት ።

እናቴ ፡ በፈገግታ ፡ ልጄ ፡ እንኳን ፡ በዕድሜና ፡ በአዕምሮ ፡ በጐለመስከበት ፡ በአሁኑ፡ ወቅት፡ በዕድሜና ፡ በአዕምሮ ፡ ባልጐለመስከበት፡ ጊዜ ፡ አስተያየትህና ፡ አስተሳሰብህ ፡ ሁሉ ፡ ቀላል ፡ አልነበረም ። አሁንማ ፡ እንኳን፡ ለራስህ፡ ለሌላም፡ የሚጠቅመውንና ፡ የማይጠቅመውን፡ ለይተህ ፡ ለመምከር ፡ ትችላለህ ። ራስህን ፡ በራስህ ፡ ለመርዳት ፡ በማትችልበት፡ ወቅት ፡ አባትህ ፡ በሞት ፡ ተለዩህ። እኔ ፡ ብኖርም ፡ በሴት፡ አቅሜ፡ ምንም ፡ ልረዳህ ፡ አልችልም ። ብቸኛ ፡ ስለሆንክ ፡ የኛ ፡ ነው፡ የሚሉህ ፡ የኔ ፡ ናቸው፡ የምትላቸው፡ ወገኖች፡ ያገኘህልኝ ፡ መስሎኝ፡ በወገን ፡ የከበረች ፡ እንድታገባ ፡ የፈለግሁት ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በአስተሳሰብና ፡ በአስተያየት፡ በጣም ፡ በመራቀቅህ ፡ ያንተ ፡ አስተሳሰብ ፡ የራቀና ፡ የጠለቀ ፡ የኔ ፡ ግን ፡ ከገርነት ፡ የመጣ ፡ ስለሆነ ፡ሐሳቤን ፡ በአንተ ፡ ሐሳብ፡ ለውጬ ፡ ተስማምቻለሁ ። እንዳልከው ፡ ይፈጸም ፡ ብላ ፡ መልስ ፡ ሰጠችኝ ።

ከእናቴ ፡ጋር ፡በሐሳብ ፡ ባለመለያየታችንና ፤ ይልቁንም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቅሬታ ፡ ሳይሰማት ፡ ሐሳቤን፡ በመቀበልዋ ፤ ርስዋን ፡ አስደስት ፡ ብዬ ፡ ሚስትን ፡ ያህል ፡ ምርጫ ፡ የማልፈልገውን ፡ ከማድረግ ስለዳንኩ ፤ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ እናቴን ፡ አመስግኜ ፡ ሳምኳት ።

እናቴ ፡ ለምታውቃቸው ፡ እባካችሁን ፡ ለልጄ ፡ የትዳር፡ ጓደኛ፡ የምትሆን ፤ ከቤተ ፡ ሰብዎችዎ ፡ ጀምሮ ፡ መልካም ፡ ቤተሰብነት ፡ ያላት ፤ ርሱ ፡ አይቶ ፡ በርሱ ፡ ምርጫ ፡ ቢወድ ፡ የሚያገባት ፡ አመልክቱኝ ፡ እያለች ፡ ሐሳብዋን ፡ አካፈለች ።

እኔም ፡ በትምህርት ፡ ጓደኞቼ ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ሐሳቤን፡ አካፈልኩ ፤ እናቴ ፡ ሐሳብ፡ ያካፈለቻቸው፡እኔም ፡ የነገርኳቸው ፤ የብዙ፡ ልጃገረዶች ፡ ስም ፡ ጠቅላላ፡ ሆኔታቸውን፡ ሳይቀር ፤ በመዘርዘር ፡ ማስታወሻ ፡ ለኔም ፡ ለእናቴም ፡ ደረሰን ። አይቶ ፡ መምረጥ ፡ የማንም፡ ሳይሆን፡ በተለይ ፡ የኔ ፡ ብቻ ፡ ድርሻ ፡ ሆነ ።



እየተዘዋወርኩ፡ ሁሉንም፡ አየሁ ። ዓይን፡ አዋጅ ፡ ሆነብኝ ። ቢሆንም፡ ስሜቴን፡ የሚያስጨንቅ፡ አላጋጠመኝም ። ያየኋቸው፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ምኞቴን ፡ አልያዙም ። ይህንኑ፡ በሐሳቤ ፡ ሳመላልስ ፤ቆንጆ፡ ልጃገረድ ፡ ከእናትዋ፡ ጋር፡ ስትሄድ፡ በድንገት፡ በመንገድ ፡ አገኘኋቸው፤ ገና ፡ ሳያት ፡ በጣም ፡ ደነገጥኩ ። ልቤ ፡ በኃይል ፡ መታ ። ለእናትዋ ፡ ሰላምታ ፡ ሰጠኋቸው ። ርሳቸውም ፡ ሰጡኝ። ከተል፡ አልኩና ፡ ወዴት፡ እንደሚሄዱ ፤ ከወዴት ፡ እንደመጡ ፡ አድራሻቸውን ፡ ሳይቀር ፡ ጠየቅኋቸው ። ርሳቸው ፡ በትሕትና ፡ ነገሩኝ ። የሚሄዱበት፡ ከተገናኘንበት፡ ቅርብ ፡ ስለነበር ፤ እያነጋገርኳቸው ፤ አብረን ፡ ሄድን ። ርሳቸው ፡ ግን፡ በመጨነቅ ፡ እባክህን ፡ ልጄ ፡ ተመልስ፡ ይሉኛል። ልጃቸውን፡ አትኩሬ፡ እየተመለከትኩ ፡ ስሸኛቸው ፤ ርስዋም ፡ ታየኛለች ። አልዋሽም ፤ ወደድኳት ።

ወደቤቴ ፡ ገሠገስኩ ። ደርሼ ፡ ለእናቴ ፡ እስክነግራት ፡ ቸኰልኩ። ቀደም ፡ ብዬ ፡ ሐሳቤን ፡ ካካፈልኩት ፡ አንዱን ፡ ጓደኛዬን፡ በመንገድ፡ አገኘሁት ። በበኩሉ ፡ የደረሰበትን ፡ ገለጠልኝ። በመጀመሪያ ፡ ደረጃ፡ ለእናቴ ፡ ነግሬ ፡ የርስዋን ፡ ፈቃድ ፡ ሳላውቅ ፡ መግለጥ ፡ ስላልፈለግሁ ፡ በማጥናትና ፡ በመከታተል ፡ ላይ ፡ ስለሆንኩ ፤ ውጤቱን ፡ በቅርብ፡ ቀን፡ አስታውቅሃለሁ ፡ ብዬ ፡ መንገዴን ፡ ቀጠልኩ ።

ከቤቴ ፡ ስደርስ ፤ እናቴ ፡ ስትጠብቀኝ ፡ አገኘኋት ፤ ከውጭ ፡ ውዬ፡ ስገባና ፤ ጥዋት ፡ እንደምን ፡ አደርሽ ፡ ስላት ፤ ስለምንሳሳም ፤ በዚሁ ፡ ልማድ ፡ ከሳምኳት፡ በኋላ ፤ እማማ፡ አልኳት ። ምነው ፡ ልጄ ፡ አለችኝ።

እማማ ! ዛሬ ፡ በእውነት ፡ ደስ ፡ ብሎኛልና ፡ አንቺም ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ አልኳት ፡ ያንተ ፡ ደስታ ፡ ደስታዬ ፡ ነው ፤ ድካሜና ፡ ጥረቴ፡ ሁሉ፡ አንተ ፡ ደስ ፡ እንዲልህና ፡ ያንተን ፡ ደስታ ፡ ለማየት ፡ ነው ፡ ብላ ፡ መለሰችልኝ ።

እማማዬ ! በአንቺም ፡ በኔም ፡ በኩል ፡ የደረሰንን፡ ዝርዝር ፡ መነሻ፡ በማድረግ ፤ እየተዘዋወርኩ ፡ ለትዳር ፡ ጓደኛ ፡ የምትሆነኝ ፡ ስመለከትና፡ በመጠያየቅ ፡ ሳጠና ፡ ዋልኩ ።

«የተጠሩት፡ ብዙዎች፡ ናቸው። የተመረጡት፡ ጥቂቶች፡ ናቸው ፡ » እንደተባለው፤ ብዙ ፡ ሰዎችን፡ አየሁ ። አንዳቸውም ፡ አልማረኩኝም ። «መራጭ ፡ ይወድቃል ፡ ከምራጭ » የተባለው፡ ተረት ፡ ደርሶብኝ፡ መተ

ረቻ ፡ እንዳልሆን ፡ እያልኩ፣ ከሐሳቤ ፡ ጋር ፡ እየተነጋገርኩ ፣ ወደቤቴ፡ ስመጣ ፣ አንዲት፡ ልጃገረድ ፡ ከእናትዋ ፡ ጋር፡ በመንገድ ፡ አገኘኋት ። ቀና ፡ ብዬ ፡ ሳያት ፡ ደነገጥኩ። ልቤም ፡ መታ ። እናትዋን ፡ በማነጋገር፡ ደኅና ፡ አድርጌ ፡ አየኋት ። እማማ ፡ አልዋሸም ፡ በጣም ፡ ወደድኳት ። አሁንም ፡ በፊቴ ፡ ላይ ፡ ውል ፡ እያለች ፡ ትታየኛለች ።

ይህ ፡ ድንገተኛ ፡ ግጥሚያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ፡ የተደገፈ፡ ከሆን ፣ ይህች ፡ የያኋት፡ ልጅ ፡ በእውነት ፡ ሚስቴ ፡ ናት ። በዕውቀትና፡ በትምህርት ፡ በምን ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ እንደምትገኝ ፡ ለማወቅ፡ ባልችልም፡ ወድጃታለሁና ፣ ባትማርም ፡ እኔ ፡ አስተምራታለሁ ፡ ብዬ ፡ ነገርኳት ።

እናቴ ፡ ደስታዬን ፡ በስሜቴ ፡ ላይ ፡ አንብባው ፡ ስለነበር ፡ አንተ፡ ከወደድካት፣ አንተን ፡ በእውነት ፡ እወዳለሁ ፡ የሚል ፡ ሁሉ ፡ መወደድ ፡ አለበት ። ሴት ፡ ልጅ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ካላት ፣ በቤት ፡ ባልትና ፡ሞያ፡ ቤትዋን ፡ ካቸነፈች ፣ ባልዋን ፡ በፍቅር ፡ ከጠበቀችና፣ ልጆችዋን፡ በጥሩ፡ ሁኔታ ፡ ማሳደግ ፡ ከቻለች ፡ ቤተሰብዋን፡ በሥነ ፡ሥርዓት፡ ካስተዳደረች፡ የሚፈለገውን ፡ ዕውቀት ፡ አሟልታ ፡ ይዛለች ፡ ማለት ፡ ነው ።

ልጄ ፡ ታዝናለህ ፡ ወይም ፡ ቅር ፡ ይልሃል ፡ ብዬ ፡ አልነገርኩህም፡ እንጂ ፣ ምርጫህ ፡ ወደ ፡ ከተሜ ፡ ልጃገረዶች ፡ ያዘነበለ ፡ እየመሰለኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እንደምን ፡ ታደርገኝ ፡ ይሆን፡ እያልኩ፡ መጸለዬ ፡ አልቀረም። የከተሜ ፡ ልጃገረዶች ፡ በሰው ፡ ሠራሽ ፡ ቀለም ፡ ተኳኩለው፡ በስም፡ ልጃገረድ ፡ ይባላሉ ፡ ትዳር ፡ ሲይዙ ፡ በቤት ፡ እያያዝ ፡ ሞያ ፡ ከወንድ ፡ ያልተሻሉ ፡ እየሆኑ ፡ አሽከር ፣ ወይም ፡ ገረድ ፡ አኩርፈው ፡ ሲሄዱ ፡ ከወጥ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ባለመተዋወቃቸው ፡ ምግብ ፡ ፍለጋ ፡ ወደ፡ ሆቴል፡ ይሄዳሉ ። ድንገተኛ ፡ እንግዳ ፡ በቤታቸው ፡ ሲመጣ፡ በሻይ ፡ ወይም፡ በቡና ፡ ይሸነግሉታል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ማቅረብ ፡ አይችሉም ። ልጄ ፡ ያንተ ፡ ቤት ፡ ሰፊና ፡ ሙሉ ፡ ስለሆነ ፣ ምንም ፡ እንኳን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ ያላቸው ፡ ሠራተኞች ፡ ቢቀጠሩም ፣ የቤትዋ ፡ እመቤት፣ ከተቀጠሩት ፡ ላቅ ፡ ያለ ፡ ሙያ ፡ የሌላት ፡ ከሆነ ፣ ቤቱ ፡ የተሟላ ፡ አይ ሆንም ።

ልጄ ፡ ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ በቤት፡ ውስጥ፡ የሚያስፈልገውን፡ዐውቆ፡ ለዓመትና ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ የሚያገለግል ፡ የቤት ፡ ባልትና፡ የሚጠ ይቀውን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ቤትን ፡ ማሟላት ፡ ቀላል ፡ ሞያ ፡ አይደለም ።



የቤትዋ ፡ እመቤት ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ባልዋን ፡ የደገፈችው፡ እን ደሆነ ፣ በቤት ፡ ውስጥ ፡ በረከት ፡ ይወርዳል ። እንግዳ ፡ ሲመጣ ፣ ባል ፡ በቤቱ ፡ አያፍርም ። ለቁጠባም ፡ ይረዳል ።

የአገር ፡ ቤት ፡ አደግ ፡ የሆነች ፣ የባልትና ፡ ሞያ ፡ ከልጅነትዋ ፣ ጀምራ ፡ ከቤተሰቦችዋ ፡ ስለምታጠና ፡ የተሟላ ፡ ሞያ ፡ ይኖራታል ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፡ ለመማር ፡ ወደ፡ትምህርት ፡ ቤት ፡ ብትላክም ፣ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ውጪ ፡ ያላትን ፡ ጊዜ ፡ የምታሳልፈው ፡ ከቤተሰ ብዎችዋ ፡ ጋር ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ስለሆነ ፣ በልማድ ፡ ያገኘች ውን ፡ ዕውቀት ፡ በትምህርት ፡ ካገኘችው ፡ ጋር ፡ ስታስተባብረው ፡ መልካም ፡ ባለሞያ ፡ እመቤት ፡ ትሆናለች ፡ አለችና ፣ ይህቺን ፡ የወደ ድካትን ፡ ልጅ ፡ ባላያትም ፡ እኔም ፡ ወደድኳት ። አስካያትም ፡ ቸኮ ልኩ ። ለቤተሰብዎችዋ ፡ መልእክተኞች ፡ መቼ፡ ነው ፡ የምንልከው ፡ ብላ ፡ ጠየቀችኝ ።

በተጠንቀቅ ፡ የምጠባበቀው ፡ በእናቴ ፡ ዘንድ ፡ ቅሬታ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ እንዳልሠራ፣ ለኔ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ የምሠራው፡ እናቴንም፡ እንዲ ያስደስት ፡ ስለሆነ ፣ ሐሳቤን ፡ ሁሉ ፡ ከልብ ፡ በመቀበልዋ ፡ ደስ ፡ ስላ ለኝ ፣ በቅድሚያ ፡ አመሰገንኳት ፣ ቀጥዬም ፡ የልጅቱን ፡ እናት ፡ አድ ራሻ ፡ ጠይቄ ፡ እንደተረዳሁት ፡ ቤታቸው፡ ከአቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ቤት ፡አቅ ራቢያ ፡ ነው። ሐሳባችንን ፡ ለአቶ ፡ ገንዘቤ፡ ብናካፍለው፡ የልጅቷንና፡ የቤተሰብዎችዋን ፡ ሁኔታ ፡ ሊያስረዳ ፡ ይችላል ፡ ብዬ ፡ ለጥያቄዋ ፡ መልስ ሰጠሁ ።

አቶ ፡ ገንዘቤ ፣ ሰብሰብ ፡ ብሎ፡ የተቀመጠ ፡ በጎ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ፡ የሐሳባችን ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናል።መልካም፡ ነው ፡ ሄደን ፡ እናማክረው፡ አለችና ፣ ጉዞዋችንን ፡ ወደአቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ቤት ፡ ቀጥለን ፡ ደረስን ። አቶ ፡ ገንዘቤም ፡ በመጥረብረብ ፡ ተቀበለን ፣ የደረስነው ፡ በቁርስ ፡ ሰዓት ፡ ስለነበር ፣ ቀርቦልን ፡ ተመገብን ። ከቁርስ ፡ በኋላ ፣ ከረዥም ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያለንን ፡ ወዳጅነት፡ በማስታወስ ፡ ሐሳባችንን ፡ ልናካፍ ልህ ፡ በጥዋት ፡ መጣን ። እንደምታውቀው ፡ ልጄ ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ ደርሰዋል ። ትዳር ፡ እንዲይዝ ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ የኑሮ፡ ጓደኛ ፡ የምትሆ ነውን ፡ ራሱ ፡ እንዲመርጥ ፡ ተስማምተን ፡ በመፈላለግ ፡ ላይ ፡ ቆይተ ናል ።

ዝርዝር ፡ ሁኔታዋን ፡ ሳያውቅ ፤ በቁንጅናዋ ፤ በደምግባትዋ ፡ አንድ ፡ ልጃገረድ ፡ ወድዋል ። ሚስትን ፡ ያህል ፡ ታላቅ፡ ምርጫ፡ርሱ፡ ከወደዳት ፡ እኛም ፡ መውደድ፡ አለብን ። ነገር ፡ ግን ፡ ጋብቻቸው፡ጋብ ቻችን ፡ የማይሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ካለ ፤ ልጁ ፡ ልጅቱን ፡ ወድጃታ ለሁ ፡ ብሎ ፡ ከፈቃዳችን ፡ አይወጣም ። የልጅቱ ፡ እናት ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ይባላሉ ። የሚኖሩት፡ በዚሁ ፡ በአንተ ፡ አቅራቢያ ፡ በቅርብ፡ ጕርብትና ፡ ነው ፤ ብላ ፡ እናቴ ፡ ነገረችው ።

መልስ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ በዝምታ፡ አሰበ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ እናቴና ፡ እኔ ፡ ተያየን ። ልጅቱን ፡ በእውነት ፡ ወድጃት ፡ አሁንም ፡ በፊቴ ፡ ውል ፡ ስለምትል ፤ ጋብቻን፡ የሚያፈርስ ፡ ነውር ፡ በልጅቱ ፡ ወይም ፡ በቤተሰብዋ ፡ ላይ ፡ ይኖር ? እያልኩ ፡ በመጨነቅ ፡ ልቤ ፡ እየመታ ፤ አቶ ፡ ገንዘቤ ፡ የሚናገረውን ፡ ለመስማት ፡ በናፍቆት ፡ ተጠባበቅሁ ። ይገርማል ! የዘነበች ፡ ልጅ ፡ ስምዋ ፡ ፀሐይ ፡ ነው ፡ አለና ፤ ስም ፡ ከምግባር ፡ ጋር ፡ አስተባብራ ፡ የያዘች ፡ ቆንጆ ፡ የቆንጆ ፡ ቆንጆ ፡ ናት ። ልጅሽ፡ በእውነት ፡ ምርጫ ፡ የሚያውቅ ፡ አስ ተዋይ ፡ ነው ። ፀሐይ ፡ ያልተወደደች፡ ማን ፡ ይወደዳል። እንዲያውም፡ አባትዋ ፡ አቶ ፡ ቡሩክ ፡ ከሞተ ፡ ጀምሮ፡ በኀዘን ፡ የተነሣ፡ ተጐሳቁላ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ርሱ ፡ በነበረበት፡ ወቅት ፡ ከውበትዋ ፡ የተነሣ ፤ ያያት ፡ ሁሉ ፡ ስንቱ ፡ ሳስቶላት ፡ ነበር፡ መሰለሽ ። አባትዋ ፡ ደግ ፡ ሰው፡ነበር። እንደ፡ ሀገራችን፡ ልማድ፡ በወግ፡ በሥርዓት፡ አስተምሮ፡ አሳድጓታል። የተዋበ፡ መልክ ፡ መልካም ፡ በመሆኑ፤ ልጅቱ፡ በርሱ፡ ነው፡ የወጣች ፤ እናትዋ፡ በአካባቢው፡ እጅግም፡ ተወዳጅ፡ አይደለችም። ስምዋ፡ በደግ፡ አይነሣም ፤ ግን ፡ ወሬ ፡ ከመስማቴ ፡ በቀር፡ የማውቀው፡ ነገር፡ የለም።

ኩራት ፡ እራት ፡ ነው፡ እንደሚባለው፤ ከመንደሩ ፡ ሴቶች ፡ ጋር፡ የቡና ፡ አጣጭነት ፡ ማኅበር ፡ የላትም ። የመንደሩ፡ ሴቶች ፡ በጥላቻ ፡ ስምዋን ፡ ይጠሩታል ። ባልዋ ፡ አቶ ፡ ቡሩክ ፡ በነበረበት ፡ ወቅት ፤ ቤቱን ፡ ዐውቀዋለሁ ። የቤቷ ፡ የባልትና ፡ አያያዝና፡ የወይዘሮ ፡ ዘነ በች ፡ የእንግዳ ፡ አቀባበል ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነበር ። ሆኖም፡ ለወሬ ፡ የለው ፡ ፍሬ ፡ እንደሚባለው ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ክብርዋን ፡ ጠብቃ፡ ቤትዋን ፡ አክብራና ፡ አስከብራ፡ መኖርዋን ፡ ያልወደዱ ፡ የመንደር ፡ ሴቶች ፡ በምቀኝነት ፡ ወይም፡ በቅናት ፡ ስምዋን ፡ እያጠፉ ፡ ለሚያው ቋትና ፡ ለማያውቋት ፡ የተናገሩት ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጠው ፡ አይደለም ።



የልጅሽ ፡ ምርጫ ፡ መልካም ፡ ስለሆነ፤ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፡ አለ ፡ አቶ ፡ ገንዘቤ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ፡ ደስታ ፡ ተሰማኝ ። ልጅቱን ፡ እንደወ ደድኳት ፡ እናቴ ፡ የተረዳች ፡ ስለሆነ ፤ ዓይን፡ ዓይኔን ፡ እያየች ፡ ደስ ፡ አላት ። በተያየንበትም ፡ ወቅት ፡ በደስታ ፡ ተሳሳቅን ።

መልካም ፡ ነገር ፡ መስማት ፡ የልብ ፡ ተስፋ ፡ ነው ። በጋብቻ፡ስለ ፈለግናት ፡ ልጅና ፡ ስለቤተሰብዋ ፡ የነገርከን ፡ ልባችንን ፡ በደስታ ፡ አረካው ። እንግዲህ ፡ ለኛም ፡ በልጅቱም ፡ በኩል ፡ አንተ ፡ ቅርብ፡ስለ ሆንክ ፤ መልእክተኛችን ፡ ሆነህ ፡ ብትላከን ፤ የበለጠ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ አለችው ።

ያቶ ፡ ቡሩክን ፡ ያህል ፡ ከወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ጋር ፡ የተቀራረበ ፡ ጨዋታ ፡ ባይኖረንም ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በቤታቸው ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ ስለ ሆንኩ ፤ ዕውቀታችን ፡ የቆየ ፡ ነው ። አቶ ፡ ቡሩክ ፡ በሞተበት ፡ ጊዜ ፡ መዋዕለ ፡ ኀዘኑ ፡ እስኪያልቅ ፡ በማጽናናት ፡ አልተለየኋቸውም ። በና ንተም ፡ በኩል ፡ ሆነ ፤ በልጅቱ ፡ ከኔ ፡ የሚያልፍ፡ አይደለም ። እጨር ሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ለእናቴ ፡ መልስ ፡ ሰጠ ።

ምኞታችን ፡ እንዳሰብነው ፡ በመሳካቱ ፡ የኔና ፡ የእናቴ ፡ ደስታ ፡ የጋለ ፡ ሆነ ። ሐሳባችን ፡ ሐሳቡ፡ ሆኖ ፤ ጥያቄያችንን፡ ሁሉ ፡ በደስታ፡ ስለተቀበለው ፡ እናቴ ፡ ከልብ ፡ አቶ ፡ ገንዘቤን ፡ አመሰገነችው ። መል ሱን ፡ ለመቀበል ፡ የሳምንት ፡ ቀጠሮ ፡ አድርገን ፡ ወደቤታችን ፡ ተመ ለስን ። የቀጠሮው ፡ ቀን ፡ እስኪደርስ ፤ እኔ ፡ ቸኩልኩ ። ቀጠሮዋችን ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ እናቴ ፡ የምትጠላው ፡ የባል ፡ ጥያቄ ፡ መጣ ። በት ዳር ፡ ጓደኛነት ፡ የፈለጋት ፡ ካለንበት ፡ በእግር ፡ ጉዞ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ርቀት ፡ አለው ። ስለኔ ፡ የተጀመረው ፡ ንግግር ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋ ዥነት ፡ መልካም ፡ ፍጻሜ፡ እንዲያገኝ፡ በሐሳብ ፡ ላይ ፡ ስለሆነች፡ በቀ ጥታ ፡ በራስዋ ፡ ላይ ፡ ስለመጣው ፡ ጥያቄ ፡ እንዳለፈው ፡ ጊዜ ፡ ሳትበ ሳጭ፡ እንዲያውም፡ እየሳቀች፡ መልእክተኞቹን፡ ተቀብላ ፡አነጋገረች።

መልእክተኞቹም ፡ የተላኩበትን ፡ መልእክት ፡ አደረሱ። እናቴም፡ በፀጥታ ፡ መልእክተኞቹን ፡ ሰማች ። ከሰው ፡ ሰውን ፡ በማበላለጥ፡ሳይ ሆን ፤ በመሠረቱ ፡ ባል ፡ የማግባት ፡ ፍላጎት ፡ ስለሌለኝ ፤ ጌቶቼ ፡ ጥያ ቄያችሁን ፡ ባለመቀበሌ ፡ ይቅርታ፡ አድርጉልኝ ፡ አለቻቸው ። ሐሳብ፡

ዋን ፡ ስትገልጽ ፤ ለዘብ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ ስለነበር ፤ የመግደርደር ፡ መስኋቸው ፡ ሐሳብዋን ፡ እንድትለውጥ ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ ተናገሩ ። ለጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ በትዕግሥት ፡ አዳምጣ ፤ ለጥያቄያችሁ ፡ አጭር ፡ መልስ ፡ የሰጠሁት ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ እንዳልሰማ ፡ ነበር ። ያንድ ፡ ሰው ፡ ታላቅነት ፡ ወይም፡ ታናሽነት ፡ ለራሱ ፡ እንጂ ፤ ለማንም ፡ አይጠቅምም ። እያንዳንዱ ፡ የሚኖረው ፡ እንደተሰጠው ፡ ዕድል ፡ ነው ። በስም ፡ መከበር ፤ በሀብትም ፡ መዳበር ፡ ሰውን ፡ እያስደሰተውም ። ሎሚና ፡ ጠጅ ፡ ቢያዘወትርም ፤ ፍላጎቱ ፡ ሳይሟላና፡ ሳይደሰት፡ ይኖራል ። ጥሬ ፡ ተመግቦ ፤ ጥሩ፡ ውሃ ፡ ጠጥቶ ፡ ከምስጋና ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ብሎት፡ የሚኖር ፡ አለ ። በስም፡ ከከበረውና ፤ ባለጸጋ ፡ ከሆነው ፡ የዕለት ፡ ምግቡን ፡ ጥራጥሬ ፡ ተመግቦ ፡ ከኖረው ፤ ማንኛውም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ደስ ፡ እንዳለው ፡ ራሳችሁ ፡ አመዛዝኑት ።

ደስታ ፡ ከሌለ ፤ ክብርና ፡ ባለጸግነት ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ፤ ደስታ ከራስ ፡ ስሜት ፡ የሚመነጭ ፡ ነው ። ባለጸግነት ፡ በማጭበርበርና ፤ ራስን ፡ ከመውደድ ፡ የተነሣ ፡ የተፈጥሮ ፡ ወንድምን ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፡ አሁን ፡ ተገኝቶ ፤ ነገ ፡ የሚጠፋ ፡ የማይጨበጥ ፡ ነው ። ከልብ የሚመነጭ ፡ ደስታ ፡ ግን ፡ አብሮ ፡ የሚኖር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የማይለወጥ ፡ የውስጥ ፡ ስሜት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ባል ፡ አግብቼ ፡ ከማገኘው፡ ደስታ ፤ ብቸኛ ፡ ሆኜ፡ብኖር፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ አገኛለሁ ፡ ብዬ ፡ ያመንኩና ፤ እምነቴም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሆኖ ፡ ከፍጻሜ ፡ እንደሚደርስ ፡ ተስፋ ፡ ያለኝ ፡ ስለሆነ ፤ ጌቶቼ ፡ ንግግር ፡ ሳታበዙ ፤ በሰላም ፡ ወደ ፡ መጣችሁበት ፡ እንድትመለሱ ፡ እለምናችኋለሁ ፡ ብላ ፡ የመጨረሻ ፡ ቃሏን ፡ ሰጠች ።

መልእክተኞቹ ፡ በእናቴ ፡ የሐሳብ፡ አገላለጥ ፡ ተደንቀው ፤ የልቡናዎን ፡ ያስፈጽምዎ ፡ ብለው ፡ ተሰናብተው ፡ ተመለሱ ።

እናቴ፡ መበሳጨትዋን፡ ትታ፤ አሁንም፡ እየተገረመች፤ አዬ፡ ሰው! የሰውን ፡ አስተሳሰብና ፡ አስተያየት ፡ አተኩረው ፡ ሲያዩት ፤ ሰው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ትንግርት ፡ ነው ። በክርስትና ፡ እምነት ፡ «እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ነው ፤ ፍቅር ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው» ፡ እያሉ ፡ ምሁራን ፡ ያስተምራሉ ። ሰው ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ካለው ፡ ፍቅር ፡ ይልቅ ፤ ከገንዘብ ፡



ጋር ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ የበለጠ ፡ ግምት ፡ ስለተሰጠው ፤ ስለአንድ ፡ ሰው፡ ታሪክ ፡ ሲነገር ፡ በቅድሚያ ፡ የሚተረከው ፡ የሀብቱ ፡ ምላትና፡ ስፋት፡ ነው ። ጠባዩና ፡ አስተሳሰቡ ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ቢቀርብም ፡ ማናቸውም ፡ ገመናው ፡ በሀብቱ ፡ እየተጋረደ ፡ እምብዛም ፡ ተጋንኖ ፡ አይተረክም ፡ ብላ ፡ በአድናቆት ፡ አጫወተችኝ ።

ከአቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ጋር ፡ ያደረግነው ፡ የሳምንት ፡ ቀጠሮ ፡ ደረሰ ። ማለድ ፡ ብለን ፡ ሄድን ። አቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ቁርስ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ጠበቀን ። ባየን ፡ ጊዜ ፡ በደስታና ፡ በቅና ፡ መንፈስ ፡ ተቀበለን ። የፀይሐና ፡ የኔ ፡ መተጫጨት ፡ መልካም ፡ አፈጻጸም ፡ እንዳገኘ ፤ የአቶ ፡ ገንዘቤ ፡ አቀባበል ፡ ማስረጃ ፡ ሊሆነኝ ፡ ቻለ ። ሆኖም ፡ ከአንደበቱ ፡ እስክሰማ ፡ በተለይ ፡ የኔ ፡ ልብ ፡ አሁንም ፡ ይደልቃል ። ቁርስ ፡ ስንበላ ፡ ልቤ ፡ እየተጨነቀ ፡ አልዋጥልኝ፡ አለ ። ለመስማት ፡ መቸኮል ፡ ለመናገር ፡ ዝግማለት ፡ እንደሚጠቅም ፡ ዐውቅ ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ ለመስማት ፡ ያለኝ ፡ ስሜት ፡ የተጣደፈ ፡ ሆነ ። የሰው ፡ ባሕርይ ፡ ሆኖ ፡ ልቸኩል ፡ እንጂ ፡ ቁርስ ፡ እንደተነሣ ፡ ከሳምንት ፡ በፊት ፡ ስለተነጋገርነው ፡ የመከባብና ፡ የፀሐይ ፡ መተጫጨት ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ስላገኘ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ይበለን ፡ ሲል ፡ ዜናውን ፡ አበሰረን ።

ከደስታዬ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ የተቀመጥኩበት ፡ ወንበር አልችለኝ ፡ ብሎ ፡ ተንቆራጠጥኩ ። አቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ገለጣውን ፡ ቀጠለ ። የፀሐይ ፡ እናት ፡ ዘነበች ፡ ጥያቄውን ፡ ሳታመነታ ፡ ተቀብላ ፡ ልጅዋ፡ለመከብብ ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ እንድትሆነው ፡ ፈቅዳለች ። ጥያቄውን ፡ በአንድ፡ ጊዜ፡ የተቀበለችው ፡ የመክብብን፡ አባት ፡ አቶ ፡ሕይወትን፡በዝና፡ ታውቅ ፡ ስለነበር ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ወይም፡ የነማን ፡ ወገን ፡ ነው፡ ብላ ፡ ሳትመራመር ፡ ፈቃድዋን ፡ በመግለጥዋ ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ አመሰገንኳት ። ለአቶ ፡ ቡሩክና ፡ ለወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ፀሐይ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ናት ። ለአቶ ፡ ሕይወትና ፡ ለአንቺ ፡ መከብብ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ለወላጆቻቸው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ልጆች ፡ የሆኑ ፡ የትዳር፡ ጓደኛ ፡ ሆነው ፡ በመካከላቸው ፡ ዘር ፡ በማስገኘት ፡ ስማችሁና ፡ ታሪካችሁ ፡ ሳይጠፋ ፡ ይኖራል ።

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ በበኩልዋ ፡ የደረሰባትን ፡ ችግር ፡ ስትገልጥልኝ ፡ ችግራችሁ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆኖ ፡ አገኘሁት ፡ ፀሐይ ፡ አባት ፡ የላትም ። መክብብም ፡ አባት ፡ የለውም ። የወደፊቱን፡ አላውቅም፡እንጂ፡

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ባል ፡ አላገባችም ። አንችም ፡ ባል ፡ አላገባሽም ። ፀሐይ ፡ በዕውቀትና ፡ በትምህርት ፡ ያደገ ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ፡ እንድታገኝ፡ የወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ምኞት ፡ ሲሆን ፤ አንችም ፡ መከብብ ፡ በዚሁ፡ተመሳሳይ ፡ የሆነች ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ እንዲያገኝ ፡ ምኞትሽ ፡ ነው ።

እኔ ፡ የማውቀውን ፡ ያህል ፡ ተመሳሳይ ፡ ችግርና ፡ ምኞት ፡ ያላቸው ፡ ሲገናኙ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜዬ ፡ ስለሆነ ፤ አንቺም፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበችም ፡ ዕድለኞች፡ ናችሁ ። እንግዲህ፡ ስለፍጥምጥማቸውና ፡ ጋብቻቸውም ፡ ቢሆን ፡ በምትፈልጉበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሆን ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ፈቃድዋ ፡ ስለሆነ ፡ ውሳኔው ፡ የናንተ ፡ ነው ፡ አለ ።

ከማዳመጥ ፡ በቀር ፡ አልተናገርኩም ። ብቻ ፡ ደስታ ፡ በውስጤ ፡ ስለበዛ ፡ ከግንባሬ ፡ ወዝ ፡ ይቀዳ ፡ ጀመር ። ይህን ፡ ላሰማኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ፡ አለችና ፡ ፈላጊና ፡ ተፈላጊ ፡በመሠረተ ፡ ሐሳቡ ፡ ከተስማማን ፡ለፍጥምጥሙ ፡ ጊዜ ፡ መስጠት ፡ አያስፈልግም ። በአንድ ፡ ሳምንት ፡ ጊዜ ፡ ቢፈጸም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ብላ ፡ እናቴ ፡ መለሰች ።

እንዳልሽው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፤ ሆኖም ፡ ልነጋገርና ፡ በቀኑና ፡ በሰዓቱ ፡ ተስማምተን ፡ እናንተ ፡ በመምጣት ፡ ፈንታ ፡ መጥቼ ፡ እነግራችኋለሁ ፡ አለንና ፡ ወደቤታችን ፡ በደስታ ፡ ተመለስን ።

ካቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ቤት ፡ ስንወጣ ፡ የጀመርን ፡ እቤታችን ፡ እስክንደርስ ፡ ከናቴ ፡ ጋር ፡ ያልተቋረጠ ፡ የደስታ ፡ ጭውውት ፡ እያደረግን ፡ ተጓዝን ። ከኔም ፡ ይልቅ ፡ የናቴ ፡ ደስታ ፡ የበለጠ ፡ ሆኖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሳነው፡ ነገር፡ የለም ፡ የሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ ላይ ፡ ከተመሠረተ ፡ ያሰቡት ፡ ሁሉ ፡ እንሆ ፡ ይፈጸማል ። አሁን ፡ የሚቀጥለው ፡ ለፍጥምጥሙና ፡ ለሠርጉ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ዝግጅት፡ መጀመር ፡ ነው። የምትጠራቸውን ፡ ሰዎች ፡ ዝርዝር ፡ አዘጋጅ ። በኔም፡ በኩል ፡ የሚጠሩትን ፡ እነግርሃለሁ ፡ አለችኝ ፡ እናቴ ።

ሌሊቱ ፡ የደስታ ፡ ሌሊት ፡ ሆኖ ፡ ቅዠት ፡ በሌለው ፡ ዕንቅልፍ ፡ አሳለፍነው ። ጥዋት ፡ በቁርስ ፡ ላይ ፡ ከናቴ፡ ጋር ፡ ተገናኝተን ፡ ሌሊቱ፡ በቀኑ ፡ ብርሃን ፡ በመለወጡ ፡ አመሰገንን ። ቁርሳችንን ፡ ስንመገብ ፡ ለፍጥምጥሙና ፡ ለሠርጉ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ ዝግጅት ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ በመለዋወጥ ፡ ተስማምተን፡ አቶ ፡ ገንዘቤ፡ የሚመጣበትን ፡ ቀን፡



በጋለ ፡ ናፍቆት ፡ ተጠባበቅን ። በተለያየን ፡ ሳምንት ፡ አቶ ፡ ገንዘቤ ፡ መጣ ። በደስታ ፡ ተቀበልነው ። ፍጥምጥሙ ፡ በሚቀጥለው፡ ሳምንት፡ እሑድ ፡ ጋብቻው ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ እንዲሆን ፡ ከወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ጋር ፡ በመስማማት ፡ መወሰናቸውን ፡ አበሰረን ።

ከምስጋና ፡ ጋር ፡ እናቴ ፡ መስማማቷን ፡ አረጋግጣ፡ ስለዝግጅቱ፡ ንግግሩ ፡ ወደዚያው ፡ ቀጠለ ። ለልጆቻችን ፡ ከኛ ፡ የበለጠ ፡ የሚያስብላቸው ፡ የለም ። ኑሮዋቸውን ፡ ይጠቅማቸዋል ፡ ብለን ፡ የምናምንበትን ፡ እንሥራላቸው ፡ እንጂ ፡ የዕለት ፡ ደስታና ፡ ግርግር ፡ በማድረግ ፡ ቅርስ ፡ ብናሳጣቸው ፡ አይጠቅምም ። ሁለቱም ፡ የሙት ፡ ልጆች፡መሆናቸውን ፡ መርሳት ፡ አይገባንም ። ሁሉም ፡ ነገር ፡ የሚያምረው ፡ በወንድ ፡ ነው ። በሠርግ ፡ ምክንያት ፡ የኛ ፡ ግርግር ፡ መፈለግ፡ ስማችንን፡ ለማስጠፋት ፡ በራሳችን ፡ ላይ ፡ ራሳችን ፡ እንደመፍረድ ፡ የሚያስቆጥር ፡ ነው ። በሥጋ ፡ የሚዛመዱንን ፡ የቅርብ ፡ ወዳጆቻችንና ፡ ቅርብ ፡ ጐረቤታችንን ፡ ብቻ ፡ ጠርተን ፡ ጋብቻቸው ፡ ቢፈጸምና ፡ በሠርግ ፡ የምናጠፋውን ፡ ለልጆቻችን ፡ ትዳር ፡ መቋቋሚያ ፡ ብናደርገው ፡ እወዳለሁ ።

በሐሳቡ ፡ ሁለታችን ፡ ተስማምተን ፤ ተመሳሳይ ፡የሆነ ፡ ዝግጅት ፡ ካላደረግን ፤ ያንዳችን ፡ካንዳችን ፡ የበለጠ፡ እንደሆነ ፤ የወንዱ ፡ ወይም ፡ የሴትዋ ፡ ቤት ፡ በዝግጅት ፡ ይበልጣል ፡ የሚል ፡ የሰዎች ፡ አስተያየት ፡ በላያችን ፡ ላይ ፡ ያርፋል ። እንደግስ ፡ ያልን ፡ እንደሆነ ፡ በድግስ ፡ውድድር ፡ ለልጆቻችን ፡ ቅርስ ፡ እናሳጣለን ፤ ብላ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ሐሳብዋን ፡ አካፍላኛለችና ፤ ያንቺ ፡ ሐሳብ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ አቶ ፡ ገንዘቤ ፡ እናቴን ፡ ጠየቀ ።

እናቴ ፡ መልስ ፡ ሳትሰጥ ፤ ዓይን ፡ ዓይኔን ፡ አየች ፤ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የተቸገረችበት ፡ ለጊዜው ፡ አልገባኝም ፡ ነበር። ዓይንዋ ፡ በኔና ፡ ፀአቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ላይ ፡ ተዘዋወረ ። ምን ፡ ሆነች ፡ ብዬ ፡ ሳስብ ፤ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የተቸገረችበት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ተስማኝና ፡ መጠነኛ ፡ ዝግጅት፡ ለማድረግ፡ ብትስማማ፡ እኔን፡ ያሳዝነው ፡ ይሆናል፡ ብላ ፡ማሰብዋ ፡ ገባኝ ። ይህ ፡ ጥያቄ ፡ እማማን ፡ ሳይሆን ፡ እኔን ፡ ስለሚመለከት ፡ ይቅርታ ፡ አድርጋችሁልኝ ፡ ልናገር ፤ ብዬ ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቅኋቸው ፤ ፈቀዱልኝ ።

ወላጆች ፡ በልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ደስታ ፡ የሚያዩት ፡ መጀመሪያ ፡ በልደት ፡ ልጅ ፡ ሲያገኙ ፤ ሁለተኛ ፡ ሠርገው ፡ ሲድሩ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ወላጆች ፡ በልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ሊያዩ ፡ የሚመኙት ፡ ደስታ ፡ በሠርግ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሊወሰን ፡ አይገባም ። የፀሐይ ፡ እናት ፡ ደኅና ፡ አስተውለዋል ። እማማ ፡ ብትስማሚ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ብዬ ፡ መልስ ፡ ሰጠሁ ።

«እግዚአብሔር፡ቤትን፡ ካልሠራ፤ ሠራተኞች፡በከንቱ፡ ይደክማሉ» እንዳለው ፡ ነቢዩ ፤ የመክብብና፡ የፀሐይ፡ ቤት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸር ነት ፡ ይቋቋማል ።

ስለ ፡ መክብብና፡ ፀሐይ ፡ ጋብቻ ፡ ሐሳባችን ፡ ስለተባበረ ፤ ልጇ ፡ እንዳለው ፡ ሐሳባችሁን ፡ በደስታ ፡ ተቀብዬዋለሁ ።

የዛሬ ፡ ልጆች ፡ የወላጆቻቸውን ፡ ምክር ፡ አይቀበሉም ። ልጇ ፡ መክብብ ፡ ግን ፡ ከፈቃዴ ፡ አይወጣም ። በሠርግ ፡ ድግስ ፡ ከብዙ ፡ ቤተ ሰቦች ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ደርሶባቸዋል ። ለሠርግ ፡ ወጭ ፡ ከማድረግ ፡ ለንብረት ፡ መቋቋሚያ ፡ መስጠት፡ ይመረጣል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የል ጆች ፡ አስተያየት ፡ የተለየ ፡ ነው ። ያለው ፡ ቅርሱን ፡ ጨርሶ ፤ የሌለው፡ ተበድሮ ፡ በመቶና ፡ በሺህ ፡ የሚቆጠር፡ ሰው ፡ ተጠርቶ ፡ በዚያ ፡ መካ ከል ፡ ተሞሽሮ ፡ መታየትን ፡ በመፈለግ ፡ በሌላ ፡ አላስቸግርም ፤ ድብ ልቅልቅ ፡ አድርጋችሁ ፡ ደግሳችሁ ፡ ዳሩኝ፡እያሉ ፡ ቤተሰቦቻቸውን ፡ የሚያሠቅቁና ፡ ዕዳ ፡ የሚያገቡ ፡ አይታጡም ።

መክብብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሠርግ ፡ እንዲሠረግ ፡ ፍላጐት፡ እንዳለውና፡ እንደሌለው ፡ አልተነጋገረንም ። አባቱ ፡ ቢኖር ፡ እንደዚህ ፡ አይሆንም፡ እንዳይል ፤ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡ አልቆጠበም ። ልጇ ፡ በወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ሐሳብ ፡ ስለተስማማ ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሠርግ፡ በመሠረግ ፡ የሚደረገው ፡ ትርምስምስ ፡ ቀረ ። ፍጥምጥሙ ፡ የነገ ፡ እሑድ ፡ ሳምንት ፡ ከሆነ ፤ ለመተጫጫ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ጌጣጌጥ ፡ ይዘጋጅ ። ከሚዜዎቹ ፡ በቀር ፡ ስንት ፡ ሆናችሁ ፡ እንደምትሔዱ ፡ ይወሰን ፡ አለች ፡ እናቴ ።

ይቅርታ ፡ጠየቅሁና ፤ ሦስት ፡ ሚዜዎች ፡ አንድ ፡ የጋብቻ ፡ የውል፡ አባት ፤ ሁለት ፡ እማኞች ፤ ከራሴ ፡ ጋር ፡ ሰባት ፡ እንበቃለን ፡ አልኳ ዋት ።



የመክብብ ፡ ሐሳብ ፡ ምን ፡ ይመስልኻል ፡ ብላ ፡ አቶ ፡ ገንዘቤን ፡ ጠየቀች ፤ በዚህ ፡ አስተያየት ፡ ምን ፡ ይታከላል ፤ መልካም ፡ ነው ፡ አሉ፡ አቶ ፡ ገንዘቤ ።

የጋብቻ ፡ የውል ፡ አባትና ፡ ሁለት ፡ እማኞች፡ መርጠን፤ አቶ ፡ ገን ዘቤ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ። ሳምንቱ ፡ በሳምንት ፡ ተለውጦ ፤ ከፀሐይ፡ ጋር ፡ ፍጥምጥም ፡ የምናደርግበት ፡ ቀን ፡ ደረሰ ። ሚዜዎችና ፡ ሽማግ ሌዎች ፡ መጡ ። ቁርስ ፡ አድርገን ፡ ጉዞዋችንን ፡ ቀጠልን ። ሚዜዎቼ ፡ የሰሙት ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ስለነበር ፤ ከልጅቱ ፡ ጋር ፡ ተዋው ቃችሁ ፡ ጠባይ ፡ ለጠባይ ፡ ተገማምታችኋልን ? ፡ ተብዬ ፡ ተጠየቅሁ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አይቻት ፡ በመልክዋና ፡ በደም ፡ ግባትዋ ፡ ወደድ ኋት ። ሽማግሌ ፡ ልኬ ፡ እናትዋን ፡ ጠየቅሁ ። ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ ዛሬ ፡ ፍጥምጥም ፡ ልናደርግ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ መለስኩ ።

ጊዜው ፡ ያመጣውን ፡ የመተጫጨት ፡ ሥርዓት ፡ አልጠብቅህም፤ ልጅቱን ፡ ከወደድካት ፤ ከናትዋ ፡ በፊት ፡ ወደ፡ ርስዋ ፡ ልከህ ፡ ሐሳብ፡ ለሐሳብ ፡ ብትለዋወጡ ፡ ደግ ፡ ነበር ፡ ተባልኩ ።

የያንዳንዳችን ፡ አስተሳሰብና ፡ አስተያየት ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ከል ጅቱ ፡ ጋር ፡ ተዋውቆ ፡ በሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ቤተሰብዎችዋን ፡ መጠየቅ ፡ ደስ ፡ አይለኝም ። ልጅቱን ፡ አይቶ ፡ መውደድ ፡ ያግቢው ፡ ምርጫ ፡ ነው ። አግቢውን ፡ ቤተሰቦች ፡ ሲቀበሉት ፡ ልጅቱን ፡ መተዋወቅ፡ የተለየ ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።

በአጥር ፡ እየተንጠለጠሉ ፡ መገናኘት ፡ ወይም ፡ አዩኝ ፡ አላዩኝ ፡ እየተባለ፡ በድብቅ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ የሚደረገው ፡ መተጫ ጨት ፡ ለኑሮ ፡ ጓደኛነት ፡ የተፈለገችውን ፡ ወይዘሪት ፡ ሌላ ፡ መን ገድ ፡ ማስተማር ፡ ነው ። የኔን ፡ ባልነት ፡ ዘለቄታ ፡ እንደሌለው ፡ ቤተ ሰቦችዋ፡ ዐወቀው፡ እንድታገባኝ፡ አልፈለጉም። ልጅዎ፡ ወዳኝ፡ እርስዎ፡ እንደ፡ት ፡ ይከለክሉኛል ፡ ብሎ ፡ ወልዶው ፡ ያሳደጉና ፡ አስተምረው ፡ ለቁም ፡ ነገር ፡ ያበቁ ፡ ወላጆችን፡ የሚሰድቡትና ፡ የሚረግሙት፡ ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ውርደት ፡ የሚደርስባቸውም፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ አኳኋን፡ እየተፈ ጸመ ፡ ነው ።

መቼ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ ይቀርና ፡ ወላጆች ፡ መከልከላቸው ፡ሲረጋገጥ፡ ትጠፋለች ። «የወለደ ፡ ያልጸደቀ» ፡ እንደሚባለው ፡ ወላጆች ፡ የሚ ሰማቸውን ፡ ኀዘንና ፡ ብስጭት ፡ ወላድ ፡ ይፍረደው ።

የደረሰች ፡ ልጃገረድና ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ጕረምሳ ፡ በድብቅ ፡ ተጫጭተው ፡ የሚያደርጉት ፡ ግንኙነት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ስለሚያስከትል ፡ አልደግፍም ፡ ራሴም ፡ አላደርገው ፡ ብዬ ፡ ሁለተኛ ፡ መለስኩ ።

ሽማግሌዎች ፡ ከርከራችንን ፡ አዳምጠው ፡ ውይይታችሁ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ። በሕዝባዊ ፡ ሸንጐ ፡ በውይይት ፡ ቀርቦ ፡ የማንኛችሁን ፡ የሚደግፈው ፡ ቢታወቅ ፡ መልካም ፡ ነው ። አስተያየታችንን ፡ ገልጠን ፡ የመከብብ ፡ ሐሳብ ፡ በስንታችን ፡ እንደተደገፈ ፡ እንዳናውቅ ፡ ጊዜው ፡ አይበቃንም ፡ አሉ ።

ይህን ፡ ተወት ፡ አድርገን ፡ እንደተጓዝን ፡ ጠባቂያችንን ፡ አገኘን። ሰላምታ ፡ ሰጥቶ ፡ ተከተሉኝ ፡ አለን ። ልቤ ፡ መታ ፡ ጭንቅ ፡ አለኝ። ከአቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ጋር ፡ ሰላምታ ፡ ከተለዋወጥን ፡ በኋላ ፡ በርሱ ፡ መሪነት ፡ ገብተን ፡ በተዘጋጀልን ፡ ሥፍራ ፡ ተቀመጥን ።

ፀሐይ ፡ ከተፈጥሮ ፡ ቁንጅናዋና ፡ ውበትዋ ፡ ጋር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጣጌጥ ፡ አጊጣ ፡ ብቅ ፡ ስትል ፡ የሁሉም ፡ ዓይን ፡ አረፈባት ። እኔ ፡ ማን ፡ ሰሰትኩላት ። በጐኔ ፡ ቁጭ ፡ ባለች ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የማላውቀው ፡ ልዩ ፡ ስሜት ፡ ተሰማኝና ፡ መላ ፡ አካሌ ፡ ተርበተበተ ።

የመተጫጫው ፡ ውል፡ ተነበበ ። መጀመሪያ፡ ሁለታችን፡ፈርመን፡ የጋብቻ ፡ አባቶችና ፡ እማኞች ፡ ፈረሙ ። የመተጫጫው ፡ ጌጣጌጥ ፡ ቀረበ ። ግብዣው ፡ ቀጥሎ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ሆነ ። ግብር ፡ መልስ ፡ ሆነ። ዘፈን ፡ ተጀመረ ። በአካባቢው ፡ የሚኖሩ ፡ የታወቁ ፡ ተጫዋቾች ፡ ለዛ ፡ ያለው ፡ ባህላዊ ፡ ጨዋታ ፡ እየተቀባበሉ ፡ ተጫወቱ ። ተቀማጩ ፡ ሁሉ፡ ስሜቱ ፡ ተነካ ። ሁሉም ፡ ዘፋኝ ፡ ሆነ ። ግብዣውና ፡ ጨዋታው ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ቀጠለ ። በመካከላችን ፡ ታላቅ ፡ አረጋዊ፡ ስለነበሩ ፡ የፀሐይንና ፡ የኔን ፡ አባት ፡ በማወቃቸው ፡ የነርሱን ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ አስታውሰው ፡ «ዘር ፡ ይመስክር» ፡ እንደተባለው ፡ ዘራቸው ፡ መሰከረ ። ዛሬ ፡ በፍጥምጥማቸው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እንዳደረጋን ፡ በሠርጋቸው ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ ለማድረግ ፡ ያብቃን ። የቅርብ ፡ የሩቅ ፡ ዘመድና ፡ ወዳጅ ፡ ባለበት ፡ ሙሽራዋ ፡ ያደገችበትን ፡ ቤትትታ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ቤትዋ ፡ ሙሽራው ፡ ሲወስዳት ፡ የበዓሉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸምበት ፡ የሠርግ ፡ ቀን ፡ ይጠበቅ ፡ እንጂ ፡ ጋብቻቸው ፡ የተፈጸመው ፡ ዛሬ ፡ ነው ። ፍጥምጥም ፡



ማለት ፡ ካለሞት ፡ ማንም ፡ በማይፍቀው ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ ተሳሰሩ ፡ ማለት ፡ ስለሆነ ፤ ዋናው ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ዛሬ ፡ ተፈጽሟል ።

ቢሆንም ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ በብዛት ፡ ቢተሰበሰበበት ፡ ተመርቃችሁ ፡ ለመሔድ ፡ እንዲያበቃችሁ ፡ የሁላችንም ፡ ምኞት ፡ ነው ፡ ብለው፡ መርቀውን ፡ ተሰነባብተን ፡ ወደቤታችን ፡ ተመለስን ። በቤታችን ፡ ስንደርስ ፡ እናቴ ፡ ባዘጋጀችው ፡ ራት ፡ ላይ ፡ ተገኝተን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ስናደርግ ፡ አመሸን ።

የሠርጋችን ፡ ቀን ፡ ተቃረበ ። ከናቴ ፡ ጋር ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ እየተነጋገርን የሚያስፈልገውን ፡ አዘጋጀን ። አቶ ፡ ገንዘቤ ፡ በድንገት ፡ ስለመጣ ፡ ደነገጥን ። የፀሐይንና ፡ የናትዋን ፡ ደኅንነት ፡ ጠየቅን ፤ ደኅንነታቸውን ፡ ነገረን ። ቀጥሎም ፡ የመጣበትን፡ ምክንያት፡ ለመስማት ፡ ቸኰልን ። ከሠርጉ ፡ በፊት ፡ መከብብ ፡ ለምን ፡ አይመጣም ። ስለዝግጅቱ ፡ ተመካክረን ፡ የሚቸግራቸው ፡ ቢኖር ፡ ብንረዳዳ ፡ ምን ፡ ይከፋል። ሁሉም ፡ የሚቃናው ፡ ተገናኝቶ ፡ በመነጋገር ፡ ስለሆነ ፡ መጥቶ ፡ ብንነጋገር ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል ፡ ብላ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ስለላከችኝ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ የመጣሁ ፡ ስላለ ፡ ከድንጋጤዬ ፡ ተመለስኩ ።

ስለመልካም ፡ ሐሳባቸው ፡ እናመሰግናለን ። ችግር ፡ የለም ፤ ሞልቶዋል ፤ ተርፎዋል ። መከብብ ፡ ያልሄደው ፡ ለኔም ፡ ለርሱም ፡ አስፈላጊነቱ ፡ ስላልተገለጠልን ፡ ነው ። የሠርጋቸው ፡ ቀን ፡ ተቃርቧል ፤ ቢሆንም ፡ ሄዶ ፡ ይጠይቃቸዋል ፡ ብላ ፡ መልስ ፡ ሰጠችው ፡ እናቴ ።

ፀሐይ ፡ ናፍቃኝ ፡ ዓይንዋን ፡ ለማየት ፡ በመቸኰሌ ፡ ነገ ፡ እሄዳለሁ፡ አልኩ ። ነገ ፡ ከመጣህ ፡ እኔም ፡ እጠብቅኻለሁ ፡ ብሎኝ፡ አቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ።

ቀንና ፡ ሌሊቱ ፡ በታምራት ፡ ወደ ፡ ነገ ፡ ቢለወጥ ፡ በወደድሁ ። ቢሆንም ፡ ቀኑ ፡ መሽቶ ፡ ሌሊቱ ፡ ተተካ ። ያለእንቅልፍ ፡ አልጋዬ፡ ላይ፡ ስገላበጥ ፤ ሌሊቱ ፡ አልፎ ፡ ቀኑ ፡ ተተካ ። ማለድ ፡ ብዬ ፡ ተነሣሁ፡ እናቴ ፡ ልጄ ፡ ምነው ፡ በጣም ፡ ማለድክ ? ረፈድ ፡ ሲል ፡ ብትሄድ ፡ ትደርሳለህ ፤ ከቸኰልክም ፡ ቁርስ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በልተህ ፡ ሂድ ፡ አለችኝ ። ቁርሴን ፡ በልቼ ፡ ጕዞዬን ፡ ቀጠልኩ ። እንደደረስኩ ፡ አቶ ፡ ገንዘቤን ፡ አገኘሁትና ፡ ወደፀሐይ ፡ ቤት ፡ ሄድን ። ወይዘሮ ፡ ዘነበችም ፡ በፈገግታ ፡ ተቀበሉን ። እንደተቀመጥን ፤ ፀሐይ ፡ መጣችና ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥታን ፤ በአጠገቤ ፡ ተቀመጠች ። እናትዋና ፡ አቶ ፡ ገንዘቤ፡ ትተውን፡

ወጣ ፡ አሉ ። መተፋፈር ፡ አይቀር ፡ ተፋፈርን ። ቢሆንም ፡ ወንድነቴ ፡ እደፋፍሮኝ ፡ ናፍቆቴን ፡ በመግለጥ ፡ ጭውውት ፡ ጀመርኩ ። ሳቅ ፡ እያለች ፡ ተነጋገርን ። የሠርጋችን ፡ ቀን ፡ በጣም ፡ ራቀኝ። ወራትና፡ ቀናት፡ የሚጠቃለሉ ፡ ቢሆን ፣ አጠቃልላቸው ፡ ነበር ፡ አልኳት ።

የተፈላለግነው ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ አብሮ ፡ ለመኖር ፡ ነው፣ ችግርህን ፡ ችግሬ ፡ ደስታህን፡ ደስታዬ ፡ አድርጌ፡ ሳንለያይ፡ እንድንኖር፡ ከልብ ፡ እንለምነው ፣ በላ ፡ መለሰችልኝ ።

በአስተሳሰብ ፡ በለጥሽኝ ፣ አመሰግናለሁ ። እንደኔ ፡ መቸኰል ፡ ሳይሆን ፡ እንዳንቺ ፡ አርቆ ፡ አስተሳሰብ ፡ ይፈጸምልን ። የቸኰልኩት ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ያለኝ ፡ የፍቅር ፡ ስሜት ፡ የጋለ ፡ ስለሆነ ፣ አብረን ፡ የምናሳልፈው ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ ይታየኛል ፡ አልኳት ።

ፍቅር ፡ የሚገኝ ፡ በአምላክ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። ደስታም፡ የደስታ፡ ምንጭ ፡ ከሆነው ፡ ከርሱ ፡ ነው ፡ የሚገኘው ። በምኞት ፡ መሻትና ፡ በተስፋ ፡ መኖር ፡ የሰው ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። የምኞትና ፡ የተስፋ፡ ፈጻሚና፡ አስፈጻሚ ፡ ርሱ ፡ ነውና፡ ፈቃዱ ፡ ይሁን ፡ ብላ ፡ መለሰችልኝ ።ሌላ ፡ ሳንቀጥል ፣ አቶ ፡ ገንዘቤና ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ወዳለንበት ፡ መጡ ።

የሠርጋችንን፡ ዝግጅት፡ወይዘሮ፡ዘነበች፡አነሡ።ርሳቸው፡ባሳሰቡት፡ መሠረት፡እንደምናዘጋጅ፡ ነገርኳቸው።አንዳንድ ፡ የጐደለ፡ ቢኖር፡ ለማሟላት፡ያላቸውን፡አሳብ፡ገለጡልኝ። የጐደለ እንደሌለ ነገርኳቸው ። ጋብቻችሁ ፡ በሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ቢሆን ፡ ደግ ፡ ይመስለኛል ፡ ምን ፡ ይመስላችኋል ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ። ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ ዓይን ፡ ለዓይን ፡ተያየን ። ይህ፡ በትእዛዝ፡ የሚሆን፡ አይደለም።ሁለቱ፡ ከተስማሙ፡ ቢፈጽሙ፡መልካም፡ ነው ፡ አለ ፡ አቶ ፡ ገንዘቤ ። ተስማምተናል ፡ ብዬ ፡ መልስ ፡ ሰጠሁ ።

በሠርጉ ፡ ቀንስ ፡ ስንት ፡ ሆኜ ፡ እንደምመጣ ፡ ጠየቅሁ ። ከኻያ ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ሆናችሁ ፡ መምጣታት ፡ ትችላላችሁ ፡ አሉኝ ። ኻያ ፡ ሆነን ፡ እንመጣለን ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ አልፈልግም ፡ አልኳቸው ፡ ተስማሙ ። አቶ ፡ ገንዘቤ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። እናንተ ፡ ተጫወቱ ፣ እኔ ፡ ዓረፍ ፡ ልበል ፡ ብለው ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ወደ፡ መኝታ፡ ቤት ፡ ገቡ።

ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ መተፋፈር፡ ቀረ ። ጨዋታችንን ፡ ቀጠልን ። ጋብቻችን ፡ በሥጋ ፡ ወደሙ ፡ እንዲሆን ፡ እናቴ ፡ ላደረገችው ፡ ጥያቄ ፡ ተስማምተናል ፡ ያልከው ፣ ከኔ ፡ ጋር ፡ አልተነጋገርን፣ ሐሳቤን ፡ እንዴት ፡ አወቅኸው ፡ ? ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ጠየቀችኝ ።



ያንቺን ፡ ተወዳጅ ፡ ጠባይ ፡ እናትሽ ፡ ባያውቁ ፣ አሳቡን ፡ እንዴት ፡ ያመነጩታል ? ያንድን ፡ ሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ ለማወቅ ፡ ደቂቃ ፡ ይበቃል ። ጋብቻችንን ፡ የአብርሃምና ፡ የሣራን ፡ ጋብቻ ፡ እንዲያደርግልን ፡ የራቀ ፡ ምኞት ፡ሲኖርሽ ፣ በሥጋ ፡ ወደሙ ፡ አልጋባም ፡ እንደማትይ ፡ በማመን ፣ ቃሌ ፡ ቃልሽ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ መልስ ፡ ሰጠሁ ። አጠፋሁ ፡ እንዴ ? አልኳት ።

ሐሳብህን ፡ ለማወቅ ፡ ያህል ፡ ጠየቅሁህ ፣ ስለሰጠኸኝ ፡ መልስ ፡ አመሰግንሃለሁ ፣ አለችና ፡ ጭውውታችንን ፡ እንደቀጠልን ፡ ቀኑ ፡ ለምሽቱ ፡ ተራውን ፡ ሊለቅ ፡ ስለተቃረበ ፣ተሰናብቼ ፡ ወደቤቴ ፡ ተመለስኩ። ከቤት ፡ ስደርስ ፣ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለእናቴ ፡ አስረዳኋት ። ርስዋም ፡ ደስ ፡ አላት ።

ያ ፣ በናፍቆት ፡ የምንጠባበቀው ፡ ሠርግ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ቀን ፡ ደረሰ ። በዘመድና ፡ በወዳጅ ፡ ቤታችን ፡ ደምቆ ፣ የሠርግ ፡ቤት ፡ መሰለ ። ዳሱ ፡ በስፋት ፡ ተሠራ ። አታሞው ፡ ድልቅ ፡ ድልቅ ፡ እያለ ፡ ዘፈን ፡ ተጀመረ ። ዝግጅቱ ፡ በብዙ ፡ ሰው ፡ ተከናወነ ። ግብዣው ምሳና ፡ ራት ፡ ስለነበረ ፣ አስተናባሪዎች ፡ ሥራውን ፡ ተከፋፈሉት ።

የኔ ፡ ተከታይዎች ፡ ማልደው ፡ ተገኙ ። ሙሽራነቴን፡ የሚለይ፡ የሀገር ፡ ልብስ ፣ ንጣቱ ፡ በረዶ ፡ የመሰለ ፡ ሲሆን ፣ ከላይ ፡ የደረብኩት ፡ ድርብ ፡ ጃኖ ፡ በጃኖው ፡ ላይ ፡ ካባ ፡ ስለነበር ፣ ግርማ ፡ ሞገስ ፡ ሰጠኝ ። ሚዜዎቼም ፡ ከኔው፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ለብሰዋል ። የለበስ ነው ፡ ልብስ ፡ ብዙዎችን ማረከ ፣ ተመሰገንበት ።

ቁመታቸው ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ስናር ፡ በቅሎዎች ፡ ተቀምጠን ፣ ጉዞአችንን ፡ ቀጠልን ። ብዙዎች ፡ ተከታይዎች ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። በቅሎዎች ፡ ታስረው ፡ የተቀለቡና ፡ ለዚሁ ፡ ቀን ፡ በመዘጋጀታቸው ፣ እየሠገሩ ፡ ደረስን ። ከጫንናቸው ፡ ብልጫ ፡ ያላት ፡ በቅሎ ፡ ለፀሐይ ፡ ተዘጋጅታ ፣ ወደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሄድን ። ቀሳውስቱ ፡ ተቀበሉን ። በተዘጋጀልን ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ እንደሆን ፡ የተክሊሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ጸሎት ፡ ተጀምሮ ፡ እንዳለቀ ፣ የቅዳሴው ፡ ጸሎት ፡ ቀጠለ ። ሲፈጸም ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ከተቀበልን፡ በኋላ ፣ ቀሳውስቱ ፡ በመዝሙር ፡ ሸኝተውን ፡ በፀሐይ ፡ ቤት ፡ በተዘጋጀው ፡ ቁርስ ፡ ላይ ፡ ተገኘን ።

የምሳ ፡ ሰዓት ፡ እስኪደርስ ፡ በዚያው ፡ ቆየን ። በስድስት ፡ ሰዓት ፡ የተጠራው ፡ እንግዳ ፡ ሁሉ ፡ ገባ ። እኛም ፡ በሚዜዎቻችንና ፡ በእድምተኞቻችን ፡ ታጅበን ፡ ስንገባ ፣ ተጨበጨበልን ። በተዘጋጀልን ፡

ከፍተኛ ፡ ሥፍራ ፡ ስንቀመጥ ፤ ግብዣው ፡ ተጀመረ ። የታወቁ ፡ ተጫዋቾች ፡ በመሰንቆና ፡ በክራር ፡ እየታጀቡ ፡ ዘፈኑን ፡ ሲያንቆረቁሩት ፡ የተጋባዡ ፡ ዓይን ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ አረፈ ። ሠርጋችን ፡ እውነተኛ ፡ ሠርግ ፡ ሆነ ። ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ዘፈኑ ፡ ተሟሟቀ ፡ ከተጋባዥዎቹ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከዘፋኞዎች ፡ ጋር ፡ እየዘፈኑ ፡ ጨዋታውን ፡ የበለጠ ፡ አሟሟቁት ።

ሚዜዎቹና ፡ እድምተኞቻችን ፡ በጨዋታው ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ሲዘፍኑና ፡ ሲጨፍሩ ፡ የተጋባዡ ፡ ስሜት ፡ ተቀሰቀሰ ።

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ደስ ፡ አላቸው ። በእውነትም ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ። ከእድምተኞቻችን ፡ በዕድሜ ፡ ከሁሉም ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ አረጋዊ ፡ ወደኔ ፡ መጥተው ፤ ልጄ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ በመጠኑ ፡ ሲሆን ፡ ደግ ነው ። ደስታውን ፡ የጤናና ፡ የሕይወት ፡ ያድርግልን ። ይብቃን ፤ ወደ ቤታታችን ፡ እንሂድ ፤ ጊዜውም ፡ መሽትዋል ፡ አሉኝ ።

ለፀሐይ ፡ አማከርኳት ፤ ርስዋም ፡ ተስማማች ። ፈቃዳቸው ፡ ሆኖ ፡ እንዲያሰናብቱን ፤ በተለይ ፡ ለተመደበልን ፡ ጋባዥ ፡ መልእክት ፡ ላክን ። ፈቃዳቸው ፡ ሆነ ። ዘፈኑ ፡ ጋብ ፡ አለና ፡ ለመነሣት ፡ ስንዘጋጅ ፤ በፍጥምጥማችን ፡ የመረቁና ፡ በሀገር ፡ የታወቁ ፡ አረጋዊ ፤ ምንጨ ፡ ደስታ ፡ ሆኖ ፤ የደስታ ፡ አዝማች ፡ ዘፈን ፡ ነው ። ደስታም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ ይገኛል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የሠርግ ፡ ደስታ ፡ ከሁሉም ፡ ላቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ወላጆች ፡ ከአብራክ ፡ ሥጋቸው ፡ የተከፈሉ ፡ ልጆቻቸው ፡ ከሕፃንነት ፡ ወራት ፡ አቅመ ፡ አዳም ፡ እስኪደርሱ ፡ ሳይለዩ ፤ አቅመ ፡ አዳም ፡ ደርሰው ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ማየታቸው ፡ ልዩ ፡ ደስታቸው ፡ ነው ። አሳድገውና ፡ አስተምረው ፡ በመጨረሻ ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ባለበት ፤ እንደ ዚህ ፡ ሠርጋቸውን ፡ ሲያዩ ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ ይሰማቸዋል ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፤ ቀን ፡ ከሌሊት ፡ ቢዘፈን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ይህ ፡ ዕድል ፡ ለሁሉም ፡ አይሰጥ ። የሙሽራዋና ፡ የሙሽራው ፡ አባት ፡ ይህን ፡ ደስታ ፡ ሊያዩ ፡ አልቻሉም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዘር ፡ ይመስክር ፡ እንደተባለው ፡ ደግነታቸው ፡ መስክሮ ፤ ልጆቻቸው ፡ ለወግና ፡ ለቁም ፡ ነገር ፡ በቅተው ፡ ዐየናቸው ። ስለዚህ ፡ ጋብቻችሁን ፡ የተባረከ ፡ ያድርግላችሁ ፡ ብለው ፡ ሲጨርሱ ፡ ጉልበት ፡ ስመን ፡ ወጣን ።

ተጋባዡ ፡ በዘፈንና ፡ በሆታ ፡ ሸኘን ። በሚዜዎቻችንና ፡ በእድምተኞቻችን ፡ ታጅበን ፤ ከቤታችን ፡ ደረስን ፤ በቤታችንም ፡ ዘፈኑ ፡ ተሟሙቆ ፤ ሠርጋችን ፡ እውነተኛውን ፡ የሠርግ ፡ ጠባይ ፡ አሳየ ። የተያዘው ፡ ዳቦ ፡ ተቆርሶ ፤ እናቴ ፡ የፀሐይን ፡ የምራት ፡ ስም ፡ «ኮከቤ» ፡ ብላ ፡ አወጣችላት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደእልፍኝ ፡ ገብተን ፡ ጥቂት ፡ ዐረፍ ፡ አልን ። የራት ፡ ሰዓት ፡ ደርሶ ፡ ራት ፡ የተጠሩት ፡ እንግዶች ፡ ገቡ ። በሥርዓት ፡ አጋጊጠንና ፡ በሚዜዎቻችን ፡ ታጅበን ፤ ስንገባ ፡ በጭብጨባ ፡ ተቀበሉን ።

ግብዣው ፡ ቀጠለ ። ተጫዋቾች ፡ በማኅበር ፡ ሆነው ፡ በመሰንቆና ፡ በክራር ፡ እየተመሩ ፡ ለተጋባዡ ፡ ጨዋታ ፡ አሳዩ ። ተጋባዡ ፡ ዓይኑ ፡ ልቡናውን ፡ በተጫዋቹ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጐ ፡ እየተመለከተ ፡ ሲጋበዝ ፡ አምሽቶ ፤ ከሌሊቱ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ የግብዣውና ፡ የጨዋታው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆኖ ፤ ወደእልፍኛችን ፡ ገባን ።

ሚዜዎቹ ፡ ማለድ ፡ ብለው ፡ የምሥራች ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ፀሐይ ፡ እናት ፡ ቤት ፡ ሄዱ ። ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ ሰብስበው ፡ እንደ ፡ ተቀበልዋቸው ፡ ሚዜዎቹ ፡ «ብር ፡ አምባር ፡ ሰበረልሽ ፤ ወንዱ ፡ ልጅሽ ፡ ጫጉላሽ ፡ አብቧል ፡ ዛሬ» ፡ እያሉ ፡ በመወዝወዝ ፡ በዘፈኑበት ፡ ሰዓት ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሽልማት ፡ ሚዜዎቹን ፡ ሸልመዋቸው ፡ ኖሮ ፡ ሽልማቱን ፡ ዐየነው ። በሽልማቱ ፡ እንኳን ፡ ተሸላሚዎቹ ፡ ተመልካቹ ፡ ደስ ፡ አለው ።

ሰባት ፡ ቀን ፡ ተሞሸርን ፡ ግብዣውም ፡ ጨዋታውም ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቀጠለ ። በስምንት ፡ ቀናችን ፡ መልስ ፡ ተጠርተን ፡ ወደ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ቤት ፡ ሄድን ። ዝግጅቱ ፡ ከሠርጉ ፡ ዕለት ፡ የማያንስ ፡ ሆነ ። እናቴም ፡ ሄዳለች ። ወይዘሮ ፡ ዘነበችም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሞሸሩን ። በአራተኛው ፡ ቀን ፡ ወደቤታችን ፡ ተመለስን ። እናቴ ፡ የቤት ፡ ማያ ፡ ብላ ፡ በሳምንቱ ፡ ጠርታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግብዣ ፡ አደገረች ። ወይዘሮ ፡ ዘነበችም ፡ ነበሩ ። እናቴና ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ተቀራረቡ ። ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ በመለዋወጥ ፡ ተለማመዱ ። በሁለቱ ፡ መቀራረብ ፡ ደስ ፡ አለን ። ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሰንብተው ፡ በአስምተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመለሱ ።

መልሱ ፡ ባለማቋረጥ ፡ ቀጠለ ። ሚዜዎቻችን ፡ የጋብቻ ፡ የውል ፡ አባቶቻችን ፤ ቤተ ፡ ዘመድና ፡ ቅርብ ፡ ወዳጆቻችን ፡ እየተቀባበሉ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ መልስ ፡ እየተጠራን ፡ ዓለምን ፡ ዐየናት ፤ ግን ፡ አልጠገብናትም ።

# ጠ ቢ ባ ን ፡

የቀድሞ ፡ ጠቢባን ፡ ሊቃውንቱ ፡ ሁሉ ፤
ዛሬም ፡ በፊንታቸው ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፤
ክቡር ፡ ነው ፡ ጋብቻ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

በአብርሃም ፡ በሣራ ፡ ቅዱስ ፡ ንጹሕ ፡ ፍቅር ፤
ተገልጧል ፡ እነሆ ፡ የጋብቻ ፡ ምሥጢር ።

ነበሩ ፡ በኋላም ፡ ብዙ ፡ ተከታይዎች ፤
ኢያቄም ፡ ወሐና ፡ ሕግ ፡ ጠባቂዎች ።

ከነዚህ ፡ ብሩካን ፡ የተገኘች ፡ ፍሬ ፤
ላለም ፡ ቤዛ ፡ አስገኘች ፡ ብሎ ፡ በዝማሬ ፤

ክርስቲያኑ ፡ ሁሉ ፡ እያመሰገነ ፤
ዘላለም ፡ ይኖራል ፡ በዚህ ፡ እያመነ ።

የጋብቻችን ፡ ሕግ ፡ ጥንትም ፡ መሠረቱ ፤
ባንድ ፡ እንዲረጉ ፡ ነው ፡ ሰዎች ፡ እስኪሞቱ ።

አልቀረም ፡ ሥራቱ ፡ ቀጥልዋል ፡ በነበር ፤
ባንዳንዱ ፡ ዘንዳ ፡ ግን ፡ አልተገኘም ፡ ፍቅር ።

አንዳንዱ ፡ የሚያስብ ፤ የሚያሰላስለው ፤
የገንዘብን ፡ ፍቅር ፡ ከሚስቱ ፡ አብልጦ ፡ ነው ።

ግን ፡ ደግሞ ፡ ለፍቅር ፡ ጥንቱን ፡ የታደሉ ፤
ለጋብቻ ፡ ገና ፡ በሐሳብ ፡ ፅንስ ፡ ሳሉ ፤
ለንብረት ፡ ለትዳር ፡ ተግተው ፡ ይሠራሉ ።

ተምሯል ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እጅግ ፡ ደግ ፡ ሰው ፤
የዳበረ ፡ ንብረት ፡ ብዙም ፡ ባይኖረው ፤
በኑሮ ፡ መካከል ፡ ፍቅር ፡ የሚያውቅ ፡ ነው ።

የምትል ፡ ሚስት ፡ ያለው ፡ ያድርበታል ፡ ተስፋ ፤
ይጠግባል ፡ ሕይወትን ፡ ንብረቱ ፡ እየሰፋ ።

አይጠቅምም ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ፍቅር ፡ ብቻውን ፤
ማግባት ፡ ይሻለኛል ፡ ባለጸጋውን ።



ቢሆን ፡ ይሆነኛል ፡ ቢቀርም ፡ ይቅር ፤
እካፈለዋለሁ ፡ ሀብቱን ፡ በስፍር ።

ወይም ፡ ይሞትና ፡ በውርስ ፡ አስቀራለሁ ፤
በብቸኛ ፡ ኑሮ ፡ እንቀባረራለሁ ።

እያሉ ፡ በምኞት ፡ የሚወናበዱ ፤
ከፍቅርም ፡ ይልቅ ፡ ገንዘብ ፡ የወደዱ ፤
አሉ ፡ በየቦታው ፡ ሳያብዱ ፡ ያበዱ ።

ናትና ፡ አገሪቱ ፡ ገና ፡ የምትለማ ፤
ወጣቱ ፡ ለኑሮ ፡ ለትዳር ፡ ፊለማ ፡

ይነሣ ፡ ይታጠቅ ፡ ወኔውን ፡ ኮስትሮ ፤
መብዛት ፡ መዋለድም ፡ በሕገ ፡ ተፈጥሮ ፤
ከፍጥረታት ፡ ጋራ ፡ የኖረ ፡ ነው ፡ አብሮ ።

## ክፍል ፡ ፬ ፡

# የልጅና ፡ የሀብት ፡ ጸጋ ፡

ፀሐይ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያደገች፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የቤት ፡ ባልትና ፡ የሠለጠነች ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ ስለሆነች ፤ የቤታችን ፡ ይዞታ ፡ ልዩ ፡ ሆነ ። ደስ ፡ አለኝ ፤ እናቴም ፡ ደስ ፡ አላት ። የሚጠሉን ፡ ቀኑ ፤ የሚወዱን ፡ ደስ ፡ አላቸው ። በፀሐይና ፡ በኔ ፡ መካከል ፤ ርስዋ ፡ ለኔ ፡ ሳሳች ፤ እኔ ፡ ለርስዋ ፡ ሳሳሁ። ውዬ ፡ እስክገባ ፡ ደኅና ፡ አገኛት ፡ አልመሰለኝ ፡ አለ ። ልቤ ፡ ተጨነቀ ። ርስዋም ፡ እንደዚሁ ፡ ሆነች ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ እንዳለን ፡ በተጋባን ፡ በዓመቱ ፡ ፀነሰች ። በፍቅራችን ፡ መካከል ፡ የበለጠ ፡ የሚያፋቅርና ፡ የሚያስተሳስር ፡ ልጅ ፡ አግኝተን ፤ ዓይናችንን ፡ በዓይናችን ፡ ማየት ፡ ደስ ፡ ሲለኝ ፤ በርግዝና ፡ ወራት ፡ በሚሰማት ፡ የጤና ፡ ማጣት ፡ ሐሳብ ፡ አደረብኝ ።

የኔን ፡ ማሰብ ፡ እያየች ፤ ቢያማትም ፡ ትችለዋለች ፡ እንጂ ፡ አመመኝ ፡ አትልም ። በርግዝና ፡ ወራት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሕመም ፡ አይጠፋም ። ለክፉ ፡ ስለማይሰጣት ፤ አታስብ ፤ ሴቶች ፡ በርግዝና ፡ ወራት ፡ ሆደ ፡ ባሻ ፡ ይሆናሉ ። የሚታያቸው ፡ ሞት ፡ እንጂ ፤ በደኅና ፡ ተገላግለው ፡ የልጅ ፡ አበባ ፡ የሚያዩ ፡ አይመስላቸውም ። በማያበሳጨው ፡ ተበሳጭተው ፡ ያበሳጫሉ ። በተቻለ ፡ መጠን ፡ የሚያስደስታቸውን ፡ እየፈለጉ ፡ ለማስደሰት ፡ መጣር ፡ እንጂ ፡ መቆጣት ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ይጥላቸዋል ። አንተም ፡ ለኮከቤ ፡ ከልብ ፡ የምታስብላት ፡ መሆንህን ፡ ባውቅም ፤ በሐሳብ ፡ ራስህን ፡ ሳትጎዳ ፡ የሚያስደስታትንና ፡ የምትወደውን ፡ በማድረግ ፡ ጠብቃት ፡ አለችኝ ፡ እናቴ ።

በእናቴ ፡ ምክር ፡ ለመጠቀም ፡ ሞከርኩ ። በሙከራዬ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አገኘሁ ። ፀሐይ ፡ ከፀነሰች ፡ ከአምስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ እየቀለላት ፡ ደኅና ፡ ሆነች ። ሳታውቀውና ፡ ሳላውቀው ፤ ዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ገባ ። ያ ፡ የምጥ ፡ ቀን ፡ መጣ ። ከርስዋ ፡ ይልቅ ፡ እኔ ፡ ተጨነቅሁ ። ቀኑ ፡ ሳይደርስ ፡ እናቴን ፡ ሩጬ ፡ እጠራለሁ ። ስታያት ፡ ደኅና ፡ ነች ። ቀኑን ፡ ስቈጥረው ፡ ገና ፡ ነው ። ልጄ ፡ ምን ፡ ሆንህ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ የሚገፋ ፡ ይመስልሃል ? አይምሰልህ ፤ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ሁሉም ፡

ይመጣል ። ያለጊዜው ፡ የሚመጣ ፡ የለም ። መታከት ፡ ነው ፡ አለችኝ ። ወድጄ ፡ አይደለም ፣ ፀሐይ ፡ ዓይንዋን ፡ ሳያት ፡ ከዓይኔ ፡ የምትጠፋ ፡ ትመስለኛለች ። የሚያያት ፡ ይፍረደኝ ። ሰው ፡ ሆና ፡ ትፈጠር ፡ እንጂ ፣ ቁንጅናዋ ፣ ውበትዋ ፣ ደምግባትዋ ፣ አቋቋሟ ፣ አካሄድዋ ፡ በዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ስትታይ ፡ ስለምታሳሳ ፣ ሰሰችኩላት ፣ ሁሉም ፡ በጊዜው ፡ ይመጣል ፡ እንዳለች ፡ እናቴ ፣ ቀኑን ፡ ቆጥሮ ፡ ምጥ ፡ ከሌሊቱ ፡ በስምንት ፡ ሰዓት ፡ መጣ ። አሞኛል ፡ ብላኝ ፡ አታውቅም ። ገፍቶ ፡ መጥቶ ፡ ስላስጨነቃት ፡ ዛሬ ፡ አሞኛል ፡ እማማን ፡ ጥራልኝ ፡ አለችኝ ። እናቴን ፡ እማማ ፡ ስለምትላት ፡ እናቴን ፡ ልጠራ ፡ ስወጣ ፣ እናቴ ፡ ቀንዋን ፡ ቈጥራ ፡ ትጠባበቅ ፡ ስለነበር ፣ ድምጣችንን ፡ ሰምታ ፡ ከቤትዋ ፡ ወጥታ ፡ ስትመጣ ፡ ተገናኘን ።

ሰላምታ ፡ ሳልሰጣት ፣ እማማ ፡ ፀሐይን ፡ አመማት ፣ ምን ፡ ይሻላል ፡ አልኳት ። ዕንባም ፡ አነቀኝ ። የታመምከው ፡ አንተ ፡ ነህ ፣ ሲነግሩህ ፡ አትሰማም ፣ ደኅና ፡ ናት ፡ አልኩህ ፡ አለችኝ ። በማናቸውም ፡ ሰዓት ፡ ስልክብዎ ፡ ቶሎ ፡ እንዲመጡ ፡ ብዬ ፡ ሰሞኑን ፡ ነግሬያቸዋለሁ ። ይቶት ፡ እግዜሯን ፡ ጥራቸው ፡ አለችኝ ።

በዚያን ፡ ቀን ፡ ጨለማውን ፡ እንደቀን ፡ ቈጥሬው ፡ በሩጫ ፡ ሄጄ ፡ ጠራኋቸው ። በጨለማ ፡ መንገድ ፡ በመቋሚያቸው ፡ መርኰዝ ፡ እያሉ ፡ በቀስታ ፡ ሲሄዱ ፣ እባክዎ ፡ ይቶት ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ይሂዱ ፡ እያልኩ ፡ አጣደፍኳቸው ። ርሳቸው ፡ ግን ፡ አካሄዳቸውን ፡ መለወጥ ፡ አልቻሉም ። በተለመደው ፡ አካሄዳቸው ፡ ቀስ ፡ አሉ ። ቢቸግረኝ ፡ ይቶትን ፡ ልዘልዎትና ፡ ቶሎ ፡ ይገፍዎት ፡ ልድረስ ፡ አልኳቸው ።

ልጄ ፡ ረጋ ፡ በል ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ። እንደርሳለን ፡ አሉኝ ። መቼ ፡ ዐይዋት ፣ አሚታል ፡ አልኳቸው ። ልጄ ፡ ምጥ ፡ መሆኑ ፡ ቀረ ። ፈቃድህ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መለመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በፍጡር ፡ ሩጫ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ አይድንም ፡ እንዳሉኝ ፡ ደረስን ።

ፀሐይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ትጮኻለች ፣ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ መሬትዋ ፡ ጠበበችኝ ፣ የምደርስበት ፡ አጣሁ ። ከቤቴ ፡ ወደውጭ ፣ ከውጭ ፡ ወደ ቤት ፡ በማለት ፡ ፀጥታ ፡ አጣሁ ። ሁኔታዬን ፡ እናቴ ፡ አይታለችና ፡ ወደ አለሁበት ፡ መጣ ፡ እያለች ፡ ደኅና ፡ ናት ። አሁን ፡ ደኅና ፡ ትገላገላለች ። አይዞህ ፡ ትለኛለች ።



እናቴ ፡ አይዞህ ፡ የምትለኝ ፡ እኔን ፡ ለማጽናናት ፡ እንጂ ፣ ፀሐይ ፡ ተሽልዋት ፡ አይደለም ፣ በማለት ፡ ጭንቀቴ ፡ አልተከፈለም ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አሰብኩ ። ብቻዬን ፡ በነበርኩበት ፡ ወቅት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሐሳብና ፡ ጭንቀት ፡ አልደረሰብኝም ። በዕድሜ ፡ ልጅነት ፡ ቢኖረኝም ፣ አባቴ ፡ ታሞ ፡ ከሞት ፡ ሲደርስ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አልተጨነቅሁም ፣ የሞተ ፡ ሰው ፡ እንደማይመለስ ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ዐውቃለሁ ። የሚስት ፡ ልዩ ፡ ነው ፣ ሚስት ፡ ማግባት ፣ ልጅ ፡ መውለድ ፣ ለደስታ ፡ ይመስለኝ ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ለሐሳብና ፡ ለጭንቀት ፡ እንጂ ፡ ለደስታ ፡ አይደለም ። ሐዋርያው ፡ «ከማግባት ፡ አለማግባትን ፡ እመርጣለሁ» ያለው ፡ ትክክለኛ ፡ አስተያየት ፡ ነው ፡ እያልኩ ፡ ራሴን ፡ በራሴ ፡ ሳነጋግረው ፣ ደስ ፡ ይበልህ ። ሴት ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፣ ብላ ፡ ዕልልታዋን ፡ እያቀለጠች ፡ እናቴ ፡ ዕቅፍ ፡ አድርጋ ፡ ሳመችኝ ። ጭንቀት ፡ በገባበት ፡ ልቤ ፡ ደስታ ፡ ተተካ ።

ይቶት ፡ እግዜሯ ፡ ሁሉንም ፡ በሚገባ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ገብተህ ፡ ዕያት ፡ አሉኝ ፣ ገብቼ ፡ ዐየኋት ። ልጅቷንም ፡ እያት ፡ አሉኝ ። የፀሐይን ፡ ጭንቀት ፡ በማስታወስ ፡ አላየኋትም ።

እናቴ ፡ ፀሐይን ፡ እንደኔ ፡ አድርጋ ፡ ትወዳታለች ። አንቺ ፡ ገና ፡ በካር ፡ ወላድ ፡ ነሽ ። ዛሬ ፡ ከተጐዳሽ ፡ ሰውነትሽ ፡ አይመለስም ። በሚገባ ፡ መታረስ ፡ አለብሽ ፡ እያለች ፣ በጥንቃቄ ፡ መገበቻት ። ለኔም ፡ ተርፎኝ ፡ ወፈርኩ ።

ፀሐይ ፡ በረታች ፣ የተወለደችው ፡ ሕፃን ፡ ፋፋች ፣ በሰማንያ ፡ ቀን ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ ተቀበለች ። እናቴ ፡ ስሟን ፡ ቡርክት ፡ አለቻት ፣ ሰው ፡ ከተወለደበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፣ ቀንና ፡ ሌሊቱ ፡ ሲለዋወጥ ፡ ዕድሜውም ፡ እየጨመረ ፡ ስለሚሄድ ፣ ቡርክት ፡ አደገች ፣ ዓመት ፡ ስለሆናት ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ባሉበት ፡ ልደትዋን ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ አከበርን ። ማጫወት ፡ ስለጀመረች ፣ ያ ፡ በፀሐይ ፡ ምጥ ፡ የነበረ ፡ ጭንቀት ፡ ከፊቴ ፡ ጠፋ ። ይህ ፡ ዓለም ፡ ምንኛ ፡ አታላይ ፡ ነው ፣ ደስታውን ፡ ወስዶ ፡ መከራውንና ፡ ኀዘኑን ፡ ሲያመጣው ፡ መድረሻ ፡ ያሳጣል ። ያን ፡ አሳልፎ ፡ ደስታውን ፡ ሲተካ ፣ ሁሉም ፡ ይረሳና ፡ በዕለታዊ ፡ ደስታ ፡ ይማርካል ፣ የሰው ፡ ኑሮ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፣ ሰው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ አጫዋች ፡ ቲያትር ፡ ነው ።

የልጅ ፡ አበባ ፡ አግኝተን ፡ ዓይናችንን ፡ በዓይናችን ፡ እያየን ፡ ደስ ብሎን ፡ ስንኖር ፣ ሀብታችን ፡ ሰፋ ፣ የምንሠራው ፡ የግብርና ፡ የንግድ ፡ ሥራችን ፡ ተቃና ፣ በቤታችን ፡ በረከት ፡ ወረደ ። ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ ያለን ፡ ፍቅር ፡ ለቤታችንና ፡ ለአካባቢያችን ፡ የደስታና ፡ የሰላም ፡ ምንጭ ፡ ሆን ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እናቴ ፡ መክብብ ፡ ሲመጣ ፡ ላኪብኝ ፡ ብላ ፡ ለፀሐይ ፡ ነግራት ፡ ኖሮ ፣ ከሥራ ፡ ስገባ ፡ ነገረችኝ ፡ ሄድኩ ። እንደደረስኩ ፣ እንደምን ፡ ዋልሽ ፡ እማማ ፡ ብዬ ፡ ሳምኳት ፣ ሳመችኝ ፡ ኮከቤ ፡ ባለችበት ፡ የምንነጋገረው ፡ ጉዳይ ፡ ስላለ ፡ እንሂድ ፡ አለችኝ ። ሄድን ፣ ልጄ ፡ ኮከቤ ፡ አለች ፣ ርስዋም ፡ እመት ፡ አለች ፣ የምነግራ ችሁ ፡ ታላቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አለና ፡ አዳምጡኝ ፡ አለች ።

ሐሳብዋን ፡ ከመግለጥዋ ፡ በፊት ፡ ደነገጥን ፣ ምን ፡ አዲስ ፡ ነገር፡ የማናውቀው ፡ ተፈጠረ ፡ ብለን ፡ ሠጋን ፣ እንዳለችው ፡ በፀጥታ ፡ ሆነን፡ የምትናገረውን ፡ ስንጠባበቅ ፣ ልጆቼ ፡ ሆይ ! የምነግራችሁን ፡ አዳ ምጣችሁ ፣ ሐሳቤን ፡ እንድትቀበሉ ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ ፡ አለቺና ፡ ንግግርዋን ፡ ቀጠለች ።

መክብብ ፡ ለሐሳቤ ፡ እንግዳ ፡ አይሆንም ፣ ያውቀዋል ፣ ለአንቺ ፡ እንግዳ ፡ ይሆንብሽ ፡ ይሆናል ። ሰው ፡ የሚኖርበትን ፡ ዘመን ፡ የማያ ውቅ ፡ እንግዳ ፡ ፍጥረት ፡ ነው ፣ ዛሬ ፡ አለ ፣ ነገ ፡ ግን ፡ የለም ፣ ላጭር ፡ ወይም ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ፡ የሚኖርበትን ፡ አያውቅም ። ሆኖም ፡ የሰው፡ ኑሮ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው ። ትዳር ፡ ይዞ ፡ በመረዳ ዳት ፡ እየተደጋገፉ ፡ የሚኖሩት ፡ መልካም ፡ ኑሮ፡ ነው ። ትዳር ፡ ሳይዙ፣ በብቸኝነት ፡ የሚኖሩ ፡ አሉ ። ትዳር ፡ ይዘው ፡ ልጅ ፡ ወልደው ፡ ብዙ ፡ ቤተሰቦች ፡ ከሚያስተዳድሩ ፡ የበለጠ ፡ ይደክማሉ ።

ለዕለት ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ ሲሉ ፡ በሴት ፡ አዳሪነት ፡ ውሃ ፡ ሸጠው ፡ በአላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ተደፍረውና ፡ ተዋርደው ፡ የሚኖሩ ፡ አሉ ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያና፡ዕውቀታቸው ፡ ሠርተው ፡ የሚኖሩ ፡ ትዳር ፡ ባለመያዛቸው ፣ ሴትነታቸው ፡ እያስደፈራቸው ፡ የሚኖሩ ፡ አሉ ።

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ፡ የተመሰቃቀለ ፡ በመሆኑ ፣ ሰዎች ፡ እንደየ ተሰጣቸው ፡ ዕድል ፡ ይኖራሉ ። ቢሆንም ፡ ትዳር ፡ ይዞ ፡ የቤተሰብ ፡ ኃላፊ ፡ ያልሆነ ፣ በምንኵስና ፡ ወይም ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ትዳር ፡ በመ ናቅ ፡ ብቸኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፣ ለሕዝብ ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ካልሠራ ፡



ፀቀር ፡ ለራሱ ፡ የዕለት፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ በመፈለግ ፡ ብቻ ፡ በዓለም፡ ውስጥ ፡ ከዓለማውያን፡ ጋር ፡ ዓላማዊ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፡ ዓላማና ፡ ውጤት፡ የሌለው ፡ ሥራ ፡ ነው ።

እኔም ፡ ከእንግዲህ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቴ ፡ ድረስ ፡ የምኖ ረው ፡ በብቸኝነት ፡ ነው ። እንደምታውቁት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቤ ታችን ፡ ራቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ጥዋት ፡ ማታ ፡ ከመመላለስ ፡ ጠቅልዬ ፡ እዚ ያው ፡ በቅጥረ ፡ ግቢው ፡ ብቀመጥ ፡ በተጠቃለለ ፡ ሐሳብ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ለመነጋገር ፡ ይመቸኛል ።

ከናንተ ፡ ጋር ፡ ብቀመጥ ፡ የምቾት ፡ ኑሮ ፡ አገኛለሁ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሰውን ፡ ሐሳብና ፡ የልቡን ፡ ምኞት ፡ ሰው ፡ አያውቀውም ። ትዳር ፡ የመያዝ፡ ፍላጎት ፡ ያለኝ ፡ የሚመስላቸው ፡ በሌላ ፡ እየፈለጉኝ፡ በሴትነቴ ፡ ከማዝንና ፡ ከምበሳጭ ፣ በተወሰነ ፡ ቁርጠኛ ፡ ሥፍራ ፡ ብቀ መጥ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከመክብብ ፡ ጋር ፡ ስወያይበት ፡ ቆይ ቻለሁ ።

ስለዚህ ፡ ልጆቼ ፡ የምለምናችሁ ፣ ይህ ፡ ፍቅራችሁና ፡ መተሳሰባ ችሁ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲኖር ፡ ነው ። መክብብ ፡ አባትህ፡ አንተን ፡ በመውለዳቸው ፡ አልሞቱም ፡ አሉ ፣ በድካማችን ፡ ያቋቋም ነውን ፡ ተመርኩዛችሁ ፡ እንደአሁኑ፡ ይዞታችሁ ፡ ከቀጠላችሁ ፣ ከጊዜ፡ ወደጊዜ ፡ ታስፋፋላችሁ ፣ ለኔ ፡ አታስቡ ፣ ባለሁበት ፡ ትረዱኛላችሁ ። ከዕለት ፡ ልብሴ ፡ በቀር ፡ የምወስደው ፡ የለም ። ያው ፡ ሁሉንም ፡ ተረ ከቡኝ ፡ አለችን ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፀሐይ ፡ ዕንባዋን ፡ አፍስሳ ፣ ምነው ፡ እማማ ፡ ምን ፡ በደልኩ ፡ እስከዛሬ ፡ ኖረው ፡ ስመጣ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ያልሰማሁትን ፡ አሳዛኝ ፡ የሆነ፡ ነገር ፡ የሚያሰሙኝ፡ ብላ ፡ እያለቀሰች፡ መልስ ፡ ሰጠቻት ።

ልጄ ፡ ምነው፡ ታለቅሽብኛለሽ ፣ መክብብ ፡ አልነገረሽም ፡ እንጂ፡ አንቺን ፡ ከማጨቱ ፡ በፊት ፡ ይህን ፡ ሐሳቤን ፡ ያውቃል ፣ የቆየሁት ፡ እስኪያገባ ፡ ነው ። ካገባም ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የተቀመጥ ኩት ፣ ያንቺ ፡ ደግነት ፡ እግር ፡ ብረት ፡ ሆኖ ፡ አሥሮ ፡ ስለያዘኝ ፡ ነው። ግን ፡ እኔን ፡ ይጐዳኛል ፡ እንጂ ፡ አይጠቅመኝም ። አሁንም ፡ በኔ ፡ በኩል ፡ ሆነሽ ፡ የኔን ፡ ሁኔታ ፡ እይና ፡ ፍረጅ ። ለርዳታው ፡ እንደሆነ ፡ ከዚያም ፡ ቢሆን ፡ ከአንቺ ፡ አልወጣም ፡ አለቻት ።

ፀሐይ፡ተከዘች ፡ እማማ ፡ ስለፀሐይ ፡ ፍቅር ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ለመኖር ፡ ሐሳብሽን ፡ የለወጥሽ፡ መስሎኝ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ነበር። እኔን ፡ ትዳር ፡ እንድይዝ ፡ ያደረገኝ ፡ ይህ ፡ አስተሳሰብሽ ፡ ነው ። ካጠገባችን ፡ ብትርቂ ፡ አንወድም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ተወስነሽ ፣ በጥዋት ፡ በማታ ፡ ከፈጣሪሽ ፡ ጋር ፡ በምታደርጊው ፡ ንግግር ፡ ትጠቀሚበት ፡ ይሆናልና ፡ የሐሳብሽ ፡ ዕንቅፋት ፡ አንሆንም ፣ እንዳልሽው ፡ ይፈጸም ፡ አልኳት ።

ከደስታ ፡ ጋር ፡ አመሰገነች ። ይዛው ፡ የምትሔደው ፡ ልብስና ፡ ዕቃ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ሰነበተ ። በተነጋገርን ፡ በሳምንቱ ፡ ይዘናት ፡ ሄድን ። የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ፀሐይ ፡ በደንብ ፡ አደረገችላት ። ስናነጋግራት ፡ ውለን ፡ የማታ ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡ ተመለስን ። የእናቴ ፡ መሄድ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትዝታ ፡ አሳደረብን ። በየሳምንቱ ፡ እሑድ ፡ ባለማቋረጥ ፡ እየሄድን ፡ እንጠይቃታለን ። በሦስት ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ መልክተኛ ፡ እየላክን ፣ በማስጠየቅ ፡ አልተለየናትም ። በወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መጥታ ፡ ትጠይቀናለች ።

ፀሐይ ፡ ሁለተኛ ፡ ፀነሰች። እናቴም ፡ ሰማች ። እንደመጀመሪያው፣ አያማትም ፡ አታስብ፡ አለችኝ ። እንዳለችውም ፡ አላመማትም ። የሆነ፡ ሆኖ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ገባ። እንደመጀመሪያው ፡ ሌሊት ፡ ምጥ ፡ የያዛት፡ እንደሆነ ፡ ማንን ፡ እጠራለሁ ፡ ብዬ ፡ አሰብኩ። ቀኑን ፡ ቈጥራ ፡ ኻያ ፡ ቀን ፡ ሲቀራት ፡ ወደቤት ፡ መጥታ ፡ ለመሰንበት ፡ ሐሳብ ፡ እንዳላት ፡ እናቴ ፡ ነገረችኝ ፣ ደስ ፡ አለኝ ። ፀሐይም ፡ ስትሰማ ፡ የበለጠ ፡ ደስ ፡ አላት ። የርግዝናዋ ፡ ወራት ፡ ስምንት ፡ ወር ፡ ከአሥር ፡ ቀን ፡ ሲሆን ፡ ወደቤት ፡ አመጣኋት ፣ በይቶት ፡ እግዜሯና ፡ በእናቴ ፡ ረዳትነት ፡ በምጥ ፡ ሳትቸገር ፣ ፀሐይ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ። የወለደችውም ፡ በሥራ ፡ ሰዓት ፡ ቀን ፡ በመሆኑ ፣ ምጥዋን ፡ ሳላይ ፡ በመውለድዋ ፣ ደስ፡ አለኝ ። ይቶት ፡ እግዜሯ ፡ እናቴ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ያዩትን ፡ የኔን ጭንቀት ፡ በሁለተኛው ፡ ሳያዩ ፡ በመቅረታቸው ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

እናቴና ፡ እናትዋ፡ ፀሐይን ፡ አሁንም ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ጠብቀዋት ፣ ሕፃኑ ፡ ፋፋ ። በአርባ ፡ ቀን ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ ተቀበለ ። እናቴ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ፀሐይን ፡ አርሳ ፡ (ተከባክባ) ፡ ወደ ፡በዓቷ ፡ ተመለሰች ።



የፀሐይ ፡ እናት ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ በብቸኝነት ፡ የኖሩት ፣ ፀሐይ ትዳር ፡ እስክትይዝ ፡ ነበር ። ፀሐይ ፡ ትዳር ፡ በያዘች ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ርሳቸውም ፡ ትዳር፡ ሊይዙ፡ ፈልገው ፡ የምንነጋገረው ፡ ጉዳይ፡ ስላለ ፣ እንድትመጡ ፡ ብለው፡ላኩብን ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በየአሥራ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ እንጠይቃቸዋለን ። ለምን ፡ ፈለጉን ፡ ብለን ፡ ሄድን ።

ምሳችንን ፡ ከጋበዙን ፡ በኋላ ፣ ልጆቼ ፡ ያለኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ በብቸኝነት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መኖር ፡ ከባድ ፡ ነው ። በብቸኝነት ፡ ከመኖር ፡ እንደ ፡ መከብብ ፡ እናት ፡ ቆርጦ ፣ በተወሰነ፡ ሥፍራ ፡ ለሥጋ ፡ ሳያስቡ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት ፡ በአንድ ፡ ዓላማ ፡ መቆም ፡ ዕድል ፡ ነው ። ይህ ፡ ለሁሉ ፡ የማይሰጥ ፡ ነው ፣ ይህ ፡ ካልሆነ ፣ ከኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ ጋር ፡ መኖር ፡ ይሻላል ። የፀሐይ ፡ አባት ፡ ከሞተ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ። እስካሁን ፡ ትዳር ፡ ያልያዝኩት ፡ አንድ ፡ ልጄን ፡ የእንጀራ ፡ አባት ፡ አላሳያትም ። ትዳር ፡ እስክትይዝ ፣ ትዳር ፡ መያዝ ፡ የለብኝም ፡ ብዬ ፡ ከርስዋ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አሳለፍኩ ። አሁን ፡ ግን ፡ ባል ፡ ላገባ ፡ ወስኛለሁ ።

ከፀሐይ ፡ አባት ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ያቋቋምነው ፡ ንብረት ፡ እስካሁን ፡ በኔ ፡ እጅ ፡ እየተጠበቀ፡ ጥቃት ፡ እንዳይገባኝ ፡ በሴት ፡ አቅሜ፡ እየተከታተልኩ ፡ አስፋፍቸዋለሁ ፡ እንጂ ፡ አልተቀነሰም ። ከዕለት ፡ ልብስና ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ በቀር ፡ የምወስደው ፡ የለም ። ልጄ ፡ አባትሽ ፡ ደግ ፡ ሰው ፣ የደግ፡ መጨረሻ፡ ነበር።አንቺም ፡ የተባረክሽ ፡ ስለሆንሽ፡ ደኅና ፡ ባል ፡ አጋጥሞሻል ። ስለዚህ ፡ ማናቸውንም ፡ንብረትና ፡ ሀብት፡ እንድትረከቡኝ ፡ አሉን ።

ፀሐይ ፡ አለቀሰች ፣ ተይ ፡ ብላትም፡ ባሰባት ፣ መተው ፡ አልቻለችም ። እናትዋም ፡ አለቀሱ ። የነርሱ ፡ ለቅሶ ፡ ለኔም ፡ ተርፎ ፡ አለቀስኩ ። እማማ ፡ ብቸኝነት ፡ እንደተሰማሽ ፡ ይገባኛል። ትዳር ፡ መያዝሽ፡ በተለይ ፡ እኔን ፡ ያስደስተኛል ። ልቤም ፡ ይረጋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ንብረቱ ፡ ባንቺው ፡ ይጠበቅ ፡ እንጂ ፡ ትዳር ፡ ስትይዥ ፡ ቤትሽን ፡ የምትደግፊበትን ፡ ለኔ ፡ የምታስረክቢበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ጠየቀቻቸው ።

ልጄ ፡ በትዳር ፡ ጓደኛነት ፡ የፈለገኝ ፡ ሊያሳድረኝ ፡ ካልቻለ ፡ በብቸኝነት ፡ ዕድሜዬን ፡ ሙሉ ፡ እኖራለሁ ፡ እንጂ ፣ አባትሽ ፡ ወጥቶ ፡

ወርዶ ፡ ያቋቋመውን ፡ ንብረት ፤ ገና ፡ ጠባዩንና ፡ አመሉን ፡ ላላወቅሁት ፡ የኑሮ ፡ መደገፊያ ፡ አላደርገውም። ሀብቱ ፡ ያንቺ ፡ ነው ፤ ለኑሮ፡ ጓደኛነት ፡ የጠየቅኹና ፡ በአምጭዎች ፡ ዝናውን ፡ ሰምቼ ፡ የወደድኩት፡ የማይስማማኝ ፡ ሲሆን ፡ ማኩረፊያዬ ፡ ነው ፡ እንጂ፤ ለኑሮ ፡ መደገፊያ፡ አድርጌ ፡ አላገባም ። ነገሩን ፡ አውጥቼ ፡ አውርጄ ፡ የወሰንኩት ፡ ስለሆነ ፡ ግዴለሽም ፡ ልጄ ፤ የኔው ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ መለሱላት ።

ፀሐይ ፡ የምትመልሰው ፡ ስታጣ ፤ ዐየችኝ ፤ ዓይን ፡ ለዓይን ፡ ተያየን ። እመቤቴ ፡ ነገሩን፡ ጨርሰውታል ። ሐሳብዎን ፡ ሲያካፍሉን ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፡ አጥንተው ፡ እንድንሰማው ፡ እንጂ ፡ አሳብ ፡ እንድናካፍልዎ ፡ አይደለም ። በጠቅላላው ፡ ትዳር ፡ መያዝዎ ፡ የሚወደድ ፡ ነው ። ንብረቱ ፡ በእጅዎ ፡ ሆኖ ፤ የንብረትዎ፡ መደገፊያ ፡ ቢሆን ፡ ባልከፋ ፡ ነበር ። ካልመሰለዎ ፡ እንዳሉት ፡ ይሁን ፡ አልኳቸው ።

ልጆቼ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጣችሁ ፤ የዛሬ ፡ ሦስት ፡ ሳምንት ፡ የጋብቻዬ ፡ ቀን ፡ ነው ። የዛሬ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ መጥታችሁ ፡ ሁሉንም ፡ እንጨርስ ፡ አሉና ፡ አሰናበቱን ።

የእናትሽ ፡ አስተሳሰብ፡እንግዳ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ተደንቅሁ ፤ በአስተዋይነታቸው ፡ ተገረምኩ ፤ አልኳት ፡ ፀሐይን ፡ ወደቤታችን ፡ ስንመለስ ።

እናቴ ፡ አስተዋይ ፡ ናት ። አሳብዋን ፡ አላመዛዘንኩም ፡ እንጂ ፤ አንቺ ፡ ትዳር ፡ ካልያዝሽ ፡ ትዳር፡ አልይዝም ። አንቺ ፡ ትዳር ፡ ይዘሽ፡ ትዳር ፡ ብይዝም፤ ከልብሴና ፡ ከጌጣጌጦች፡ በቀር ፡ የምወስደው ፡ የለም፡ ሁሉንም ፡ ለአንቺ ፡ አስረክቤ ፡ መሄድ ፡ አለብኝ ። ይህን ፡ ንብረት ፡ ለማቋቋም ፡ አባትሽ ፡ የደከመው ፡ ድካም ፡ አይረሳኝም ። ርሱ ፡ የደከመበትን ፡ ሳይጠቀምበት ፡ በሞት ፡ ቢቀድመኝ፤ ትዳር ፡ ካልያዝኩ ፡ እጠቀምበታለሁ ። ከያዝኩ ፡ አንቺ ፡ ልጁ ፡ ትጠቀሚበታለሽ ፡ ትለኝ፡ ነበር ። ያለችውን ፡ በሥራ ፡ ልትገልጠው ፡ ነው ፡ ብላ ፡ መልስ ፡ ሰጠችኝ ።

የፀሐይ ፡ እናት ፡ አስተሳሰብ ፡ አሁንም ፡ አስደነቀኝ ። የማላውቀውን፡ አዲስ፡ ዜና ፡ በመስማቴ ፤ ባልና ፡ ሚስት፡ አብረው ፡ ያፈሩት፡ ንብረት ፡ የጋራቸው ፡ ነው ። ወንዱ፡ ወይም ፡ ሴትዋ ፡ ፅሞት ፡ ሲለዩ፡ ድርሻቸውን ፡ ለልጆቻቸው ፡ በኑዛዜ ፡ ይደለድላሉ ። ልጆቹ ፡ በአባታ



ቸው ፡ ወይም ፡ በእናታቸው ፡ ድርሻ ፡ ሳይጠቀሙ፡ ይቸገራሉ ። ችግር ፡ ሲበዛ ፤ በፍርድ ፡ ቤት፡ከሰው፡ በየአደባባዩ፡ የሚንከራተቱ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

ያንቺ ፡ እናት ፡ አስተሳሰብ ፡ ከማንም ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ አባትሽ ፡ የደከሙበትን ፡ በሙሉ፡ ተረክበሽ ፡ እንድታስተዳድሪ ፡ መወሰናቸው፡ የታላቅነት ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ አልኳት ።

ቀጠሮዋችንን ፡ በማስታወስ ፡በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ቤት ፡ ሄድን ። የባላቸውን ፡ ቅርብ ፡ ጓደኞች ፡ ሰብስበው ፡ ሲጠብቁን ፡ ደረስን ። በበኩላችን ፡ ተዘጋጅተን ፡ ነው ፡ የሄድነው ። ማናቸውም ፡ ንብረታቸው ፡ በጽሑፍ ፡ ተመዝግበዋል ። መዝገቡ ፡ ቀርቦ ፤ ምንና፡ ምን ፡ እንደሆነ ፤ የሚገኝበት ፡ ሥፍራ ፡ እየተለየ፡ ተነቦ ፡ መዝገቡን ፡ ተረከብን ። የቤት ፡ ዕቃዎችን ፡ በዝርዝር ፡ የሚያሳየውና ፡ የገንዘብ ፡ ወጭ ፡ መዝገብ ፡ እንደዚሁ ፡ ቀርቦ ፡ ተነበበ ። መዝገቦቹን ፡ ተቀብለን ፡ በመዝገብ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ተረከብን ።

ርክክቡ ፡ ሲያልቅ ፤ ምሳ ፡ ተጋበዝን ። ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ወደቤት ፡ ስመለስ ፤ ፀሐይ ፡ ከናትዋ ፡ ጋር ፡ ልትሰነብት ፡ ቀረች ። ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ጋብቻቸው ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሲቀረው ፤ እናቴን ፡ ይዤ ፡ ሄድኩ ። ማናቸውንም ፡ አዘጋጀን ። በጋብቻቸው ፡ ቀን ፡ ሙሽራው ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ራሳቸውን፡ ሆነው ፡ መጡ ። ዝግጅታችን ፡ የተሟላ ፡ ስለሆነ፡ በደስታ ፡ ተቀበልናቸው ። በጋብቻቸው ፡ ውል ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተስማምተው ፤ ተነቦ ፡ ተፈረመ ። ግብዣው ፡ ቀጠለ ፤ የግብዣው ፡ ፍጻሜ ፡ እንደሆነ ፤ ከሽማግሌዎቹ ፡ አንዱ፡ «ጋብቻ ፡ ክቡር ፡ ነው ፤» ክቡር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይበቃም ፤ እኛም ፡ ካላከበርነው ፤ ጋብቻ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ ሁለት ፡ ጋብቻ ፡ የለም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጋብቻን ፡ በሕግ፡ ከሚያፈርሱት ፡ አንዱ ፡ ሞት ፡ ነው ። ወንዱ ፡ ወይም ፡ ሴትዋ ፡ የሞቱ ፡ እንደሆነ ፤ በመካከላቸው ፡ ያለው፡ጋብቻ ፡ በሕግ ፡ ይፈርሳል።በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻው፡ ወይም ፡ ጋብቻዋ ፡ የፈረሰባቸው ፡ ሁለተኛ ፡ ማግባት ፡ ይችላሉ ። ወይዘሮ ፡ ዘነበች፡ባለቤትዋ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳሉ ፡ ጋብቻን ፡ አክብራ ፡ የኖረችና ፡አሁንም ፡ አክብራ ፡ የምትኖር ፡ ወይዘሮ ፡ ናት ። ስለዚህ ፡ ጋብቻችሁ ፡የተባረከ ፡ ጋብቻ፡ እንዲሆንላችሁ ፡ የሁላችንም ፡ ምኞት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መረቁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተሰነባብተን ፡ ሄዱ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ፀሐይና ፡ እናትዋ ፡ አንገት ፡ ለአንገት ፡ ተያይዘው ፡ እየተላቀሱ ፡ አንላቀቅም ፡ አሉ ። በሽማግሌዎች ፡ ቁጣ ፡ ተላቀው ፡ በዕንባ ፡ ተለያዩ ። የኔም ፡ እናት ፡ በጣም ፡ አለቀሰች ። ወደቤታችን ፡ ሳንሄድ ፡ በዚያው ፡ ሰነበትን ። ፀሐይ ፡ እናትዋን ፡ በሳምንቱ ፡ ጠራች ። ከባላቸው ፡ ጋር ፡ መጥተው ፡ ለሦስት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ሰንብተው ፡ ተመለሱ ።

ማናቸውንም ፡ በደንብ ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፡ እንደራሳችን ፡ የምናምነው ፡ እንደራሴ ፡ በቤቱ ፡ አስቀምጠን ፡ ወደቤታችን ፡ ተመለስን ። እናቴም ፡ ወደ ፡ በዓቷ ፡ ሄደች ። ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ከባላቸው ፡ ጋር ፡ ቤታችንን ፡ እንዲያዩ ፡ ጠራናቸው ።

ጥሪያችንን ፡ አክብረው ፡ መጡ ፤ ዐራት ፡ ቀን ፡ አቆየናቸው ። በአምስተኛው ፡ ቀን ፡ ሄዱ ።

እናቴ ፡ ንብረቱን ፡ በሙሉ ፡ አስረከበችን ፤ ቢሆንም ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ከምታይ ፡ ለምትፈልገው ፡ የምታውለው ፡ ገንዘብ ፡ መስጠት ፡ የሚገባን ፡ ይመስለኛል ። ምን ፡ ይመስልሃል ፡ ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ጠየቀችኝ ።

የሚገባ ፡ ነው ፡ አልኳትና ፡ ማናቸውንም ፡ ሁሉ ፡ አዘጋጅተን ፡ ብንወስድላቸው ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አልኳት ። ተስማማች ፤ አዘጋጅተን ፡ ሄድን ። በደረስን ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ ፈንታ ፡ ደነገጡ ፤ ሊጠሩን ፡ አስበው ፡ ሳለ ፡ ቀድመን ፡ ስለሄድን ፤ ልጆቻችንን ፡ ይዘን ፡ ስለነበር ፡ አስነበቡን ። በወሰድነው ፡ ሁሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ተቆጡ ። በተለይ ፡ ገንዘብ ፡ አልቀበልም ፡ ብለው ፤ ፀሐይ ፡ አስገድዳ ፡ እንዲቀበሉ ፡ አደረገች ። እናትና ፡ ልጅ ፡ የተነፋፈቁትን ፡ ያህል ፡ አብረው ፡ በመሰንበታቸው ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ከፀሐይ ፡ እንጀራ ፡ አባት ፡ ከአቶ ፡ ግሩም ፡ ጋር ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ በመለዋወጥ ፡ ተለማመድን ። የልጆቻቸውን ፡ እናት ፡ ትተው ፤ የፀሐይን ፡ እናት ፡ ያገቡበትን ፡ ምክንያት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ አጫወቱኝ ። ከሻያ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ዕድሜ ፡ ያላቸው ፡ ልጆች ፡ አሉዋቸው ። ንብረታቸው ፡ ሰፊ ፡ በመሆኑ ፤ ልጆቹ ፡ የሚኖሩት ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ ነው ። ሁኔታውን ፡ ከተረዳሁ ፡ በኋላ ፡ ለወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ አዘንኩ ። ለአቅመ ፡ አዳምና ፡ ለአቅመ ፡ ሔዋን ፡ የደረሱ ፡ ልጆቻቸው ፡ ያሳዝንዋቸዋል ፡ ብዬ ። የፀሐይ ፡ እናት ፡ ከልጃቸውና ፡ ከልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ ሲደ



ሰቱ ፡ ሰንብተው ፤ ወደ ፡ ቤታችን ፡ ስንመለስ ፤ እናትና ፡ ልጅ ፡ መላቀሳቸው ፡ አልቀረም ። ሆኖም ፡ ተሰነባብተን ፡ ሄድን ። ካንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ እናቴን ፡ ጭምር ፡ ግብዣ ፡ ጠሩን ። ፀሐይ ፡ ለእናትዋ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ አሁንም ፡ አዘጋጀች ። እናቴ ፡ ግን ፡ በየምክንያቱ ፡ ከበዓቴ ፡ መለየቱ ፡ አይገባኝም ፤ ልጄ ፡ ኮከቤ ፡ ቅር ፡ ካላለሽ ፡ ልቅር ፤ እናትሽንም ፡ ይቅርታ ፡ ጠይቂልኝ ፡ አለቻት ።

ቅር ፡ አይለኝም ። እናቴም ፡ ከነገርኳት ፡ ይገባታል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ባልዋ ፡ ቅር ፡ ይላቸዋል ። ወደፊት ፡ ባናስቸግርዎ ፡ ዛሬ ፡ አብረን ፡ ሄደን ፡ ባይሆን ፡ በቶሎ ፡ ብንመለስ ፡ ይሻላል ፡ ብላ ፡ መልስ ፡ ሰጠቻት ።

ልጄ ፡ አንቺ ፡ ካልሽ ፡ ይሁን ። የተባረክሽ ፡ ቡርክት ፡ ስለሆንሽ ፡ ምክርሽን ፡ እቀባላለሁ ፤ እንሂድ ፡ ብላ ፡ ተስማማች ።

ጥሪያቸውን ፡ አክብረን ፡ ሄድን ። ምክንያቱም ፡ እኛ ፡ እንሁን ፡ እንጂ ፡ ዝግጅቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ተጋባዡም ፡ ብዙ ፡ ነው ። ሦስት ፡ ቀን ፡ አድረን ፡ በዐራተኛው ፡ ቀን ፡ ወደቤታችን ፡ ተመለስን ።

በጉዞ ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፤ ፍቅርና ፡ ሰላም ፡ ካለ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ደኅና ፡ ቤት ፡ ገብተዋል ። ባልና ፡ ሚስት ፡ በሐሳብ ፡ የሚራራቁና ፤ ፍቅር ፡ የሚያጡት ፤ በሰላማቸውና ፡ በፍቅራቸው ፡ መካከል ፡ ሌላ ፡ የገባ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ባልና ፡ ሚስት ፡ ልብ ፡ ከልብ ፡ ከተራራቁና ፡ መተማመን ፡ ከመካከላቸው ፡ ከጠፋ ፤ አብረው ፡ የሚኖሩበት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ያጠረ ፡ ነው ፡ አለች ፡ እናቴ ።

እማማ ፡ ካሉስ ፡ እረ ፡ ሌላ ፡ አለ ፡ አለችና ፤ እናቴ ፡ በርከት ፡ ላሉ ፡ ዓመታት ፡ ሳታገባ ፡ የቆየችው ፡ አንድ ፡ ልጄን ፡ የእንጀራ ፡ አባት ፡ አላሳያትም ፤ ትዳር ፡ ካልያዘች ፡ ትዳር ፡ አልይዝም ፡ ብላ ፡ ነው ። ከልቤ ፡ አውጥቼ ፡ ባልናገረውም ፤ ለኔ ፡ ትጠነቀቅና ፡ ታስብ ፡ የነበረች ፡ ራስዋን ፡ የእንጀራ ፡ እናት ፡ አድርጋ ፡ ትልልቅ ፡ ልጆች ፡ ካሉበት ፡ ቤት ፡ መግባትዋ ፡ ደስ ፡ አላለኝም ። ፈቃድዋን ፡ ሳትሰጥ ፡ አማክራኝ ፡ ቢሆን ፡ ጋብቻውን ፡ እንዳትቀበል ፡ እምክር ፡ ነበር ። አሁን ፡ የሆነ ፡ ሆንዋል ። ለኔ ፡ ብላ ፡ በብቸኝነት ፡ የኖረችበትን ፡ ቈጥሮ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ እንዲያደርግላት ፡ እመኝላታለሁ ፡ ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ተናገረች ።

የናቴንና ፡ የፀሐይን ፡ የሐሳብ ፡ ገለጣ ፡ ከማዳመጥ ፡ በቀር ፡ አልተናገርኩም ። መክብብ ፡ ዝም ፡ ያልከው ፡ ንግግራችንን ፡ ጠልተኸው ፡

ነው ፡ ምንድነው ? ብላ ፡ እናቴ ፡ ጠየቀችኝ ። ሁለታችሁም ፡ ደኅና ፡ እስተውላችኋል ፡ ብዬ ፡ መለስኩላቸው ።

ይህን ፡ እየተነጋገርን ፡ እቤታችንም ፡ ደረስን ። እናቴም ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ እድራ ፡ ጧት ፡ በዓትዋ ፡ አደረስኳት ።

በየወሩ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበችን ፡ እየሄድን ፡ ስንጠይቅ ፡ አይናገሩ ፡ እንጂ ፤ የደስታ ፡ ስሜታቸው ፡ ከፊታቸው ፡ ጠፍቶ ፡ ታየን ። በመካከሉ ፡ ፀሐይ ፡ ሦስተኛ ፡ ነፍሰጡር ፡ ስለሆነች ፤ እኔ ፡ ብቻ ፡ እየሄድኩ ፡ እጠይቃቸው ፡ ነበር ። አቶ ፡ ግሩም ፡ የነበራቸው ፡ አቀባበል ፡ ተቀነሰ ፤ ቢሆንም ፡ ሁኔታውን ፡ እየታዘብኩ ፡ እመለሳለሁ ።

የማይለመድ ፡ የለም ፡ የፀሐይ ፡ ዕርግዝናና ፡ ምጥ ፡ ተለመደ ። ሳንደነግጥ ፡ በተለመደው ፡ አኳኋን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወለደች ። የምሥራቹን ፡ ለእናትዋ ፡ ላክሁና ፡ መጡ ። ፀሐይ ፡ ሁለቱን ፡ ልጆች ፡ ስትወልድ ፡ ያረሰቻት ፡ እናቴ ፡ ነበረች ። አሁን ፡ ግን ፡ የኔ ፡ ተራ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሊያርሱ ፡ ቀሩ ። አቶ ፡ ግሩም ፡ ደስ ፡ ሳይላቸው ፡ ወደቤታቸው ፡ ተመለሱ ።

ውሎ ፡ ከማደር ፡ የተነሣ ፤ ከባላቸው ፡ ጋር ፡ እንዳልተስማሙ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ለፀሐይ ፡ አጫወትዋት ። ፀሐይ ፡ ከልብ ፡ ትዘን ፡ እንጂ ፡ በትዕግሥት ፡ እንዲቀመጡ ፡ መከረቻቸው ። ኻያ ፡ ቀን ፡ እንደተቀመጡ ፡ አቶ ፡ ግሩም ፡ መጥተው ፡ ወሰድዋቸው ። የሕፃንዋ ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ ደርሶ ፡ ጠርተናቸው ፡ እንደገና ፡ መጡ ። በየምክንያቱ ፡ አንድ ሳምንት ፡ አቆየናቸው ።

ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ልጠይቃቸው ፡ ሄድኩ ። አቶ ፡ ግሩም ፡ በአቀባበል ፡ ትሕትና ፡ አሳዩኝ ። ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ቤቴ ፡ ቤቴ ሲሉ ፡ አየኋቸው ፤ ደስ ፡ አለኝ ።
ተመልሼ ፡ ለፀሐይ ፡ አጫወትኳት ፡ ርስዋም ፡ ደስ ፡ አላት ።

# በ ሀ ብ ት ሽ ፡

ሆኖ ፡ ጋብቻችን ፡ በሀብትሽ ፡ በሀብቴ ፤
እማረ ፤ ዳበረ ፡ ሕይወትሽ ፡ ሕይወቴ ።
ሳንጋባ ፡ ገና ፡ ስንተሳሰብ ፤
እልነበረን ፡ ምንም ፡ አንዳችም ፡ ገንዘብ ።



የሰው ፡ ልጅ ፡ ጥንቱንም ፡ ተፈጥሮ ፡ ሲመጣ ፤
ከሥጋው ፡ በስተቀር ፡ ምንም ፡ ይዞ ፡ አይወጣ ።
ተሳስበን ፡ በፍቅር ፡ ጣርን ፡ ለቤታችን ፤
ተገኘ ፡ ያልነበር ፡ ሞላ ፡ ሐሳባችን ።
ደግሞ ፡ ይልቁንም ፡ ታላቁ ፡ ስጦታ ፤
መርካት ፡ ነው ፡ በመንፈስ ፡ በልጆች ፡ ደስታ ።
አድገው ፡ ልጆቻችን ፡ ደርሰው ፡ ለቁም ፡ ነገር ፤
ያስፋፉሉ ፡ ትውልድ ፡ ይበዛሉ ፡ በዘር ።
ይህንን ፡ ችሮታ ፡ ለሰጠን ፡ አምላክ ፤
ይድረሰው ፡ ምስጋና ፡ ስሙ ፡ ይባረክ ።
ከምስጋና ፡ ጋራ ፡ እንመልስ ፡ ውለታ ፤
ሥራችን ፡ እንዲያገኝ ፡ የጠበቀ ፡ ዋልታ ።
የቤታችን ፡ ዋልታ ፡ የሚጠነክረው ፤
እንዲሁ ፡ ፍቅራችን ፡ ጸንቶ ፡ ሲቀጥል ፡ ነው ።
በመካከላችን ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ሳይኖር ፤
ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ነው ፡ የኖርነው ፡ በፍቅር ።
መሠረት ፡ ነው ፡ ፍቅር ፡ የመሠረት ፡ ድንጋይ ፤
ሠራን ፡ ቤታችንን ፡ ከጽኑዕ ፡ ዓለት ፡ ላይ ።
ቊንጅናና ፡ ውበት ፡ ጠባይና ፡ ሞያ ፤
ስጥቷል ፡ አደላድሎ ፡ እንበል ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።
ተርቧል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደርሶበታል ፡ ጥም ፤
ምንም ፡ ቢነጋገር ፡ አይጣጣምም ፤
ላይ ፡ ላይውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፍቅር ፡ የለውም ።
ፍቅር ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ከምግባር ፡ የራቀ ፤
ምንም ፡ ነገር ፡ ሳይዝ ፡ ሁሉን ፡ የለቀቀ ።
ሀብታም ፡ ቢሆን ፡ ከቶ ፡ ክብርም ፡ ቢጨምር ፤
ኃላፊ ፡ ነው ፡ ሁሉም ፡ እንዲሁ ፡ ሳይቀር ፤
ይነገርለታል ፡ እንደዚህ ፡ ነበር ።
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ትርፉ ፤
በቁም ፡ ነገር ፡ ሞያ ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ሲያልፉ ።

## ክፍል ፡ ፩ ፤

# ምርቅና ፡ ፍትፍት ፡

ፀሐይ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ከወለደች ፡ በኋላ ፡ መውለድ ፡ አቆመች ። እኔና ፡ ርስዋ ፡ ለወላጆቻችን፡ አንዳንድ ፡ ነን ። ይባረኩ ፡ እንጂ ፤ ሦስቱ ፡ ይበቁናል ፡ ብለን ፡ በምስጋና ፡ ተቀበልነው ። ወንድ ፡ ልጃችን ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፤ ሴቶች ፡ ሁለት ፡ እንደሆኑ ፡ ወንዶቹም ፡ ሁለት ፡ ቢሆኑ ፡ እወዳለሁ ፡ ትላለች ፡ ፀሐይ ።

ገና ፡ ልጆች ፡ ናችሁ ፡ በልጅነት ፡ መውለድ ፡ የልጅ ፡ ወንድም ፡ ማግኘት ፡ ነው ። ኮከቤ ፡ መውለድ ፡ ማቆምሽ ፡ ደስ ፡ አላለኝም ፡ አለች ፡ እናቴ ።

ያሁኑ ፡ የፀሐይ ፡ አለመውለድ ፡ እንደ ፡ ዕረፍት ፡ ይቈጠራል ፡ እንጂ ፤ መውለድ ፡ አቆመች ፡ አይባልም ፡ ብዬ ፡ ለእናቴ ፡ መለስኩ ።

ፍሬ ፡ ከተባረከ ፡ አንድ ፡ በቂ ፡ ነው ። ለኔ ፡ አንተ ፤ ለወይዘሮ ፡ ዘነ በች ፡ ኮከቤ ፡ ብቻ ፡ ናችሁ ። በሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ አንድ ፡ ምን ፡ ጊዜም፡ አንድ ፡ ነውና ፡ ካንድ ፡ ሁለትና ፡ ሦስት ፡ ይሻላል ። ልጆች ፡ በዛ ፡ ቢሉ ፡ ደስ ፡ ይላል ። ካንድ ፡ ማኅፀን ፡ ተገኝተው ፡ አስተሳሰባቸ ውና ፡ አስተያየታቸው ፡ የተለያየ ፡ ልጆች ፡ ይወለዳሉ ። በተለይ ፡ ወላ ጆች ፡ በዕድሜ ፡ ገፍተው ፤ በአዕምሮ ፡ በሰለው ፡ የሚወለዱ ፡ ልጆች ፡ መልካም ፡ አስተሳሰብ ፡ ያላቸው ፡ ይሆናሉ ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ልጆቻችሁ ፡ በርከት ፡ ብለው ፡ ማዕዳችሁን ፡ አጣባው ፡ ባያቸው ፡ የተለየ ፡ ደስታ ፡ ይሰማኛል ፡ አለች ፡ እናቴ ።

እማማ ፡ ምን ፡ ይታወቃል ፤ እንዳሉት ፡ ይሆናል ፤ በጥበብ ፡ አላ ቆምነው ፤ በርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ከመሞቴ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ደስ ፡ ስለሚለኝ ፡ ነው፡ እንጂ ፤ እናንተማ፡ ልጆች ፡ ስለሆናችሁ ፡ እንዳልሽው ፡ መውለዳችሁ ፡ የማይቀር ፡ ነው ፡ ብላ ፡ መለሰች ፡ እናቴ ።

ሞትን ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ አመጣውና ፡ ከመሞቴ ፡ በፊት ፡ ብለሽ ፡ የተናገርሽው ፡ እማማ ፤ ሰው ፡ እኖራለሁ፡ብሎ ፡ ያስባል ። የሚደከመው፡

ለመኖር፡ ነው ። እሞታለሁ ፡ እያለ ፡ሞትን ፡ ዘወትር ፡ ካሰበማ ፤ ሥራ ፡ ሳይሠራ ፡ ሞቱን ፡ ብቻ ፡ እያሰበ ፡ የሞት ፡እሥረኛ ፡ ሆኖ ፡ መቀመጡ፡ ነው ። በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ይምጣ ፡ እንጂ ፤ ሞትን ፡ አንጠራውም ፡ አልኳት ፡ እናቴን ።

ዋ ፡ ልጄ ፤ መስሎህ ፡ ነው ፤ ሞት ፡ ቢጠሩት ፡ አይመጣም ። እንዲያውም ፡ አቤት ፡ አይልም ። ኑሮ ፡ የመረራቸው ፤ ከመኖር ፡ ያለመኖርን ፡ መርጠው ፡ ሲጠሩት ፡ አይሰማቸውም ። በክብር ፡ ከፍ ፡ ብለው ፤ በሀብት ፡ ልቀው ፤ ይህን ፡ ዓለም ፡ ያዝነው ፤ ያዝነው ፡ እያሉ ፡ ሞት ፡ ይኑር ፡ አይኑር ፡ የረሱትንና ፡ ሞት ፡ ወደኛ ፡ የሚመጣበት ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ ነው ፡ ካሉት ፡ ቤት ፡ ድንገት ፡ ከተፍ ፡ ብሎ ፡ ቤተሰቡ ፡ እንደ ፡ ዓይን ፡ ብሌን ፡ የሚያዩትን ፡ ለይቶ ፡ ይወስዳል ። ልጄ ፤ እኔ ፡ የሞት ፡ ስሙን ፡ ስለጠራሁት ፡ አይመጣም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ «ቀን ፡ እመጣ፡ ሌሊት፡ እመጣ፡ አታውቁምና ፡ ተዘጋጅታችሁ ፡ ጠብቁኝ ፡»ያለውን ፡ ካስተዋልን ፤ ዕለተ ፡ ሞትን ፡ ማሰብ ፡ ይገባል ፤ ብላ ፡ መልስ ፡ ሰጠችኝ ፡ እናቴ ።

ይሁንና ፡ ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ኑሮዋችንን ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እያሻሻልን ፤ ከአብራካችን ፡ ከተገኙት ፡ ከዓይናችን ፡ ማረፊያ ፡ ልጆቻችን ፡ ጋር ፡ እየተጫወትን ፤ ለመንፈሳችን ፡ ጤና ፡ ለሕሊናችን ፡ ፀጥታና ፡ ደስታ ፡ አገኘን ። በእናቶቻችን ፡ ላይ ፡ ያለን ፡ አክብሮትና ፡ ፍቅር ፡ የጋለም ፡ ቢሆን ፡ በተለይ ፡ ልጆች ፡ ወልደን ፤ በልጆቻችን ፡ ላይ ፡ ፍቅርና ፡ ስስት ፡ ስላደረብን ፤ ለካስ ፡ የኛም ፡ ወላጆች ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ስሜት ፡ አላቸው ፡ በማለት ፤ ፍቅራችንንና ፡ አክብሮታችንን ፤ አድራጎታችንንም ፡ በበለጠ ፡ ለግሠን ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ባለማቋረጥ ፡ እናቶቻችንን ፡ እንጠይቃለን ። በምንሄድበት ፡ ጊዜ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምርቃት ፡ እንቀበላለን ።

በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ እየቀጠልን ፤ በደስታ ፡ ስንኖር ፤ እፈልጋችኋለሁ ፤ መልእክቱ ፡ እንደደረሳችሁ ፡ እንድትመጡ ፡ ስትል ፡ እናቴ ፡ ላከች ። ምን ፡ ነገር ፡ ቢያገኛት ፡ ይሆን ፤ ደኅና ፡ አይደለችም ፡ ብለን ፡ መልእክተኛውን ፡ ብንጠይቅ ፡ ደኅና ፡ ናቸው ፡ አለን ። ቢሆንም ፡ ድንጋጤ ፡ ተሰማን ። ጐረቤቶቻችን ፡ ስለሰሙ ፤ ፀሐይና ፡ እኔ ፡ መንገዳችንን ፡ ስንቀጥል ፡ ተከተሉን ። በየሳምንቱ ፡ ስንመላለስ ፡ ያልታወቀን ፤ በድንጋጤ ፡ እንዳለን ፡ ስንጓዝ ፡ መንገዱ ፡ ረዘመብን ። ሆኖም ፡ እናቴ ፡ አ



ዋት ፡ ኖሮ ፡ ደርሰን ፡ ባየችን ፡ ጊዜ ፡ ምርር ፡ ብላ ፡ አለቀሰች ። ተዉ ፡ የሚል ፡ አልተገኘም ፡ ሁሉም ፡ አልቃሽ ፡ ሆነ ።

ሆዴ ፡ ባባ ፤ ባየኋችሁ ፡ ጊዜ ፡ አልችለው ፡ ብዬ ፡ አለቀስኩ ። ቅዝናለሁ ፤ እናንተንም ፡ አስለቀስኩ ። እንደቤቴ፡ በሞት ፡ ከመታሠሩ፡ ፊት ፡ ላነጋግራችሁ ፡ ጠራኋችሁ ። ልጆቼ ፡ ሁሉም ፡ ጊዜውን ፡ ጠብቆ ፡ ይመጣል ። ከጊዜው ፡ በፊት ፡ የሚመጣ ፡ የለም ። እየመሰለን ፡ እናስባለን ፡ እንጨነቃለን ፡ እንጂ ።

የኔ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መኖር ፡ በቃ ። ከምወዳችሁና ፡ ከምትወዱኝ፡ ልጆቼ ፡ በሞት ፡ ልለያችሁ ፡ ነው። መከብብ ፡ የተባረከች ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ አግኝተህ ፤ አበባ ፡ ልጆችህን ፡ በማየቴ ፡ አምላክን ፡ አመሰግናለሁ ። በመካከላችን ፡ ያለው ፡ የፍቅር ፡ አምላክ ፡ ፍቅራችንን ፡ አጽንቶ ፤ እስካሁን ፡ በአንድ ፡ አቆየን ። ፍቅር ፡ ባይኖር ፤ ሞት ፡ እንዲመጣ ፡ እለም ነው ፡ ነበር ። አሁን ፡ የፈራሁትና ፡ ባብቼ ፡ ያባባኋችሁ ፤ ፍቅራችሁ ፡ በፊቴ ፡ ተደቅኖ ፡ እንዴት ፡ ልለያችሁ ፡ ብዬ ፡ ነው ። ግን ፡ የተቈረጠ ፡ ቀለሆነ ፡ መለያየታችን ፡ ነው ።

ልጆቼ ፡ ቤታቸውን ፡ አቸንፈው ፤ ክብራቸውን ፡ ጠብቀው ፡ በፍቅር ፡ በሚኖሩ ፡ ቤተሰቦች ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ፈተና ፡ አለ ። በይዞታቸው ፡ የቀኑ ፡ ትዳራቸውን ፡ የሚያፈርሱበት ፡ ምክንያት ፡ ሲያጡ ፤ በልብ ፡ ወለድ ፡ ወሬ ፡ ስማቸውን ፡ አጥፍተው ፤ ለስም ፡ አጥፊዎች ፡ ይዘሩታል ። አንተ ፡ ወይም ፡ አንቺ ፡ ስትሰሙ ፤ መበሳጨት ፡ አያስፈልግም ፤ ናቁት ፡ የናቀ ፡ አቸናፊ ፡ ነውና ። ማናቸውንም ፡ ስትሰሙ ፤ በፍቅር ፡ የተመሠረተውን ፡ ቤት ፡ ለማፍረስ ፡ የተፈጠረ ፡ ዘዴ ፡ መሆኑን፡ አስተውላችሁ ፤ ዋጋ ፡ አትስጡት ።

ወዳጅ ፡ አታብዙ ። የተወሰኑ ፡ ምርጥ ፡ ወዳጆች ፡ ብቻ ፡ ይኑርዋችሁ። «ሰውን ፡ ውደደው ፡ እንጂ፤ አትመነው»እንደተባለው፤ለማንም፡ ቢሆን ፡ በሐሳባችሁ ፡ ያለውን ፡ ገልጣችሁ ፡ አትንገሩ ፤ እናንተ ፡ ባላሰባችሁትና ፡ ባልተረዳችሁት ፡ መንገድ ፡ ነገራችሁን ፡ ተርጉሞ ፡ ክጉዳት ፡ ላይ ፡ እንዳይጥላችሁ ። ከዚህ ፡ በተረፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤቱ ፡ አይለያችሁ ፡ ልቦናችሁን፡ ያብራላችሁ ፡ ብላ ፡ ምክርዋን ፡ አበረከተችን እናቴ ።

ተስፋ ፡ የቈረጥሽው ፡ እንዴት ፡ ነው ፣ ለሕመምሽ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መድኃኒት ፡ እንፈልጋለን ። ፈቃድሽ ፡ ቢሆን ፡ ሐኪም ፡ ወዳለበት ፡ ከተማ ፡ ይዘንሽ ፡ እንድንሄድ ፡ ተነሽ ፡ አልኳት ።

ልጄ ፡ ተቈርጥዋል ፣ አግኝቼዋለሁ ፣ አትድከም ። የመዳን ፡ ተስፋ ቢኖረኝ ፣ እንድትረዱኝ ፡ ባሳሰብኳችሁ ፡ ነበር ። መላም ፡ የለው ፣ የኔ ነገር ፡ አልቅዋል ። ከሞት ፡ በኋላ ፡ ለሞተ ፡ ሰው ፡ የሚደረገው ፡ ሁሉ ፣ ዋጋ የሌለው ፡ ስለሆነ ፣ ተዝካር ፡ እናወጣለን ፡ ብላችሁ ፡ አትድከሙ። ከፈቃዴ ፡ እንደወጣችሁ ፡ እቈጥረዋለሁ ። ምስጋና ፡ ይድረሰውና ፣ ከተቀበለልኝ ፡ በሰጠኝ ፡ ረዘም ፡ ባለው ፡ ዕድሜ ፡ በእጄ፡የሠራሁት ፡ ይበቃል ። በኀዘንም ፡ በኩል ፣ ለእንደኔ ፡ ላለ ፡ አይታዘንም ። በዕድሜም ፣ የዕድሜ ፡ ደኃ ፡ አላደረገኝም ፣ እስካሁን ፡ አኖረኝ ፣ የምወዳቸው ፡ ባሌ፡ በሞት ፡ ከተለዩኝ ፡ ጀምሮ ፡ ልቦናዬ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ትዳር ፡ ሳይመለስ ፣ ነፍሴ ፡ ከሥጋዬ ፡ በምትለይበት ፡ በዚህ ፡ በዓቴ ፡ ልቦናዬን ፡ ሰጥቸዋለሁ ፡ አለች ።

የምናደርገውን ፡ ማወቅ ፡ አልቻልንም ። ኀዘንና ፡ ትካዜ ፡ ሆነ ። እናቴም ፡ ንግግር ፡ አቆመች ። ዓይንዋን ፡ ገለጥ ፡ እያደረገች ፣ የድካም ሰመመን ፡ ያዛት ። ብናነጋግራትም ፡ መመለስ ፡ አልቻለችም ። ወሃም አልቀበል ፡ አለች ፣ ቀኑ ፡ ወደ ፡ ማታ ፣ ማታው ፡ ወደ ፡ ሌሊት ፡ ተለወጠ ። የእናቴም ፡ ሁኔታ ፡ እየተባባሰ ፡ ትንፋሽዋ ፡ ተለወጠ ። እኛም፡ ተስፋ ፡ ቈርጠን ፡ ልቅሶ ፡ በልቅሶ ፡ ሆን ።

በተለይ ፡ በሐሳቤ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ስለእናቴ ፡ አስታወስኩ ። አባቴ፡ ከሞተ ፡ ጀምሮ ፡ ስለኔ ፡ ትዳር ፡ መያዝና ፡ ራስ ፡ መቻል ፡ የነበራት ፡ ድካም ፣ ስንት ፡ ሰዎች ፡ በኑሮ ፡ ጓደኝነት፡ሲከጅልዋት፣አንዱን፡ ልጇን የእንጀራ ፡ አባት ፡ አላሳየውም ፡ ብላ ፡ ፈተናውን ፡ ሁሉ ፡ እንደተቋቋመች ፣ ትዳር ፡ ከያዝኩ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ንብረቱን ፡ ሁሉ ፡ አስረክባኝ ፣ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ትዳር ፡ ንቃ በዚህች ፡ ጠባብ ፡ ጐጆ ፡ ተኰራምታ ፡ ንጽሕናዋን ፡ ጠብቃ ፡ ኖረች ። ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ በየሳምንቱ፡እየመጣን ፡ በዚህች ፡ ጠባብ ፡ ጐጆ ፡ ስናነጋግራት ፣ የጐጆዋ ፡ ንጽሕናና ፡ መዓዛው ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ በረከትም ፡ እንቀበል ፡ ነበር ። እንግዲህ ፡ በቃ ፣ ተለየችን ፡ ታዛቢ ፡ አጣን ፣ ብዬ ፣ ከሐሳቤ ፡ ጋር ፡ መነጋገሬን ፡ ስጨርስ ፡ በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ አለቀስኩ ።



ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ደነገጡ ። ፀሐይም ፡ ደንግጣ ፣ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ ምን ፡ ይታወቃል ፡ ይድኑ ፡ ይሆናል ፣ ታገስ ፡ ስትለኝ ፣ በሐሳቤ፡ ተመስጬ ፡ የሠራሁት ፡ ታወሰኝና ፡ ዕንባዬን ፡ ጠራርጌ ፡ እናቴን ፡ ዓይን ፡ ዓይንዋን ፡ ተመለከትኩ ።

በኀዘንና ፡ በትካዜ ፡ ስንጠባበቅ ፣ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ እናቴ ፡ የመጨረሻ ፡ ዕረፍት ፡ አደረገች ። ፀሐይና ፡ እኔ ፡ ከላዩዋ ፡ ላይ ፡ ወድቀን ፡ ዕንባ፡በዕንባ ፡ ሆን። አብረውን፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ትግል ፡ ያዙ። ብዙ ፡ አስቸገርን ። ሆኖም ፡ ተቸነፍን ፣ የኀዘን ፡ ስሜቴ ፡ እንዲቀንስ ፡ ስሜ ፡ ልሰናበታት ፡ አልኩ ።

የሞተ ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ ነውና አይሳምም ፣ ለሳሚው ፡ ደግ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ በብርቱ ፡ ከለከሉኝ ። እናት ፡ ናትና ፡ ራሴን ፡ ባለመቈጣጠሬ ፡ ስሜ፡ ተሰናበትኳት ። ከልቅሶዬ ፡ ታግሼ ፡ የቀብሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጸምበትንና ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ እንዲሰማ ፡ ለማድረግ ፡ አስከሬንዋን ፡ ወደቤታችን ፡ ወስደን ፣ ዝግጅቱ ፡ ቀጠለ ።

ዋ ! ሰው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፣ እያለች ፡ እናቴ ፡ ትናገረው ፡ የነበረው ፡ ትዝ ፡ አለኝ ፣ አሁንም ፡ ከንቱ ፡ ነው ። እናቴን ፡ በጊዜዋ ፡ ቍንጅናዋን ፣ ውበትዋን ፣ ደምግባትዋን ፣ አቋቋሟንና ፡ አካሄድዋን ፡ ያየ ፡ ሁሉ ፡ ይማረክ ፡ ነበር ። አባቴ ፡ ከሞተና ፡ ዓለማዊ ፡ ኑሮን ፡ ንቃ ፡ በብቸኝነት ፡ ስትኖር ፣ አካልዋን ፡ መከባከብ ፡ ተወች ። ቢሆንም ፡ በተፈጥሮ ፡ ውበትዋ ፡ አሁንም ፡ ተወዳጅ ፡ ነበረች ። ኻያ ፡ ዐራት ፡ ሰዓት ፡ ለማይሞላ ጊዜ ፡ ተለያይተን ፡ ስንገናኝ ፡ እስማታለሁ ። ትስመኝም፡ አለች።አሁን፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ስትወድቅ ፡ ናፍቆቴን ፡ ቢቀንስልኝ ፣ ስሚያት ፡ ልሰናበታት ፡ ብል፣ ተወዳጅ ፡ የነበረው ፡ የእናት ፡ አካልዋ ፡ የማይሳም ፡ በድን ፡ ነው ፡ በማለት ፣ ሬሳ ፡ አይሳምም ፣ ለሳሚው ፡ አይበጅም ፡ ይበሉኝ ።

ሰው ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ፍጥረት ፡ ነው ። ከዓይኔ ፡ ብሌን፡ አብልጬ፡ እወድሃለሁ ፣ እስብልሃለሁ ፡ ይለው ፡ የነበረው ፡ ሲለየው ፣ ይዳስሰው ፡ ያፈቅረው ፡ የነበረው ፡ ሥጋ ፡ የማይሰማ ፡ በድን ፡ ሲሆን ፡ ይጠላዋል ፣ ይሸሸዋል ! ነገ ፡ በራሴም ፡ አይል ! እያልኩ ፡ በትካዜም ፡ አሰብኩ ።

የቅርብም ፡ የሩቅም ፡ ወዳጅ ፡ ተሰበሰበ ። ሥርዓተ ፡ ፍትሐቱ ፡ ተከናወነ ። አስከሬንዋ ፡ ቍጥሩ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሕዝብ ፡ ታጅቦ ፡ ጉዞው ፡ ቀጠለ ። በሕይወትዋ ፡ በምትኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ባሠራችው ፡ በዓትዋ ፡ አስከሬንዋ ፡ በክብር ፡ አረፈ ። ሕዝቡ ፡ ከመሰናበቱ ፡ በፊት ፡ የገ

ዳሙ ፡ መምህር ፤ «የፍጡር ፡ መጨረሻው ፡ ሞት ፡ ነው ፤ ከሞት ፡ የሚቀር ፡ የለም ፡ ግን ፡ ሞታቸውን ፡ አሳምረው ፡ የሚሞቱ ፡ የተመሰገኑናቸው ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ መለየት ፡ ዕረፍት ፡ እንጂ ፤ ሞት ፡ አይደለም ። ለዚሁም ፡ ሊቁ ፡ ሞት ፡ ማለት ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፡ ነው፤ ያለው፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ። ሰው ፡ ከኃጢአት ፡ የማይነፃ ፡ አዳፋ ፡ ሰውነቱን ፡ አሁን ፡ ታጥቦ ፤ አሁን ፡ እንደሚያቆሽሽ ፤ ውስጣዊ ፡ ሰውነታችንም ፡ እንደዚሁ ፡ አሁን ፡ ቢነፃ ፡ አሁን ፡ በኃጢአት ፡ ያድፋል ። ስለዚህ ፡ እንደቸርነቱ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ኃጢአታችን ፡ አይደለም ።

ሰው ፡ አቅሙ፡ የሚፈቅድለትን፡ ያህል ፡ ከሞተ ፡ ነፍስ ፡ ለመዳን፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፤ ለበጎ ፡ ሥራና ፡ አገልግሎት ፡ ሰውነቱን ፡ ማስገዛት ፡ አለበት ። «በራስህ ፡ ሊያደርጉብህ ፡ የማትወደውን ፡ አንተም ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ አታድርግ» የተባለውን ፡ ከጠበቅን ፡ እግዚአብሔር ፡ አይርቀንም ። የእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ መንፈሱ ፡ ካልራቀን ፡ ሞተ ፡ ነፍስ ፡ አያገኘንም ።

አሁን ፡ እስከሬንዋ ፤ በፊታችን ፡ ያረፈው ፤ የሀብት ፡ ድኃ ፡ አልነበረችም ፤ ሞተ ፡ ነፍስን ፡ ድል ፡ አድርጋ ፤ ሕይወተ ፡ ነፍስን ፡ ለመግዛት ፤ ንጽሕናዋን ፡ ጠብቃ ፡ ከፈጣሪዋ ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ ስትል ፡ ከተድላ ፤ ከደስታ፡ ተለይታ ፡ በዓቷን ፡ አጽንታ ፡ ኖረች ፤ እርሷ ፡ ያገኘችውን ፡ በረከት ፡ ለማግኘት ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ ይደርብን ፡ እንጂ ፤ ለርስዋ ፡ ማልቀስ ፡ የሚገባ ፡ አይደለም»፡ ካሉ ፡ በኋላ ፤ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ ሰጥተው ፡ አሰናበቱን ።

በእናቴ ፡ ሞት ፡ ከኔ ፡ ይልቅ፡ ፀሐይ ፡ በጣም ፡ አዘነች ። በወለደች፡ ጊዜ ፡ በማረስ ፤ ያደረገችላትን ፡ እያስታወሰች ፡ አልቅሳ ፡ ታስለቅሰን ፡ ጀመረ ። እናትዋ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ኀዘን ፡ በማጥበቅዋ ፡ ሐሳብ ፡ ገባቸው ። እኛን ፡ ለማጽናናት፡ ከወር ፡ በላይ ፡ ተቀመጡ ። የሆነ ፡ ሆኖ፡ ውሎ ፡ ሲያድር ፡ የማይረሳ ፡ የለምና ፡ እየረሳን ፡ ሄድን ። በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስንሄድ ፡ መቃብርዋን ፡ እየጐበኘን ፤ ፀሐይ፡ አበባ ፡ ታስቀምጣለች ።

ትዝታዋ፡ ከፊታችን ፡ ሳይጠፋ፤ ከተለየችን ፡ ዓመት ፡ ሆነ ። ብዙ፡ አስለምዳን ፡ ልንረሳት ፡ አልቻልንም። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ሳለን ፤ ፀሐይ ፡ ዐራተኛ ፡ ልጅ ፡ ፀነሰች ፤ በርግዝናዋ ፡ ወራት ፡ እናቴን፡ የበለጠ ፡ አስ



ታወሰቻት ። በርግዝናዋ ፡ ፍርሃት ፡ የማታውቅ ፤ በናቴ ፡ ሞት ፡ ኀዘን፡ ስለተሰማት ፤ ብስጭትና ፡ ፍርሃት ፤ ታየባት ። እናቴን ፡ ረስቼ ፤ ሐሳቤ፡ ለርስዋ ፡ ሆነ ። እናትዋ ፡ በየሳምንቱ ፡ እየመጡ ፡ በማነጋገር ፤ የናቴን ፡ ኀዘን ፡ ለመርሳት ፡ ምክንያት ፡ ሆኑን ። ፀሐይ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከሞላት፡ በኋላ ፡ እናትዋ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ተቀመጡ ።

በዘጠኝ፡ ወር ፡ የርግዝና ፡ ወራት፤ በፀሐይ፡ አጠገብ ፡ ሆና፡ እናቴ፡ ትጠባበቅ ፡ ስለነበር ፤ ይህ ፡ ለፀሐይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትዝታ ፡ ጣለባት ። ይህንኑ ፡ በማስታወስ ፡ እናትዋ ፡ በአጠገቧ ፡ በመገኘታቸው ፡ ፀሐይ ፡ ደስ ፡ ሲላት ፤ እናቴን ፡ ለመርሳት ፡ ባለመቻልዋ ፤ በየምክንያቱ ፡ ታነሣት ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፤ እናትዋ ፡ በቅርብ ፡ ሆነው ፡ ሲከባከብዋት ፤ በይቶት ፡ እግዜሮና ፡ በእናትዋ ፡ ረዳትነት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ።የተመኘችውን ፡ በማግኘትዋ ፡ ሁላችንም ፡ ደስ ፡ አለን ። እናትዋ ፡ ለሁለት ፡ ወር ፡ ሳይለይዋት ፡ ቆዩ ። ከሁለት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ወደቤታቸው ፡ ሄዱ ።

ፀሐይ ፡ በማስተዋል ፡ ተመራመረችና ፤ የሞተ ፡ ሰው ፡ እንደማይመለስ ፡ ዐውቃለሁ ፡ ግን ፡ እማማን ፡ መርሳት ፡ አቃተኝ ። ብዙ ፡ አስለምደውኛል ። ሳስታውሳቸው ፡ መልካም ፡ ሥራቸው ፡ በፊቴ ፡ ድቅን ፡ እያለ ፡ አነባዋለሁ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ እናቴ ፡ ቤትዋን ፡ ትታ ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ ከኔው ፡ ጋር ፡ ባጀች ። «መድኃኒታችን ፡ ሆይ ፡ እንዳንተ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፤ እንደኛ ፡ አይደለም። ይህችን ፡ እናታችንን ፡ ጠብቅልን» እያልን ፡ ኀዘናችንን ፡ መርሳትና ፡ መተው ፡ የሚገባን ፡ ይመስለኛል ፡ አለች ።

ሙት ፡ ዓመትዋ ፡ ድረስ ፡ እያስታወስኩ ፡ አዝን ፡ ነበር ። ከኔ ፡ ያንቺ ፡ እየበዛ ፡ ሲሄድ ፡ አየሁ ። ነፍሰ ፡ ጡር ፡ ስትሆኚ ፤ ሐሳቤ ፡ ሁሉ ፡ ወደአንቺ ፡ በመዛወሩ ፡ ፍጹም ፡ ባልረሳትም ፤ ከልቦናዬ ፡ ኀዘኑ ፡ ተቀነሰ ። «ለሞተ ፡ አታልቅሱ ፤ ለራሳችሁ ፡ አልቅሱ» የተባለውን ፡ እያስታወስን ፤ መርሳት ፡ አለብን ፤ መልካም ፡ አስበሻል ፡ አልኳት ፤ ተስማማን ።

ሥራችን ፡ እየተቃና ፤ ንብረታችን ፡ እየዳበረ ፡ ከምናገኘው ፡ አሥራት ፡ አውጥተን ፤ ለበጎ ፡ አድራጎት ፡ እየሰጠን ፤ ልጆቻችንን ፡ እያስተማርን ፤ ቤተሰቦቻችንን ፡ እያስተዳደርን ፡ በሰላም ፡ ነዋሪዎች ፡ ሆን ።

ልጆቻችን ፡ በአቅራቢያው ፡ በሚገኘው ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጠውን ፡ ትምህርት ፡ አጠናቀቁ ። የተሻለ ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከመኖሪያ ፡ ቤታችን ፡ በመራቁ ፤ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጡ ። ችሎታ ፡ ያለው ፡ መምህር ፡ በማግኘታችን ፡ ቀጥረን ፡ ትምህርታቸውን ፡ ቀጠሉ ። ሠርተን ፡ ራሳችንን ፡ ረድተን ፤ ከኛ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ከመርዳትና ፡ ቤተሰቦቻችን ፡ ከማስተዳደር ፡ በቀር ፡ ከሰው ፡ አንደርስም ፤ በሰው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ አንገባም ። በተለይ ፡ ካልተጠራን ፡ ከሰው ፡ ቤት ፡ አንሄድም ። ውለታ ፡ ላደረጉልን ፡ ውለታ ፡ ለመመለስ ፡ ከምንጠራቸው ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡ ሰው ፡ አይመጣም።ቤተሰብ ፡ ብዙ ፡ ስለሆን ፤ ጊዜያችንን ፡ ከቤተሰቦቻችን፡ ጋር፡ እያሳለፍን ፡ ደስ ፡ ይለናል። ይህ ፡ አኗኗራችን ፡ አስከበረን ፤ አስወደደን ። በርሻና ፡ በንግድ ፡ ሥራችን ፡ በአካባቢው ፡ ከሚኖሩት ፡ ሁሉ ፡ የተሻልን ፡ ሆን ። የከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ ወደ ፡ ቀበሌያችን ፡ መጥተው ፡ የባላገሩን ፡ ልማት ፡ ሲጐበኙ ፤ በቅድሚያ ፡ የሚጐበኙት ፡ የኛን ፡ ነው ። በአቀባበልና፡ በማስተናገድ፡ ረገድ ፡ ከጠበቁት ፡ በላይ ፡ እናደርግላቸዋለን ። የኑሮዋችንን ፡ ደረጃ ፡ ከከተማቼ ፡ ኑሮ ፡ በላይ ፡ ግምት ፡ እየሰጡ ፡ ተደንቀው ፡ ይሄዳሉ ።

በዚህ ፡ አጋጣሚ ፡ ግንኙነት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጅት ፡ ከሚሠሩ ፡ የከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ ተዋውቀን ፤ በሥራችን፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ሌሎች፡ ጐብኝዎችን ፡ ጭምር ፡ ይዘው ፡ እየመጡ ፡ እንደገና ፡ ዐዩን ።

ከመቀራረብ ፡ የተነሣ ፤ ሥራችንን ፡ ለልጆቻችን ፡ እንድናወርስና፡ በልጆቻችን ፡ እየተመራ ፡ ሥራችን ፡ በበለጠ ፡ እየተስፋፋ ፡ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ምክር ፡ አበረከቱን ።

ሐሳባችን ፡ እነርሱ ፡ ባሳሰቡን ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆኑን ፡ ገለጽኩላቸው ። ሐሳባችሁ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፤ ልጆቻችሁን ፡ በከተማ ፡ በአዳሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ብታስተምርዋቸው ፤ ከናንተ፡ የሚወርሱትን፡ ሥራ ፡ በቆየ ፡ ልማድ ፡ ብቻ፡ ከሚሠሩት ፡ በትምህርት ፡ በተገኘ ፡ ልዩ፡ ልዩ ፡ ጥበባዊ ፡ ዕውቀት ፡ እያሻሻሉ ፡ በበለጠ ፡ ለመሥራት ፡ ይችላሉ። በአዳሪ ፡ የሚማሩበትን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መርጠን ፡ በቅርብ ፡ ቀን፡ በጽሑፍ ፡ እናስታውቃችኋለን ፡ አሉን ። ስለመልካም ፡ ሐሳባቸው ፡ አመስግነናቸው ፡ ሄዱ ።

ለጊዜው ፡ በሐሳባችን ፡ ያልመጣ ፤ ልጆቻችን ፡ ከጉያችን ፡ ራቅ፡ ብለው ፡ በአዳሪ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይማሩ ፡ በተባለው ፡ ሐሳብ ፡ ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ ልንነጋገርበት ፡ ወደድሁ ።



ውዴ ፡ ሆይ ፡ እነዚህ ፡ የከተማ፡ ሰዎች ፡ ስለልጆቻችን ፡ የሰጡን፡ ምክር ፡ የሚያነጋግረን፡ ነው ። አባቴ፡ ሞቶ፡ የሴቱና፡ የወንዱን ፡ ሥራ ፡ እናቴ ፡ ይዛ ፡ ታስተዳድር ፡ በነበረበት ፡ ወቅት ፤ ከሚገኘው ፡ ገቢ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሩብ ፡ ቀነሰ ። ሞት ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ጥቃት ፡ ያስገባል ፤ እያለች ፡ እናቴ ፡ አዘነች ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ትምህርቴን ፡ አቋርጬ ፡ አባቴ ፡ ባቋቋመው ፡ ሥራ ፡ ተተክቼ ፡ ልሠራ ፡ ወደድሁ ። ከሥራው ፡ ጋር ፡ አንተዋወቅም ፤ ሆኖም ፡ አባቴ ፡ ሲሠራ ፡ እየተከታተልኩ ፡ ዐይ፡ ስለነበር ፤ በልጅነት ፡ ወራት ፡ ያየሁት ፡ በአዕምሮዬ ፡ ተቀርጾ ፡ ተጠቀምኩበት ።

ልጆቻችን ፡ ሥራችንን ፡ በመመልከት ፡ ላይ ፡ ናቸው ፤ ይህ ፡ እንደዋዛ ፡ የሚያዩት ፡ በአዕምሮዋቸው ፡ ይቀረፃል። ባደጉ ፡ መጠን ፡ እያስታወሱ ፡ ይሠሩበታል ፤ በዚህ ፡ ላይ ፡ ትምህርት ፡ ሲታከልበት ፤ ከኛ ይዞታ ፡ አሻሽለው ፡ በበለጠ ፡ ይሠራሉ ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ልጆቻችን ፡ ለትምህርት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ብንልካቸው ፡ መልካም ፡ የሚሆነው ፡ አልኳት ፡ ፀሐይን ።

ሰው ፡ ጠለቅ ፡ ብሎ ፡ ባደረገው ፡ ምርምር ፡ ራሱን ፡ በመልካም ፡ አስተዳደር ፡ ለመምራት ፡ በቃ ። ይህ ፡ የተገኘው ፡ ከዕውቀት ፡ ሲሆን ፤ ዕውቀት ፡ ከሚመነጭበት ፡ ማዕድ ፡ ልጆቻችንን ፡ ማራቅ፡ የለብንምና፡ ደብዳቤ ፡ እንደደረሰን ፡ መላክ ፡ አለብን ፤ እስከዚያ ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ አዘጋጅ ፡ ብላ ፡ መለሰችልኝ ።

ከማንም ፡ ሐሳብ ፡ ቢቀርብ ፡ ፀሐይ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ሳትቸኩል ፡ ታስባለች ። አስባ ፡ የምትናገረው ፡ ፍሬያማ ፡ ስለሆነ ፡ አይወድቅም ።

በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፤ የዘወትር ፡ ጐብኛችን ፡ ከተፍ ፡ አለ ። ሰላምታ ፡ ከተለዋወጥን ፡ በኋላ ፤ ስለልጆቻችሁ ፡ ትምህርት ፡ ለመነጋገር ፡ መጣሁ ። በበኩላችሁ፡ ምን ፡ ወሰናችሁ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀን።

በሐሳብህ ፡ ተጠቅመንበት ፤ ለልጆቻችን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ አዘጋጅተን ፡ ደብዳቤህን ፡ ስንጠባበቅ ፤ ራስህ ፡ በመምጣትህ ፡ በበለጠ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ አልኩት ።

ሐሳቤን ፡ ልግለጥላችሁ ፡ እንጂ ፤ ሐሳባችሁን ፡ አላወቅሁም ፡ ነበር ። ሐሳቤን ፡ በመቀበላችሁ ፡ አመሰግናችኋለሁ ፡ አለ ፡ የዘወትር ፡ ጐበኛችን ።

የሚገቡበትን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለማየት ፤ እኔም ፡ እሄዳለሁ ፤ አልኩና ፡ ጉዞዋችንን ፡ ሲነጋ ፡ ልንቀጥል ፡ ተስማማን ።

ማታውን ፡ ለልጆቻችን ፡ የመሰነባበቻ ፡ ግብዣ ፡ ተደረገ ። በዕድሜ ፡ አቻ ፡ የሆኑ ፡ ባልንጀሮቻቸው ፡ ተሰበሰቡ ። በውካታ ፡ ግብዣው ፡ ቀጠለ ። የቅርብ ፡ ጐረቤቶችም ፡ በግብዣው ፡ ላይ ፡ ተገኝተዋል ። ግብዣው ፡ ከተጀመረ ፡ ከግማሽ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፤ «ልጆች ፡ በአሁኑ ፡ ዕድሜያችሁ ፡ የሚጐዳችሁንና ፡ የሚጠቅማችሁን ፡ በትክክል ፡ ለይታችሁ ፡ አታውቁም ። የሚነገረውንና ፡ የተባለውን ፡ በአዕምሮዋችሁ ፡ ቀርፃችሁ ፡ ነገ ፡ ማስታወሳችሁ ፡ አይቀርም። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ከሕይወታችሁ ፡ ጋር ፡ የሚኖር ፤ ነገ ፡ የምታስታውሱት ፡ ምክር ፡ ላበረክታችሁ ፡ የምወደው ፤ አለችና ፡ ፀሐይ ፡ ንግግርዋን ፡ ቀጠል ፡ አድርጋ ፤ ከኛ ፡ ተለይታችሁ ፡ የምትሔዱት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕውቀት ፡ ለመገብየት ፤ በምትገበዩትም ፡ ዕውቀት ፡ ወገናችሁንና ፡ ሀገራችሁን ፡ ትረዳላችሁ ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

ትምህርት ፡ ለደግም ፤ ለክፉም ፡ የሚያገለግል ፡ ታላቅ ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑን ፡ ታስታውሳላችሁ ፡ ልጆች ፤

የምትማሩት ፡ ብዛት ፡ ካላቸው ፤ በመልክ ፤ በቋንቋ ፤ በባህል ፤ ከተለያዩ ፡ ጋር ፡ እንደሆነ ፡ ተገንዝባችኋል ?

እንደብዛታቸው ፡ ጠባያቸው ፡ የተለያየና ፤ አስተያየታቸው ፡ ሁሉ ፡ ያንዱ ፡ ካንዱ ፡ እንደማይገጥም ፡ ታውቃላችሁ ?

አባታችሁ ፡ በአባቱ ፡ ተተክቶ ፤ ባድማውን ፡ አስከብርዋል ። እናንተም ፡ ባባታችሁ ፡ ተተክታችሁ ፤ ባድማችንን ፡ እንድታስከብሩ ፡ ምኞት ፡ እንዳለን ፡ ዕወቁ ።

ዕድልና ፡ ጊዜ ፡ ተባብረው ፡ የተማሩ ፤ አባትና ፡ እናታቸውን ፡ ይጠራሉ ። «የወለደ ፡ ያልጸደቀ» እንደተባለው ፡ ወላጆች ፡ አሉበት ፡ ድረስ ፡ ሊጠይቅዋቸው ፡ ሲሔዱ ፤ ከዓይናችን ፡ ጥፉ ፡ እያሉ ፡ አባትና ፡ እናትን ፡ ያባረሩ ፡ እንዳሉ ፡ ይነገራል ።

ማናቸውም ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የምታዩት ፡ ቀላል ፡ መስልዋችሁ ፡ አትናቁ ፤ አትንቀፉ ። እጃችሁ ፡ ላይ ፡ ቢወድቅ ፤ ወይም ፡ ቢገባ ፡ የተሻለ ፡ ማድረግ ፡ ያልቻላችሁ ፡ እንደሆነ ፤ ታሪክና ፡ ትውልድ ፡ ይታዘባችኋል ። ሕሊናችሁም ፡ ይወቅሳችኋል ።



ጥቂቶች ፡ ለጥቅማቸው ፡ ብለው ፡ የሚያደርጉት ፤ በብዙዎች ፡ ላይ ጉዳት ፡ እንደሚያስከትልባቸው ፡ እያሰባችሁ፤ በበጐ ፡ ፈቃድና፡ ሐሳብ ፡ ለሚመሠረት ፤ ከመሥራቾቹ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ሁኑ ፤ አለች ።

አየ ፡ መውለድ ፤ በልጆችና ፡ በወላድ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ አስተሳሰብ ፤ የልጆችዋን ፡ መሔድ ፡ እያስታወሰች ፤ ፀሐይ ፡ ዓይኖችዋ ፡ እንቅልፍ ፡ ሳያዩ ፡ ሌሊቱ ፡ ነጋና ፤ ማለዳ ፡ ተነሥታ፡ ቍርስ ፡ አቀረበች ። ከቍርስ ፡ በኋላ ፡ ጉዝዋችንን ፡ ቀጠለን ። ከጐብኛችን ፡ ጋር ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ እየተለዋወጥን ፡ ጉዞዋችን ፡ አሰልቺ ፡ ጉዞ ፡ ሳይሆን ፤ ከወዳጃችን ፡ ቤት፡ ደረስን ። ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መስተንግዶ ፡ ተደርጐልን ፡ አደርን ።

ጥዋት ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄድን፡ የዓመቱን፡ የትምህርት ፡ ሂሣብ ፡ ከፍዬ ፡ ልጆቼ ፡ ትምህርት ፡ ጀመሩ ።

ወደ ፡ ቤቴ ፡ ከመመለሴ ፡ በፊት ፤ ከተግባሬ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ እየተዘዋወርኩ ፡ ስጐበኝ ፡ ሰነበትኩ ። ባየኋቸው ፡ ትምህርታዊ ፡ አስተያየት ፡ አገኘሁ ። «ማየት ፡ ብርሃን ፡ ነው ፤ አለማየት ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ ነው ፡ » የተባለውን ፡ አስታወስኩና ፡ ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ መጥተን ፡ እንደገና ፡ ብናይ ፡ ጠቃሚ ፡ አስተያየቶችና ፡ አስተሳሰቦች ፡ እንደምናገኝ ፡ አምኜ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ተመለስኩ ።

## ሰ ዎ ች ፡

ይገኛሉ ፡ ሰዎች ፡ ከሰዎች ፡ ተከፍለው ፤
ይለቃሉ ፡ ምድርን ፡ በእግራቸው ፡ ተክተው ።
ሲሄድ ፡ የቀደመው ፡ የመጣው ፡ ሲቆይ ፤
ያለም ፡ ዓመል ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሰውም ፡ ጠባይ ።
ተቃዋሚ ፡ የለም ፡ የተፈጥሮን ፡ ሕግ ፤
ከመሔድ ፡ አይቀርም ፡ ክፉም ፡ ሆነ ፡ ደግ ።
አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ቀድመው ፡ መሄዳቸው ፤
ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ነው ፡ እንዳመጣጣቸው ።
ልጆቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ቆመው ፡ ሲሸኙዋቸው ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ አንዳንድዬ ፡ ልጆች ፡ ይቀድሙና ፤
የሚጥሉት ፡ ኀዘን ፡ ይመታል ፡ ሕሊና ።

ወላጆች ፡ ለልጆች ፡ ያላቸው ፡ ፍቅር ፤
ምንጊዜም ፡ አይጠፋም ፡ እስከ ፡ መቃብር ።

ርኅሩኅ ፡ ናት ፡ እናት ፡ በልጅ ፡ አትጨክንም ፤
በልጅዋ ፡ ላይ ፡ በደል ፡ ማየትን ፡ አትወድም ።

ብሩና ፡ ናት ፡ ዓለም ፡ ቀለም ፡ ትጠጣለች ፤
መጪና ፡ አላፊውን ፡ ትመዘግባለች ፤
ለተከታይ ፡ ትውልድ ፡ ታሪክ ፡ ታቆያለች ።

ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ዓለምን ፡ የመረመራት ፤
እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ይኖራል ፡ ንቋት ።

ሲያምኗት ፡ የምትከዳ ፡ ሲወዷት ፡ የማታውቅ ፤
ናት ፡ የማትጨበጥ ፡ ተፈጥሮዋ ፡ ረቂቅ ።

ለምትጠፋው ፡ ዓለም ፡ ከንቱ ፡ ለምትቀረው ፤
በስንት ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ እጇን ፡ ማጥቀሴ ፡ ነው ።

መጠጥ ፡ ምኞት ፡ ሆኖ ፡ ፍላጎት ፡ ስካር ፤
ዓለም ፡ ምግብ ፡ አቅራቢ ፡ አሳላፊው ፡ ፃዕር ፤
ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ለሚያልፈው ፡ ኀማር ።

ለኀማሩ ፡ ኑሮ ፡ አልፎ ፡ ለሚያልፈው ፤
ጠቅሼ ፡ የሰው ፡ ደም ፡ መብላቴ ፡ ምን ፡ ነው ! ! !

የመረረኝና ፡ የዘገነነኝ !
የዓለም ፡ ጠባይ ፡ ነው ፡ ሰዎች ፡ ምከሩኝ ።



## ክፍል ፡ ፮ ፡

# የአቶ ግሩምና የወይዘሮ ዘነበች ፍቺ

ቤቴንና ፡ ይልቁንም ፡ የምወዳትን ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛዬን ፤ ፀሐይን ፡ ለሁለት ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ ስለተለየኋት ፤ ተነፋፍቀን ፡ ነበርና ፤ እንደ ደረስኩ ፡ አንገት ፡ ለአንገት ፡ ተያይዘን ፡ ተሳሳምን ። የልጆችዋን፡ ጤን ነት ፡ አጥብቃ ፡ ጠየቀችኝ ። ደኅንነታቸውንና ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ነገ ርኳት ። የልጆችዋን፡ ደኅንነት ፡ ሰምታ ፡ ሐሳብዋ ፡ ከተሰበሰበ፡ በኋላ፡ ይቅርታ፡ አለችኝና ፤ ከመንገድ ፡ ገብተህ ፡ እህል ፡ ውሃ ፡ ሳልል ፤ በወሬ፡ ስላደከምኩህ ፡ ተሳስቻለሁ ፡ አለችኝ ።

የልጅ ፡ ናፍቆት ፡ ከፊት ፡ የማይጠፋ ፡ ሆኖ ፡ በቅድሚያ ፡ የልጆ ችሽን ፡ ጤንነት ፡ መጠየቅ ፡ ይቅርታ ፡ የሚያስጠይቅ ፡ አይደለም ፡ ብዬ ፡ ከመለስኩላት ፡ በኋላ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጭውውት ፡ እያደረግን፤ በታ ወቀው ፡ ባልትናዋ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ተመገብን ።

የፀሐይ ፡ እናት ፡ በሌለሁበት ፡ ወቅት ፡ መልክተኞች ፡ መላካቸ ውን ፡ ፀሐይ ፡ ሳትነግረኝ ፤ ሁለተኛው ፡ መልክተኛ ፤ እኔ ፡ እቤቴ ፡ በገ ባሁ ፡ ዕለት ፡ መጣና ፤ ባየነው ፡ ጊዜ ፡ በተለይ ፡ ፀሐይ ፡ ደነገጠች ።

የፀሐይን ፡ እናት ፡ ጤንነት ፡ ደጋግመን ፡ ስንጠያየቅ ፤ ከባላቸው፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ እንደሌላቸው ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ መልክተኛው ፡ ነገ ረን ። ያም ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ሄድን ። የፀሐይ ፡ እናት ፡ በጣም ፡ አዝነውና ፡ ተጐሳቁለው ፡ በመቆየታቸው ፤ አተኩረን ፡ ተመ ለከትናውቸ ። ትክ ፡ ብላችሁ ፡ አያችሁኝ ። በጉስቁልናዬ ፡ እንደሆነ ፡ አትደነቁ ፤ ሁሉንም ፡ ትሰሙታላችሁ ፡ አሉን ።

ከግብግቡው ፡ በኋላ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ አለቀሱ ። ፀሐይ ፡ በእና ትዋ ፡ መጐሳቆል ፡ ስትገረም ፡ በማልቀሳቸው ፡ ምን ፡ ያህል፡ ብስጭት፡ ቢደርስባቸው ፡ ይሆን ፡ ብላ ፡ ተይ ፡ በማለት ፡ ፋንታ ፡ በበለጠ ፡ በማ ልቀስዋ ፤ እናትና ፡ ልጅ ፡ አንገት ፡ ለአንገት ፡ ተያይዘው ፡ ሲያለቅሱ ፡ ያያቸውን ፡ ያስለቅሱ ፡ ነበር ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ አቶ ፡ ግሩም ፡ ትተውን ፡ ወጡ ። እኔ ፡ ብቻ ፡ በመቅረቴ ፡ ምክር ፡ ለበስ ፡ ንግግር ፡ አድርጌ ፡ ልቅሶዋቸውን ፡ አስትቼ ፡ በፍሬ ፡ ነገሩ ፡ እንድንነጋገር፡ አደረግሁ ። የቤቱን፡ ባለቤት ፡ ወጣ ፡ ብዬ ፡ ስጠራ ፣ «ለቅሶም ፡ ጅጌ ፡ አለው ፡ እንዴ ፡ » አሉኝ ። ለመስማት ፡ ቸኩል ፣ ለመናገር ፡ ግን ፡ አትቸኩል » እንደተባለው ፡ መልስ ፡ ሳልሰጥ ፡ ወደቤት ፡ አብረን ፡ ገባን ።

የወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ የእንጀራ ፡ ልጆች ፡ በቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ ግድግዳ፡ ተለጥፈው ፣ በከፍተኛ ፡ ድምፅ ፡ ይስቃሉ ። የሚስቁበት ፡ ምክንያት ፡ ባይታወቅም ፣ ሳቃቸው ፡ ይሰማን ፡ ነበር ።

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ምን ፡ አለ ? አሉና ፣ እኔ ፡ አለቅሳለሁ ፡ የእንጀራ ፡ ልጆቼ ፡ ይስቃሉ ። የኔ ፡ ልቅሶ ፡ ለነሱ ፡ ደስታ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ የተውትን ፡ ለቅሶ ፡ እንደገና ፡ ጀመሩ ። ተፈጥሮዬ ፡ ወንድ ፡ በመሆኑ ፣ ደስ ፡ አለኝ ። ሴት ፡ በመሆናቸው ፡ ያለቅሳሉ ፡ እንጂ ፣ ማልቀስ ፡ ባልተገባቸው ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ለቅሷቸውን ፡ ትተው ፣ በፍሬ ፡ ነገሩ ፡ እንድንነጋገር ፡ ሆነ ።

የሆነውንና ፣ የተደረገውን ፡ መግላለጥ ፣ አብሮ ፡ የመኖር ፡ ተስፋ፡ ሲኖር ፡ ነው ። በዚህ ፡ ቤት ፡ የመኖር ፡ ተስፋዬ ፡ ተቆርጦዋል ። ማንንም ፡ ሳላማክር ፡ ጋብቻ ፡ ፈጽሜያለሁ ። ጋብቻዬንም፡ አፍርሼ፡ ስወጣ፡ ማንንም ፡ ማማከር ፡ የለብኝም ።

በዚህ ፡ ቤት ፡ የማይረሳ ፡ ጉስቍልና ፣ በፊቴ ፡ ላይ ፡ የማድያት ፡ ምልክት ፡ አትርፌያለሁ ። ልጆቼን ፡ የጠራሁ ፡ እንድትወስዱኝ፡ ነው። ከዕለት ፡ ልብሴና ፣ ከሴት ፡ ጌጤ ፡ በቀር ፡ የምፈልገው ፡ የለም ። በባልና ፡ ሚስት ፡ ፍቺ ፡ የነገር ፡ ምዕራፍ ፡ የሚከፈተው ፣ የንብረት፡ መከፋፈል ፡ ሲነሣ ፡ ነው ። በበኩሌ ፡ በንብረት ፡ በኩል ፡ አልጠይቅም ። አልሆን ፡ አለ ፡ እንጂ ፣ ቢሆንማ ፣ ለንብረት ፡ ዋጋ ፡ ከመስጠት ፣ «እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ማንም ፡ አይለያቸውም» የተባለውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ፣ ጋብቻ ፡ እንዳይፈርስ ፡ ነበር ፣ መታገሥ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አልሆነም ። ስለዚህ ፡ ሹልክ ፡ ብዬ ፡ እንደገባሁ ፡ ሹልክ ፡ ብዬ ፡ መውጣት ፡ አለብኝ ፣ ወንድሜ ፡ ጌታዬ ፡ ደኅና ፡ ይዋሉ ፡ ብዬ ፣ በሳቅ ፡ በደስታ ፡ እንድሄድ ፣ እባክዎን ፡ የጋብቻችንን ፡ ውል ፡ እንቅደድ ፡ ብለው ፡ ረጋ ፡ ባለ ፡ አገላለጥ ፡ ተናገሩ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ።



አቶ ፡ ግሩም ፡ አጐንብሰው ፣ መሬት ፡ መሬት ፡ እየተመለከቱ ፣ የወይዘሮ ፡ ዘነበችን ፡ ንግግር ፡ አዳመጡ ። ለጥያቄያቸው ፡ መልስ፡ ይሰጣሉ ፡ ብለን ፡ ብንጠባበቅ ፣ እንዳጐነበሱ ፡ ደቂቃዎች ፡ አለፉ ። የምንሄድበት ፡ ሩቅ ፡ ስለሆነ ፣ ሳይመሽ ፡ እንድንሄድ ፡ እባክዎን ፡ ጌታ ፡ ያስናብቱን ፡ ብለው ፡ እንደገና ፡ ጠየቁ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ።

አቤቱ ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባኝ ። ለጥያቄው ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መልስ ፡ መስጠት፡ ይገባኝ ፡ ይሆን ? ፡ ምን ፡ በደልኩ ፣ ምን፡ አጠፋሁ፣ አጥፍቼም ፡ እንደሆነ ፡ ይቅርታ ፡ ይደረግልኝ ፡ እንዳልል ፡ ጥፋቴና ፡ በደሌ ፡ አልተዘረዘረም ። ራሴን ፡ በራሴ ፡ ስጠይቀው ፣ የምወድሽ ፡ ባለቤቴ ፡ የተከፋሽውና ፡ የተበሳጨሽው ፡ ከልጆቼ ፡ እንደበት፡ በየጊዜው፡ በሚወጡት ፡ መራራ ፡ ቃላት ፡ ነው ። ይህን ፡ አልክድም ። በዚህ ፡ የተነሣ ፡ ልጆቼን ፡ ከቤት ፡ እንዳላስወጣና ፣ አላውቃችሁም ፡ ብዬ ፡ እንዳላባርር ፣ ሰው ፡ ይፈርድብኛል ። የወለደ ፡ ሆድ ፡ የማይፈጽመው ፡ ስለሆነ ፣ ወላድ ፡ ይፍረደኝ ።

የልጆቼን ፡ ጥላቻና ፡ ምግባረቢስ ፡ ንግግር ፡ እየተቀበልሽ ፡ ኑሪ ፡ እንዳልል ፣ ራሴ ፡ የማላደርገውን ፡ አድርጊ ፡ ብዬ ፡ አልፈርድም ። ብፈርድ ፡ ይፈረድብኛል ። ሂጂ ፡ እንዳልል ፣ በኔና ፡ በአንቺ ፡ መካከል ፡ በደል ፡ ሳይኖር ፣ በልጆቼ ፡ ምክንያት ፡ ትዳሬ ፡ በመፈታቱ ፡ ባላዝንም፡ ይገርመኛል ።

እኔን ፡ ያየህ ፡ ተቀጣ ፡ የተባለው ፡ ተረት ፡ በኔ ፡ ደረሰ። የወለደች፡ ሚስቱን ፡ ፈትቶ ፣ ሌላዋን ፡ አግብቶ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ እኖራለሁ፡ የሚል፡ ቢኖር ፣ እንደቂል ፡ ይቈጠራል ። ከንቱ ፡ ነው ፡ ደስታ ፡ የለም ። እንዲያውም ፡ ከሁለት ፡ ያጣ ፣ በሚስቱ ፡ ወይም ፡ በልጆቹ ፡ ሳይወደድ፣ በሐሳብ ፡ እንደዋለለ ፣ እንዳቸውንም ፡ ሳያስደስት ፡ የሚያተርፈው ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ጥላቻ ፡ ነው ።

አሆ ፣ «ጐመን፡ በጤና፡ » የሚሉት፡ አነጋገር፡ ለካስ፡ ያለብልሃት፡ አልተነገረም ፡ አሉና ፣ አቶ ፡ ግሩም ፡ ንግግራቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ወደልጆቼ ፡ ሄድ ፡ ብዬ ፣ እባካችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ተዉ ፣ የምትፈልጉትን ፡ ፍላጐታችሁን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ አሟላለሁ ፣ ጠይቁኝ ። የኑሮዬ ፡ ሰላም ፡ በናንተ ፡ ምክንያት ፡ ተበጥብጦ ፡ አይፍረስ ፣ ስል ፣ እናታችን፡ ባቀናችው ፡ ቤት ፡ ገብታ ፣ እርስዋ ፡ ልትኖር ! አትኖርም ። አንተ ፡ ፍቅር ፡ ይዞህ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ይናገሩኛል ።

እርስዋን ፡ ልጆቼ ፡ ናቸው ፤ በንግግራቸው ፡ አይከፋሽ ፡ ስላት ፤ እርስዎማ ፤ ምን ፡ ቸገረዎ ! ልጆችዎ ፡ ናቸው ፤ ትለኛለች ። ከአንዳቸውም ፡ ሳልሆን ፡ ቀረሁ ። ደግሞስ ፡ የማያውቁት ፡ ሀገር ፡ ይናፍቃል ፡ እንጂ ፤ የሚያውቁትን ፡ ነገር ፡ መላልሶ ፡ በማድረግ ፤ ከመቃጠል ፤ ልጆችን ፡ እያሳደጉ ፡ ብቸኛ ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፡ የሚሻል ፡ መሆኑን ፡ ስለ መረጥኩ ፤ ከአንቺ ፡ የቀረ ፡ ሚስት ፡ የለኝም ። ሕይወቴ ፡ ካለ ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ እኖራለሁ ። ቆርጠሽ ፡ የተነሣሽ ፡ ስለሆነ ፤ የጋብቻችን ፡ ወረቀት ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ይቀደድ ፡ ብለው ፡ በፊታችን ፡ ቀዳደው ፡ ጣሉት ።

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ የቈረጡ ፡ ስለሆነ ፤ እኔና ፡ ፀሐይ ፡ ማግለድም ፡ አልቻልንም ። ከርሳቸውም ፡ መቍረጥ ፤ የአቶ ፡ ግሩም ፡ መበሳጨትና ፤ ተስፋ ፡ ከመቁረጣቸው ፡ የተነሣ ፤ የጋብቻቸውን ፡ ውል ፡ ቀዳደው ፡ ስለጣሉት ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ጣልቃ ፡ ሳንገባ ፡ በዝምታ ፡ አቶ ፡ ግሩምን ፡ ተሰናብተን ፡ ጉዝዎቻችንን ፡ ቀጠልን ።

የአቶ ፡ ግሩም ፡ ልጆች ፡ በአጥር ፡ ላይ ፡ ሆነው ፤ በከፍተኛ፡ ድምፅ ፡ እየተሳሳቁ ፤ በወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ መሄድ ፡ የተሰማቸውን ፡ ደስታ ፡ ገለጹ ። ተሳቀቅሁ ፤ በጣምም ፡ አዘንኩ ።

እንደተከዛችሁ ፡ ሳንጨዋወት ፤ ከመቸው ፡ ደረስን ! ምን ፡ ሆናችሁ ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ፤ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ።

እማማ ፡ የትዳርሽ ፡ መፍረስ ፡ ያንቺ ፡ መበሳጨትና ፡ መጐሳቆል፡ አሳዝኖናል ። አሁን ፡ ባይታወቅሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ብስጭትና ፡ ኀዘን ፤ ከሙሉ ፡ ጤንነት ፡ ምን ፡ ያህሉን ፡ የሚቀንስ፡ ይመስልሻል ! እማማ ፡ ብስጭት ፡ ቀላል ፡ አይምሰልሽ ። ወረርሽኝ ፡ የታመመ ፡ ሰው ፤ በመድኃኒት ፡ ተከላክሎ ፡ ከሞት ፡ ከተረፈ ፤ በእህልና ፡ ውሃ፡ አገግሞ፡ በፊት፡ የነበረውን ፡ ጤንነት ፡ ያገኛል ። በነገር ፡ የተቀጣ ፡ ሰው ፡ ግን ፤ ማገገሚያ ፡ የለውም ፡ ሳያውቀው ፡ ውስጣዊ፡ ሰውነቱ ፡ የተቃጠለ ፡ ስለሆነ፤ ያንን ፡ የሚያስረሳ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ማግኘት ፡ አለበት ። ደስታ ፡ በቀላል ፡ አይገኝም ። እማማ ፡ስለዚህ ፡ ነው ፡ አዝነንና ፡ ተከዝን ፡ ሳንነጋገር ፡ ከቤታችን ፡ የደረስነው ፡ ብላ ፡ መለሰች ፡ ፀሐይ ።



ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ የልጃቸውን ፡ መልስ ፡ አዳምጠው ፤ የፀሐይን ፡ አስተያየት ፡ሰማሁ ፤ ያንተስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ልጄ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁኝ ። በአቶ ፡ ግሩም ፡ ንግግር ፡ ልቤ ፡ ተነክትዋል፡ አልኩና ፤ ርስዎና ፡ አቶ፡ ግሩም ፡ ንብረታችሁን ፡ የፈታችሁ ፡ በሁለታችሁ ፡ መካከል ፡ በተፈጠረ ፡ አለመግባባት ፡ ሳይሆን ፤ በልጆቻቸው ፡ ነው ። አቶ ፡ ግሩም ፡ «አቤቱ ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባኝ » አሉና ፤ ሂጂ ፡ እንዳልል ፡ የምወዳት ፡ ሚስቴ፡እንደምን ፡ ትሂድ ። ኑሪ ፡ እንዳልላት ፡ ልጆቼ ፡ በነገር፡ እሳት ፡ እንደሚያቃጥልዋት ፡ ስለማውቅ ፤ «በራሴ ፡ ቢያደርጉብኝ ፡ የማልወደውን ፡ እንደምን ፡ በርስዋ ፡ እንዲደረግ ፤ ይፈረድብኝ ፡ ብዬ፡ ልፍረድባት ፡» ብለው ፡ የተናገሩት ፡ ከአዕምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ አለ ።

ርስዎ ፡ የወለደ ፡ የምታገባ ፡ ሴት ፤ በቁመናዋ ፡ ገሐነመ ፡ እሳት፡ እንደገባች ፡ አድርገው ፡ ሲናገሩ ፤ ልጅ ፡ የወለደ ፡ ወንድ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሚስት ፡ የሚያገኝ ፡ አይመስልም ። ነገሩን ፡ በጥልቅ ፡ ብንመረምረው ፤ ልጆች ፡ የሚቃወሙት ፡ እናታችን ፡ በደከመችበት ፡ ቤት ፡ ሌላዋ ፡ ገብታ ፡ አትደሰትም ። መንፈስዋን ፡ እንበጥብጠው ፡ ብለው ፡ የሚያደርጉት ፡ ይመስላል ። ልጅ ፡ ያላትን ፡ ያገባ ፡ ወንድ ፡ በንብረትዋ ፡ ቢጠቀም ፤ እንደዚሁ ፡ አባታችን ፡ በደከመበት ፡ መደሰት ፡ የለበትም ፡ በሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ይነካል ።

የወለዱ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ የጋብቻን ፡ ሕግ ፡ እያፈረሱ ፡ ለሚያደርጉት ፡ ማግባትና ፡ ማውጣት ፡ መንፈሳቸው ፡ በነገር ፡ እየተበጠበጠ ፡ ሰላም ፡ ማጣታቸው ፡ እንደቅጣት ፡ ሆኖ ፤ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ስለሚያርማቸው ፤ የልጆቹን ፡ አድራጎት ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ አልነቀፍኩም ።

አቶ ፡ ግሩምና ፡ ርስዎ ፡ ንብረታችሁ ፡ የፈረሰበትን ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ በቅርብ ፡ ሆኜ ፡ ሳውቅ ፡ ለራሴ ፡ ታላቅ ፡ ትምህርት ፡ አግኝቼበታለሁ ። አያምስልብን ፡ እንጂ ፤ እኔና ፡ ፀሐይ ፡ አብረን ፡ ለመኖር ፡ ባንችል ፤ ልጆቼን ፡ እያሳደግሁ ፡ እኖራለሁ ፡ እንጂ ፡ ሚስት ፡ ማግባትን ፡ ንክች ፡ አላደርገውም ። ሰው ፡ ደጉንም ፡ ሆነ ፡ ክፉውን ፡ መማር ፡ የሚችለው ፤ ከሰው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ለሚያስተውል ፡ እናንተ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ናችሁ ።

የእንጀራ ፡ እናት ፤ ወይም ፡ የእንጀራ ፡ አባት ፡ የሚለው ፡ ስም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ትርጉሙ ፡ አልገባኝም ። እንጀራ ፡ እናት ፡ የሚለው ፡

ቃል ፡ ለምን ፡ ገባ ? ያልወለደችውን ፡ የባልዋን ፡ ልጅ ፣ ወይም ፡ ያልወለደውን ፡ የሚስቱን ፡ ልጅ ፡ እየመገቡ ፡ ባሳደጉ ፡ ይሆን ፡ የእንጀራ ፡ እናት ፣ ወይም ፡ የእንጀራ ፡ አባት ፡ የተባለበት ? ዝምድናው ፡ ለእንጀራ ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ይሆንን ። ይህ ፡ አባባል ፡ ራሱ ፡ የልጆቹንም ፡ ሆነ ፡ ከአብራካቸው ፡ ተከፍለው ፡ ላልወለድዋቸው ፣ ልዩ ፡ ስሜት ፡ የሚፈጥር ፡ ነው ። አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ለአንድ ፡ ልጅ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እያደረጉ፡ ካሳደጉ፡ «መውለድ፡ ቋንቋ ፡ ነው » እንደሚባለው ፡ ከአብራካቸው ፡ ተከፍለው ፡ ባይወለዱም ፡ ውለታቸው ፡ ስለሚያስወድዳቸው ፣ እንደወለደ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ መታየታቸው ፡ አይቀርም ፡ ነበር ፡ አልኩና ፡ በሕፃንነት ፡ ወራት ፡ አባታቸው ፣ ወይም ፡ እናታቸው ፡ ሞተውባቸው ፡ በእንጀራ ፡ እናትና ፡ ወይም ፡ በእንጀራ ፡ አባት ፡ ሲያድጉ ፣ አሳዳጊዎቻቸውን ፡ እንደ ፡ ልጆቻቸው ፡ አድርገው ፡ በመመልከት ፡ ሳሉ ፣ የእንጀራ ፡ እናት ፡ ወይም ፡ የእንጀራ ፡ አባት ፡ የሚለውን ፡ የተለምዶ ፡ አነጋገር ፡ ሲያጠኑና ፡ እንዳልወለድዋቸው ፡ ሲያውቁ ፣ ያሳደጉዋቸውን ፡ ውለታ ፡ ረስተው ፡ አስተያየታቸውና ፡ አስተሳሰባቸው ፡ መልኩን ፡ ይለውጣል ፡ አልኳቸው ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፣ እግሬን ፡ አውጥቻለሁ ። እኔን ፡ ያየ ፡ ይቀጣ ፣ እንደሚባለው ፡ ለማውቃቸውና ፡ ለምወዳቸው ፡ ወዮላቸው ፡ እያልኩ ፡ መምከሬ ፡ አይቀርም ፡ አሉና ፣ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ የጭውውታችንን ፡ አቅጣጫ ፡ ወደሌላ ፡ ለወጡት ።

ፀሐይ ፡ ግን ፡ የእናቷን ፡ የወደፊት፡ ሁኔታ ፡ ለመመሥረት ፡ አስባ ፡ እማማ ፡ በትዳር ፡ በኩል ፡ የመኖር ፡ ተስፋሽ ፡ ከተቈረጠ ፡ እቤትሽ ፡ ገብተሽ ፡ መቀመጥ ፡ ስላለብሽ ፣ በቤቱ ፡ የጐደለውን ፡ ማሟላት ፡ አለብን ፣ ከኛ ፡ ጋር ፡ ለመኖር ፡ የምትፈቅጅ ፡ ቢሆን ፣ ቤት ፡ ሥርተንልሽ ፣ ሳንራራቅ ፡ ብንኖር ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ነበር ፡ አለቻቸው ።

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ተከዙ ። እማማ ፡ አሳዘንኩሽ ፡ እንዴ ፣ በሞትኩት ፡ አለችና ፡ ፀሐይ ፡ ልታለቅስ ፡ ዓይንዋ ፡ ዕንባ ፡ ቋጠረ ። ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ቀና ፡ ብለው ፡ ዐይተው ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ ክፉ ፡ ተናግረሽ ፡ ነው ፣ የማዝንብሽ ፡ አሉና ፣ የተከዝኩት ፡ በራሴ ፡ ዕድልና ፡ አጭሩ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ አለመገፋቱን ፡ አስታውሼ ፡ ነው ። የወደፊት ፡ አኗኗሬን ፡ ገና ፡ አልወሰንኩም ፡ ለማሰብ ፡ ጊዜ ፡ ያስፈልገኛል ፡ አሉ ።

ፀሐይ ፡ እናትዋን ፡ በቅርብ ፡ እየተጠባበቀች ፣ የዕለት ፡ ሥራችንን ፡ እያከናወን ፡ ስንኖር ፣ ዘወትር ፡ ልጆችዋን ፡ ታስታውሳለች ።ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከቤት ፡ ሳሉት ፡ ልጆችና ፣ ለቤቱ ፡ አጠባበቅ ፡ እኔ ፡ አለሁ ። ወደ ፡ ከተማ ፡ ሄዳችሁ ፡ ልጆቻችሁን ፡ ብታይዋቸው ፣ ሐሳብሽ ፡ ይቀንሳል ፡ አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ።



መልስ ፡ ሳትሰጥ ፡ ፀሐይ ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ አየችኝ ። ያልተመካከርነበት ፡ ድንገተኛ ፡ ጥያቄ ፡ ሲመጣ ፡ መልስ ፡ ከመስጠትዋ ፡ በፊት ፡ የማይጠገብ ፡ ዓይንዋን ፡ ጣል ፡ አድርጋ፡ ስታየኝ ፡ መልስ ፡ ስጥ ፡ ማለትዋ፡ መሆኑን ፡ ስለማውቅ ፣ ሐሳቡ ፡ መልካም ፡ ነበር ፣ ዳሩ ፡ ግን ፡ ርስምን ፡ ትተን ፡ ለአንድ ፡ ቀን ፡ እንኳን ፡ መሔድ ፡ ደስ ፡ አይለንም ፡ አልኩ ።

ስለአስተሳሰባችሁ ፡ አመሰግናለሁ ፣ ይሁን ፡ እንጂ ፣ እኔን ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ዓይናችሁ ፡ ብሌን ፡ የምትጠብቁኝ ? ሄዳችሁ ፡ ልጆቻችሁን ፡ ዐይታችሁ ፡ መምጣት ፡ አለባችሁ ፡ ብለው ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ በድጋሚ ፡ አሳሰቡን ። ተስማምተን ፡ ለልጆችዋ ፡ የምትወስድላቸውን ፡ ፀሐይ ፡ ስታዘጋጅ ፡ ሰንብታ ፣ ልጆቻችን ፡ ወደሚገኙበት ከተማ ፡ ሄድን ። በቅድሚያ ፡ ከዘወትር ፡ ጐብኛችን ፡ ቤት፡ ደረስን ። እንደአጋጣሚ ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲገባ ፡ ስለደረስን ፣ ከሰማይ ፡ የወረድን ፡ እንግዶች ፡ ሆንበት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ደስታ ፡ ተቀበለን ። ከሞቀ ፡ አቀባበል ፡ ጋር ፡ ሌሊቱን ፡ በርሱ ፡ ቤት ፡ አሳልፈን ፣ በቀኑ ፡ ብርሃን ፡ ልጆቻችን ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሄደን ፡ ከልጆቻችን ፡ ጋር ፡ ተገናኘን ። እንደአጋጣሚ ሆኖ ፣ በዚያን ፡ ቀን ፡ ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዝግ ፡ ስለነበር ፣ ከኻያ ፡ ዐራት ፡ ሰዓት ፡ ያላነሰ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ቆዩ ።

እናትና ፡ ልጆች ፡ ከመነፋፈቃቸው ፡ የተነሣ ፣ ዓይናቸው ፡ በእንቅልፍ ፡ ሳይከደን ፡ በትምህርት ፡ ቤታቸውና ፡ በከተማው ፡ ያዩትን ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ለእናታቸው ፡ አወግዋት ። ፀሐይ ፡ ስሜትዋን ፡ አትግለጥ ፡ እንጂ ፣ ስታዳምጥ ፡ በኀዘን ፡ ትመሰጥ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሆነና ፡ ዓይኖቻቸው ፡ በእንቅልፍ ፡ ተከደኑ ። ከጥዋቱ ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ተነሣን ። ፀሐይ ፡ ከልጆችዋ ፡ በሰማቸው ፡ ቅሬታ ፡ እንደገባት ፡ በሁኔታዋ ፡ ታወቀ ። ከጐብኛችን ፡ ጋር ፡ ሆነን፡ ልጆቻችንን ፡ ተሰነባብተን ፣ ወደማረፊያችን ፡ ስንመለስ ፣ ፀሐይ ፡ ቅሬታዋን ፡ በፊትዋ ፡ ከማስነበብ ፡ በቀር ፣ ልትገልጠው ፡ አልወደደችም ።

የርስዋን ፡ አስተያየት ፡ ሳላውቅ ፡ የራሴን ፡ ልገልጥ ፡ ባለመው ደዴ፡ ሐሳቤን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መራሁና ፤ ከሥራችን፡ ጋር ፡ የተያያዘውን፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ ተዘዋውረን ፡ እንድንመለከት ፡ አሳስ ቢያት ፤ ከሥራችን ፡ ጋር ፡ የተያያዘውንና ፤ ያልተያያዘውንም ፤ ትም ህርት ፡ የሚገኝበትን ፡ ማናቸውንም ፡ የሥራ ፡ አቅዋምና ፡ ድርጅት፡ ልናይ ፡ ተስማምተን ፡ ለዘወትር ፡ ጐብኛችን ፡ አማከርነው ። ርሱም የሐሳባችን ፡ ደጋፊ፡ ሆኖ ፤ በተለይ ፡ ለኛ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑትን ፡ ለይቶ ዝርዝሩን ፡ አቀረበልን ። ቀጠሮም ፡ ተቀብሎልን ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜና ፡ ሰዓት ፡ ተዘዋውረን ፡ ጐበኘን ። ባየነው ፡ ሁሉ ፡ ፀሐይ ፡ በበለጠ ፡ ደስ፡ አላት ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሐሳባችን ፡ ቀድሞን ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡ ስለሄደ ፤ ለመሄድ ፡ ተቻኰልን ። ከቤታችን ፡ ከወጣን ፡ አሥራ ፡ አምስት፡ ቀን፡ ሲሆነን ፤ አስተናጋጃችን ፡ ብንቆይ ፡ ፍላጎት ፡ እንዳለው ፡ ገለጸልን ። ቢሆንም ፡ ፍላጎታችን ፡ ሁሉ ፡ የተፈጸመ ፡ በመሆኑ ፡ ወደቤታችን ፡ ተመለስን ።

ፀሐይ ፡ ከልጆችዋ ፡ የሰማችውን ፡ በሐሳብዋ ፡ ይዛ ፡ ኖሮ ፤ ስለ ልጆቻችን ፡ ትምህርትና ፡ አንዋንዋር እናትዋ ፡ ቢጠይቅዋት ፤ ደኅ ንነታቸውን ፡ ገልጣ ፤ ቅሬታዋን ፡ ዘረዘረች ።

እማማ ፡ አለች ፡ ፀሐይ ፤ በምግብ ፤ በጤና ፡ አጠባበቅ ፡ በመሳሰ ለው ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ይዞታ ፡ አላቸው ። ዳሩ ግን ፤ አንድ ፡ ሌሊት፡ ከኔው ፡ ጋር ፡ አብረን ፡ ስናድር ፤ ናፍቆት ፡ እንደሆነ ፡ እንጂ፤ ዓይናችን፡ በእንቅልፍ ፡ ሳይከደን ፤ እንደተጫወትን ፡ ነጋ ። ጨዋታው ፡ ከነርሱ ፡ ይመነጫል ፡ እኔ ፡ እሰማለሁ ።

የነገሩኝ ፡ በዕድሜያቸው ፡ ሊከተሉት ፡ የማይገባውን ፤ ዕድሜያ ቸው ፡ የማይፈቅድላቸውን ፡ ስለሆነ ፤ በዕድሜ ፡ ሲገፉ ፡ ለዚሁ ፡ ለአወ ጕኝ ፡ ወግ፡ ተገዥ ፡ የሆኑ፡ እንደሆነ ፤ ምኑን፡ ሰው ፡ ሆኑ ፡ ብዬ፡ ሠጋሁ። ሲነግሩኝ ፡ ነገሩን ፡ሁሉ ፡ እንደተቀበሉት ፡ እንጂ፤ የሚያስከትለውን ፡ ጉዳት ፡ ወይም ፡ መጥፎና ፡ ደጉን ፡ ባለማመዛዘናቸው ፤ አሁን ፡ በአዕ ምሮዋቸው ፡ የያዙትን ፡ በሥራ፡ የተጠቀሙበት ፡ እንደሆነ ፤ የወላድ፡ መካን ፡ ልሆን ፡ አይደለምን ፡ ብዬ ፡ ልቤ ፡ ተጨነቀ ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ እንደምን፡ ማወቅ ፡ ቻላችሁ ? ትምህርት፡ ቤቱ ፡ የሚያስተምራችሁ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ ነው ? ብዬ ፡ ብጠይ ቃቸው ፤ «ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ አያስተምርም ።



እንዲያውም ፡ተቃዋሚ ፡ ነው ። ያጠናነው ፡ በዕድሜ ፡ ከገፉት ፡ ተማሪ ዎችና ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የውጭ ፡ መጻሕፍት ፡ ነው » አሉኝ ።

በዚህ ፡ በአሁኑ ፡ ዕድሜ ፡ ልታውቁ ፡ የማይገባውን ፤ የሚያስተ ምራችሁ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው፡ ብዬ ፡ ብላቸው፡ «ከልዩ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ የመጡ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ይሸ ጣሉ ። ለምሳሌ ፡ ስለፍቅር ፡ ለማወቅ ፤ በተለይ ፡ ስለዚሁ ፡ የሚናገረ ውን ፡ ማንበብ ፡ ይቻላል ። ስለሌላውም ፡ እንደዓይነቱ ፡ የሚያስረዳ ፡ በብዛት ፡ አለ ። እንዲያውም ፡ ቋንቋው ፡ አይገባንም ፡ እንጂ ፤በቋንቋ ፡ በስለን ፡ ሁሉንም ፡ እንደልባችን ፡ በምናነብበት ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ እና ውቃለን ፡ ብለው ፡ መለሱልኝ ።

ታዲያ ፡ ልጆቼ ፡ መጻሕፍት ፡ ካነበባችሁ ፤ በአሁኑ፡ ዕድሜያችሁ፤ በአዕምሮዋችሁ ፡ተቀርጾ ፡ ባደጋችሁና ፡ ይልቁንም ፡ ትምህርታችሁን፤ ጨርሳችሁ ፡ በምትወጡበት፡ጊዜ ፡ ልትሠሩት ፡ የሚገባ ፡ ጥበባዊ፡ ሥራ፡ ብታጠኑ ፡ አይሻልምን ?

በአዕምሮ ፡ ተመራማሪነት ፡ የሚሠራ ፡ የጥበብ ፡ ሥራ ፡ በአሳባ ችሁ ፡ ቢቀረጽ፤ ረዘም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ለእረፍት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ስትመጡ፡ ሠርታችሁ ፡ ልታሳዩንና ፤ በናንተ ፡ ሥራ ፡ እኛ ፡ ወላጆቻችሁና ፡ ጠቅ ላላው ፡ ኅብረተሰቡ ፡ ሊጠቀም ፡ ይችላል ። አሁን ፡ ግን ፡ የነገራችሁኝ፡ ራሳችሁን ፡ ከንቱ ፡ አድርጐ ፡ የሚያስቀር ፤ ወላጆቻችሁንም ፡ የሚያሳ ፍርና ፡ የሚያሳዝን ፡ ስለሆነ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምራችሁ ፡ የመከርኳችሁን ፡ ብትከተሉ ፡ ትጠቀማላችሁ ፤ እኔንም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አልኳቸው ።

አዬ ፡ እማማ ፤ አንቺ ፡ ያልሽው ፡ ርግጥ ፡ የተሻለ ፡ ይሆናል ፤ ከት ምህርት ፡ በኋላ ፡ ባለን ፡ ጊዜ ፡ በተለይ፡ በዕድሜ ፡ የገፉና ፤ በትምህርት፡ ደካማ ፡ የሆኑ ፡ ተማሪዎች ፡ ልጆችን ፡ እያጫወቱ ፤ የሚያስቋቸውና ፡ የምንስቀው ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጨዋታ፡ ሲያጫውቱን ፡ ነው ። ከክፍል፡ ትምህርት ፡ በኋላ ፡ ስለትምህርት ፡ ወይም፡ ስለጥበባዊ ፡ ሥራ ፡ ማነው፡ እስከዚህ ፡ ጠለቅ ፡ ብሎ ፡ የሚናገርና ፡ በኛ ፡ ዕድሜ ፡ ላሉት ፡ አንቺ ፡ ያልሽውን ፡ የሚነግረን ፡ የለም ፡ አሉኝ ። ይኸውልሽ ፡ የልጆቻችን ፡ ሁኔታ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፡ ብላ ፡ ፀሐይ ፡ ለእናትዋ ፡ አዋ የቻቻው ።

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ በፀጥታ ፡ አዳምጠው ፤ ልጄ ፡ ጊዜ፡ ተለዋዋጭ፡ ነው ። ሰው ፡ እንደጊዜው ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፤ ከዘመናት ፡ በፊት ፡ በያ

ዘው ፤ በቆየው ፡ ልማድ ፡ ብቻ ፡ ታሥሮ ፡ አይኖርም ። ሰው ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ካልተቈጣጠረ ፤ በሰው ፡ ቊጥጥር ፡ ደኅንነት ፡ አይገኝም ። ሰው ፡ ራሱ ፡ የያዘውን ፡ ለቆ ፡ የሌላውን ፡ የሚይዘውና ፡ የሚከተለው ፡ ለማያውቀውና ፡ ላላየው ፡ ነገር ፡ ጉጉ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ዓለም ፡ ስለተቀራረበ ፡ የአንዱን ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፤ ሌላው ፡ ሲያየው ፡ ከራሱ ፡ ይልቅ ፡ የሌላውን ፡ ቢይዝና ፡ በሌላው ፡ ቢሠለጥን ፤ በአካባቢው ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያወቀ ፡ እየመሰለው ፡ ይሳሳታል ። ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፤ ዘመን ፡ ከተቈጠረ ፡ ጀምሮ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ባደረገው ፡ ትግል ፡ የሰው ፡ አዕምሮ ፡ ይሠራዋል ፡ ተብሎ ፡ ከማይገመት ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ ደርሷል ።

በአዕምሮ ፡ ያደጉና ፡ በአስተያየት ፡ የበሰሉ ፤ የሚጠቅመውን ፡ ሲከተሉ ፤ ገና ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ቡቃያው ፡ ትውልድ ፡ ከሚጠቅመው ፡ ይልቅ ፤ አይጠቅምም ፡ የተባለውን ፡ ስለሚከተል ፤ ጥቅምና ፡ ጉዳቱን ፡ አመዛዝኖ ፡ ካልተመለሰ ፤ የተጠላውን ፡ ፀበለጠ ፡ ያስወድዳል ፡ እንጂ ፡ አያርምም ፤ ልጆ ፡ ልጆቻችን ፡ ደኅና ፡ ይሁኑ ፡ እንጂ ፤ ለዚህ ፡ ሐሳብ ፡ አይግባሽ ፡ አሉ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ።

ቀጥለውም ፡ ወደእኔ ፡ ዘወር ፡ ብለው ፤ አንተስ ፡ ምን ፡ አስተያየት ፡ አለህ? ብለው ፡ ሲጠይቁኝ ፤ ሳቅ ፡ አልኩና ፡ ከርስዎ ፡ የምጠብቀውን ፡ መልስ ፡ ስለሰማሁ ፡ ደስ ፡ አለኝ ። ከልጆችዋ ፡ በሰማቸው ፡ ፀሐይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅሬታ ፡ እንዳደረባት ፤ እዚያው ፡ በነበርኩበት ፡ ወቅት ፡ ባውቅም ፤ እየተዘዋወርን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡ ክፍሎችን ፡ ስንጐበኝ ፤ የረሳችው ፡ ወይም ፡ የተወችው ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ።

እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ ርስዎ ፡ የሰጡት ፡ መልስ ፡ ሁሉንም ፡ ስለሚያጠቃልለው ፤ የምናገረውን ፡ ቀድመው ፡ ስለተናገሩት ፤ የምጨምርበት ፡ ነገር ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። ዓለም ፡ መገናኛ ፡ አጥቶ ፡ በርቀት ፡ ተጋርዶ ፡ በነበረበት ፡ ወቅት ፡ ዐያይም ፤ አይሰማም ፡ ነበር ።

ዓለም ፡ ተቀራርቦ ፡ የዕለቱን ፡ በዕለት ፡ ይሰማል ። አንዱ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ሄዶ ፡ ያያል ፤ ከርሱ ፡ በተሻለ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሲያይ ፤ ራሱንና ፡ የራሱን ፡ ንቆ ፤ የሌላውን ፡ ልውረስ ፡ ይላል ። በዚህ ፡ በመሸጋገሪያ ፡ ዘመን ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ይደባለቃል ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ ሁሉንም ፡ ሞክሮ ፡ ለውጥና ፡ ውጤት ፡ ሲያጣበት ፡ ወደነበረበት ፡ ይመለሳል ።



ልጆቻችን ፡ ልጆች ፡ ስለሆኑ ፤ ተዉ ፡ ቢልዋቸው ፡ ይተዋሉ ። የነርሱ ፡ መተው ፡ ግን ፡ ለጠቅላላው ፡ ደኅንነት ፡ ይሆናል ፡ ወይ? በኃይል ፡ የነፈሰን ፡ ነፋስ ፡ ያው ፡ የነፋሱ ፡ አዛዥ ፡ ካልመለሰው ፡ በቀር ፡ አይመለስም ። ልዩም ፡ ጥፋት ፡ ያስከትላል ። ርግጥ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ ባህልና ፡ ጠባይ ፡ መቃረም ፡ የራስን ፡ ያስረሳል ። ባህል ፡ ከታሪክ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ስለሆነ ፤ ታሪክ ፡ አይረሳም ። ለአመዛዛኝ ፡ ወይም ፡ ለአስተዋይ ፡ ትውልድ ፡ ያስተላልፍና ፡ ታሪኩ ፡ በታሪክ ፡ የሚታሰብበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ፡ አልኳቸው ።

በሉ ፡ ጊዜ ፡ ያመጣውን ፡ ጊዜ ፡ እስኪመልሰው ፡ አሉና ፡ ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፤ ሰው ፡ ያልለመደው ፡ ወይም ፡ የማያውቀውና ፡ ያላየው ፡ በፊቱ ፡ ሲደቀን ፤ አዲሱን ፡ ድቅን ፡ ካለፈው ፡ ጋር ፡ ሲያመዛዝን ፡ ልዩነት ፡ እያየበት ፡ ከቀጠለ ፡ ጥፋት ፡ ያስከትላል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ጊዜ ፡ የሚያመጣውንና ፡ ጊዜ ፡ የሚለውጠውን ፡ የሚያውቅ ፡ የጊዜው ፡ ባለቤት ፡ ስለሆነ ፤ ሰው ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ተለዋዋጭ ፡ ባሕርይ ፡ ሲያይ ፤ ያለበትን ፡ ጊዜ ፡ ክፋት ፡ ይናገራል ። የጊዜ ፡ ክፋት ፡ የለውም ። ጊዜውን ፡ የሚያከፋው ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፤ ሰው ፡ በጊዜ ፡ ሳይለወጥ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ ይለወጣል ፤ ብለው ፡ ንግግራቸውን ፡ ደመደሙ ።

# አወይ ፡ ሰው ፡

አወይ ፡ ሰው ፡ መሆኔ ፡ ደካማ ፡ ፍጡር ፤
ለማውቀው ፡ የንጓሁ ፡ ምን ፡ ሳገኝ ፡ ነበር !!!
የነበረው ፡ ትናንት ፡ ዛሬ ፡ የሌለው ፤
ሳየው ፡ በፍቅር ፡ ላይ ፡ ከዓይኔ ፡ የጠፋው ።
የነበረው ፡ ሲሄድ ፡ የሌለው ፡ ሲተካ ፤
ይመስላል ፡ የሚገኝ ፡ ያልታየ ፡ ፋሲካ ፤
እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሕይወትን ፡ ሊያረካ ።
ልንገራችሁ ፡ እኔ ፡ ስሙኝ ፡ አዳምጡኝ ፤
ከመጀመሪያው ፡ ጋር ፡ እንበል ፡ የሙጥኝ ።
ምን ፡ ይሆናል ፡ ብቻ ፡ ድንገተኛ ፡ መንገድ ፤
በሞት ፡ ኃባዥነት ፡ አለ ፡ ትቶ ፡ መሄድ ።

በታጣው ፡ ሰው ፡ ፈንታ ፡ ሲጠፋ ፡ እሚተካ ፤
ያማር ፡ እንጀራውን ፡ ሊጋግር ፡ ሊያቦካ ፤

ይገደዳል ፡ የግድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ እንደከብት ፤
ይህ ፡ ነውና ፡ ጥንትም ፡ የሕይወቱ ፡ ሥርዓት ።

ነበረ ፡ ተለምዶ ፡ ተንቀባርሮ ፡ ኑሮ ፤
ብስጭት ፡ ተተካ ፡ ካሁኑ ፡ ጀምሮ ።

ባሌ ፡ እኔን ፡ ቢወደኝ ፡ እኔ ፡ ርሱን ፡ ብወደው ፤
አካባቢው ፡ ካለ ፡ መቼ ፡ የሚሆን ፡ ነው ።

አንድ ፡ አካል ፡ በሆኑ ፡ በተመሳሰሉ፤
ለማፍረስ ፡ ጋብቻን ፡ ጣልቃ ፡ ይገባሉ ።

በመልኩ ፡ ሁሉንም ፡ እይዛለሁ ፡ ብል ፤
ከዚያም ፡ ከዚያ ፡ ሳልሆን ፡ ቀረሁ ፡ በማሀል ።

ያልተወለደ ፡ ልጅ ፤ ልጅ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፤
መመኘት ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ይሄዳል ፡ ኮብልሎ ።

ያልተወለደ ፡ ልጅ ፡ ያሳያል ፡ ጥላቻ ፤
ይጥላል ፡ አጋልጦ ለመዘባበቻ ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፤ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ጭንቅ ፤
እያሳደጉ ፡ ልጅ ፡ መኖር ፡ በድብቅ ።

የትዳር ፡ ጋጋታው ፤ ለምን ፡ ነው ፡ ሁካታው ፤
ገብይቶ ፡ ደስታን ፡ ትርፉ ፡ መከራ ፡ ነው ።

ትዳር ፡ ትዳር ፡ ብዬ ፡ የጓጓሁለት ፤
ያን ፡ ዛላ ፡ ያን ፡ ውበት ፡ የሠዋሁለት ፤

አጋለጠኝ ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ ጠቀመኝ ፡ ከቶ ፤
በተስፋ ፡ ለተስፋ ፡ የሚኖረው ፡ ጓጉቶ ፤
መቼም ፡ ተስፋ ፡ አይቆርጥም ፡ ይህን ችግር ፈርቶ ።



ክፍል ፡ ፳ ፡

# የወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ የገዳም ፡ ኑሮ ፡

ወይዘሮ ፡ ዘነበች ፡ ከሟቹ ፡ ባላቸው ፡ ጋር ፡ ያፈሩትን ፡ ማናቸውንም ፡ ሀብት ፡ ለልጃቸው ፡ አስረክበዋል ። ባል ፡ ፈትተው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ እንደተቀመጡ ፤ በድካማቸው ፡ ወደ ፡ ሠሩት ፡ ቤት ፡ እንዲመለሱ ፡ ቢጠየቁ ፤ አለመወሰናቸውን ፡ አስታውቀውን ፡ ነበር ። ነገሩን ፡ ረስተነው ፡ በሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የማነጋግራችሁ ፡ ጉዳይ ፡ አለኝ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፤ ፀሐይ ፡ ደንገጥ ፡ አለችና ፡ ምነው ፡ እማማ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አገኘሽ ፡ ብላ ፡ ጥያቄ ፡ አቀረበች ።

ርሳቸውም ፡ ቀጠል ፡ አድርገው ፤ የማያስደነግጠው ፡ ያስደነግጥሻል ። ልነግራችሁ ፡ ካሰብኩ ፤ ሰንብቻለሁ ። ያንቺን ፡ ድንጉጥነት ፡ እያስታወስኩ ፤ ሳልነግራችሁ ፡ ዘገየሁ ። አኗኗሬን ፡ ገና ፡ ያልወሰንኩ ፡ ስለሆነ ፤ ወደፊት ፡ ወስኜ ፡ እንደምነግራችሁ ፡ ገልጬላችሁ ፡ ነበር ። ራሴን ፡ በራሴ ፡ አነጋገርኩ ። ጥሪ ፡ እስኪደርሰኝ ፡ ድረስ ፡ ማንኛውንም ፡ መንገድ ፡ መከተል ፡ እንደሚሻለኝ ፡ ከልብ ፡ አሰብኩ ። እስተያየቴ ፡ በአንድ ፡ አቅጣጫ ፡ ሳይወሰን ፡ በብዙ ፡ ሁኔታዎች ፡ ተመራመረ ። እስካሁን ፡ ባለኝ ፡ ዕድሜ ፡ በዚህ፡ዓለም ፡ ያገኘሁትን ፡ ትርፍ ፡ አስታወስኩ ። «ቢከፍቱት ፡ ተልባ» እንደሚባለው ፡ ከድካም ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ አተረፍኩ ፡ የምለው ፡ ፈጽሞ ፡ የለም ፡ እንዳልል ፡ አንቺ ፡ ከሰውነቴ ፡ ተከፍለሽ ፡ መገኘትሽን ፡ ብቻ ፡ እንደትርፍ ፡ ስቈጥረው ፡ ሌላው ፡ ከንቱ ፡ ድካም ፡ ነው ።

ይህ ፡ ያለፈ ፡ ሲሆን ፤ ወደፊት ፡ ምን ፡ አገኛለሁ ፡ ብዬ ፡ ሳስብ ፤ ሰውነቴ ፡ እየተዳከመ ፤ ውበቴና ፡ ለዛዬ ፡ እየጠፋ ፤ ዓለምን ፡ ስንቅ ፤ በዓለም ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ የተናቅሁ ፡ እሆናለሁ ።

እንግዲህ ፡ በመጨረሻ ፡ የሚጠብቀኝ ፡ ዕድል ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፤ ለምን ፡ ልበጥበጥ ፡ ብዬ ፡ የመከብብ ፡ እናት ፡ በመጨረሻ፡ጊዜ ፡ የመረጡትን ፡ ከማድነቅና ፡ ከማመስገን ፡ ጋር ፡ ስለመረጥኩ ፤ ርሳቸው ፡ የተከተሉትን ፡ ዓላማ ፡ ተከትዬ ፡ የጥሪ ፡ ደብዳቤዬን ፡ ልጠባበቅ ፡ ምርጫ ፡ ስላደረግሁ ፤ ሐሳቤን ፡ ብታውቁልኝ ፡ እወዳለሁ ፡ አሉ ።